መዝገበ ፡ ፊደል ፡

የግእዝና ፡ ያማርኛ ፡ ቋንቋ ፡ መከፈያ ።

አርእስተ ፡ ክፍላት ፡ ወገጻት ።

(አርእስቶች)	(ክፍሎች)	(ገጾች)
፩ኛ ፡ ፊደል ፡ ከንጓሁ ፡	፲ ክፍል ፡	ከ፯ እስከ ፡ ፲፯
፪ኛ ፡ ፊደል ፡ ከንጓሁ ፡	፭ ክፍል ፡	ከ፲፰ — ፴፪
የፊደላዋሪያ ፡ ለውጥ ፡	፲፭ ክፍል ፡	ከ፴፪ — ፴፱
፫ኛ ፡ ባለዋየል ፡ ፊደል ፡	፱ ክፍል ፡	ከ፵ — ፵፰
የቍጥር ፡ ዐውድ ፡	፭ ክፍል ፡	»፵፰ — ፶፪
የዘመን ፡ ታሪክ ፡	፭ ክፍል ፡	»፶፫ — ፶፱
ውዳሴ ፡ አምላክ ፡	፭ ክፍል ፡	»፶፱ — ፷፬

፪ኛ ፡ መጣፍ ።

መዝገበ ፡ ፊደላት ፡ ሴማውያት ።

ወእማንቱ ፡ ፊደላተ ፡ ግእዝ ፡ ወዐምሐራ ፡

እለ ፡ ምስለ ፡ ሱርስት ፡ ወዐረብ ፡ ወምስለ ፡ ዕብራይስጥ ፡ የኀብራ ።

« የግእዝና ፡ ያማርኛ ፡ ፊደል I የመናዊ ፡ ወይም ፡ ከለዳዊ ፡ የሚባል »

እምኪዳነ ፡ ወልድ ፡ ክፍሌ ፡ ወልደ ፡ አባ ፡ ተክሌ ፡

ተጽሕፈ ፡ ወተኀትመ ፡ ለውሉደ ፡ ጽባሕ ፡ ወሠርክ ፡

በማኅተመ ፡ ሚስዮን ፡ ካቶሊክ ።

ድሬ ፡ ዳዋ ።

፲፱፻፳፯ ፡ ዓ ፡ ም ።

(1934)



ጎድጉ ፡ ሕፃናተ ፡ ይምጽኡ ፡ ኀቤየ ፡ ወኢትክልእዎሙ ። ወደኔ ፡ ይመጡ ፡ ዘንድ ፡ ሕፃናትን ፡ ተዉ ፡ አትከልክሏቸው ። (ማር፲ ፡ ፲፬)

በስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሕያው ፡ ዘይሰመይ ፡ አልፋ ፡ ወሃቤ ፡ ፊደል ፡ ተስፋ ፡ ወጸጋዊ ፡ መምህር ፡ ሱታፋ ፤ ንዜኑ ፡ በጽሒፍ ፡ ወ ናየድዕ ፡ በአፍ ፡ ህላዌ ፡ ቀዳማይ ፡ አልፍ ፡ ወጠባይዐ ፡ ሆይ ፡ ት ሩፍ ፡ ዘጎበኢ ፡ እምሰብእ ፡ ወአዕዋፍ ፡ በላዕተ ፡ መጽሐፍ ። ሎቱ ፡ ስብሐት ፡ ለበኵረ ፡ ምእመናን ፡ ፊደላት ፤ እምአፈ ፡ ደቂቅ ፡ ወ ሕፃናት ፡ ጽሙኣን ፡ ትምህርት ፤ በቃለ ፡ አሚን ፡ ወበትፍሥሕት ፤ አሜን ።

መ ቅ ድ ም ።

ፊደል ፡ ማለት ፡ የነገር ፡ የቃል ፡ ምልክት ፡ አምሳል ፤ ወይም ፡ መግለጫ ፡ ማስታወቂያ ፡ ማ ለት ፡ ነው ፤ ሥዕል ፡ እንደ ፡ ማለት ። ዐይነተኛ ፡ ፍችው ፡ ይኸ ፡ ነው ፤ የቀረውን ፡ በግስ ፡ ይመ ለክቷል ። የፊደል ፡ ተራ ፡ የተፋለሰና ፡ አልፍ ፡ አ ፡ ከርስቱ ፡ ከቀዳማዊነት ፡ ተንቅሎ ፡ በር ሱ ፡ ፈንታ ፡ ሆይ ፡ ሀ ፡ መዠመሪያ ፡ ፊደል ፡ የኾነ ፤ ከግቴ ፡ ብርሃን ፡ ከሚባለው ፡ ከንደኛው ፡ ሰላማ ፡ ከመዠመሪያው ፡ ጳጳስ ፡ ከፍፌ ፡ ምናጦስ ፡ ወዲኽ ፡ ነው ። አበገደ ፡ የነበረውን ፡ ሀለሐ መ ፡ ብለው ፡ ከላይ ፡ እስከ ፡ ታች ፡ ያፋለሱትም ፤ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ አብረው ፡ የነበሩ ፡ ጽርኣውያንን ፡ ቅብጣውያን ፡ ናቸው ፡ ይባላል ። ያፋለሱበትም ፡ ምክንያት ፡ የግእዝን ፡ ፊደል ፡ ከአኃዝነት ፡ አውጥቶ ፡ የርሳቸውን ፡ ፊደል ፡ በግእዝ ፡ ፊደል ፡ ላይ ፡ አኃዝ ፡ አድርጎ ፡ ለማግባት ፤ አል ፋ ፡ ቤታ ፡ ጋማ ፡ የነበረውን ፡ (፩ ፡ ፪ ፡ ፫) አሐዱ ፡ ክልኤቱ ፡ ሠለስቱ ፡ እያሉ ፡ አሳኣያውና ፡ አላምሳያው ፡ ለመጣፍና ፡ ለመፈደል ፤ ወይም ፡ ተሰብስቦ ፡ ባንድ ፡ ወንዝ ፡ እንደሚያድር ፡ እን ደ ፡ ጥምቀትና ፡ እንደ ፡ ገጠር ፡ ታቦት ፡ አንዱን ፡ ባንዱ ፡ ላይ ፡ ለመደረብና ፡ ለማዳበል ፡ እንዲ መቻቸው ፡ ነው ። እንሆ ፡ ይኸ ፡ ከአሐዱ ፡ እስከ ፡ እልፍ ፡ (፩—፼) ያለ ፡ አኃዝ ፡ ከስብዓ ፡ (፯) በቀር ፡ ዅሉም ፡ የጽርእና ፡ የቅብጥ ፡ ፊደል ፡ ነው ። ይኸውም ፡ ሮ ፡ ያሚከሮኝ ፡ ከሚሉ ት ፡ ክታናሹ ፡ ያ ፡ ስም ፡ የመጣ ፡ ነው ። ፱ና ፡ ፹ም ፡ የጽርእ ፡ ሮ ፡ ነው ፤ መልኩ ፡ የግእዝን ፡ የ ፡ ይመስላል ። ፯ና ፡ ፯ም ፡ የጽርእ ፡ ዜታ ፡ (ዜድ) ነው ፤ መልኩ ፡ የገን ፡ ኃምስና ፡ ግልበ ፡ ይመ ስላል ። ፴ና ፡ ፵ ፡ ፶ ፡ ተዛውረውና ፡ ተዘቅዝቀው ፡ አለቦታቸው ፡ አለመልካቸው ፡ ተጥፈዋል ፤ እ ኒኹም ፡ በጽርእና ፡ በቅብጥ ፡ ኒ ፡ ሚ ፡ ላምዳ ፤ በሮማይስጥ ፡ ኤን ፡ ኤም ፡ ኤል ፡ የሚባሉት ፡ ናቸው ። ፸ም ፡ የነሱው ፡ አኃዝ ፡ ነው ፤ መልኩ ፡ ተለውጦ ፡ እንደ ፡ ን ፡ ኹኑዋል ፤ በወዲያ ፡ ግ ን ፡ ራሱ ፡ ግጥም ፡ ነው ፤ እግሩም ፡ ቀጥ ፡ ያለ ፡ ነው ። ጥንታዊውም ፡ የግእዝ ፡ አኃዝ ፡ እንደ ፡ ጽርእ ፡ እንደ ፡ ቅብጥ ፡ እንደ ፡ ዕብራይስጥ ፡ ርሱው ፡ ፉሱ ፡ ፊደሉ ፡ እንጂ ፤ እንዳረብና ፡ እን ደ ፡ ላቲን ፡ ሌላ ፡ ትርፍ ፡ አኃዝ ፡ አልነበረውም ። አጣጣሉም ፡ እንዳረብና ፡ እንደ ፡ ሱርስት ፡ እ

ንደ ፡ ዕብራይስጥ ፡ ክቀኝ ፡ ወደ ፡ ግራ ፡ የንበረው ፡ ተዛውሮ ፡ እንደ ፡ ጽርእ ፡ እንደ ፡ ቅብጥ ፡ ከግራ ፡ ወደ ፡ ቀኝ ፡ ያኽን I የግሡም ፡ አካሄድ ፡ ተለውጠ ፡ ሥሩ ፡ ጣፍ ፡ መጨረሻ I ጣፋ ፡ ሥር ፡ መንሻ ፡ የኽን ፡ በንሱው ፡ እጅ ፡ ነው ። ይኽም ፡ ሐዲስ ፡ ሥራ ፡ የግእዝን ፡ ፊደል ፡ ከጥንታዊ ፡ ሕጉ ፡ ከሴም ፡ ቋንቋ ፡ ዐዋጅ ፡ አውጥቶ ፡ ጥርጊያ ፡ መንገዱን ፡ አጥፍቶ ፡ ቍጥሩን ፡ አሳስቶ ፡ በዚኽ ፡ ብቻ ፡ የቀረ ፡ አይደለም I ከዚኽ ፡ ይልቅ ፡ ደግሞ ፡ ያልፋወያን ፡ ምስጢር ፡ አፍርሷል I (ራእ ፡ ፭ ፡ ፰) ። ከዚያ ፡ ወዲኽ ፡ በኢትዮጵያ ፡ አበገደ ፡ እየተረሳና ፡ እየጠፋ ፡ ሀለሐመ ፡ እየሰፋ ፡ ሂዱል I ኹዋላ ፡ ግን ፡ በኾሎ ፡ አገር ፡ ጠፍቶ ፡ በሸዋ ፡ በስሜን ፡ ስለ ፡ ተገኘ ፡ እኩሉ ፡ የሸዎች ፡ ፊደል ፡ እኩሉ ፡ የስሜኖች ፡ ፊደል ፡ ይሉታል I ፡ ርሱ ፡ ግን ፡ ከጥንት ፡ ከሰላማ ፡ በፊት ፡ የነበረ ፡ አንቲክ ፡ ፊደል ፡ ነው ። አንቲክነቱም ፡ ሊታወቅ ፡ ባኾስም ፡ ሐውልት ፡ በየመንም ፡ በሕምያር ፡ ጥፊት ፡ በየዋሻውና ፡ በየደንጊያው ፡ ተቀርጠ ፡ ይገኛል I በሸዋም ፡ በያድባራቱ ፡ በየገዳማቱ ፡ ይልቁንም ፡ በደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ በቡልጋ ፡ መማሪያቸው ፡ ማስተማሪያቸው ፡ ርሱ ፡ ነው ። ስሙንም ፡ ኹለተኛ ፡ ፊደል ፡ አቡጊዳ ፡ ፊደል ፡ ይሉታል I ባላገሮችም ፡ እንደ ፡ ብርቅ ፡ ያዩታል I (ተረት) አቡጊዳ ፡ የተማሪ ፡ ዕዳ ። ይኽም ፡ ይኽ ፡ ነው I በዚኽ ፡ ላይ ፡ ደግሞ ፡ የ ፊደላችን ፡ ረድፍና ፡ ተራ ፡ አንቲክውና ፡ እውነተኛው ፡ አበገደሀ ፡ እንደ ፡ ኾነ I ሀለሐመሠ ፡ እንዳይደለ I ዐረቦች ፡ ሳይቀሩ ፡ ሌማውያንም ፡ ያፌታውያንም ፡ በቃል ፡ በታሪክ ፡ ይመስክራሉ ። ይልቁንም ፡ በምስር ፡ ያሉት ፡ የንግሊዝ ፡ ሊቃውንት ፡ ግእዝና ፡ ዕብራይስጥ ፡ አንድ ፡ ነው ፡ ሲሉ ፡ ታሪኩን ፡ ከነፊደሉ ፡ በጋዜጣ ፡ ጥፈው ፡ ለዓለም ፡ ኹሉ ፡ ይናኙታል ። እኛም ፡ ደኽን ፡ ታሪኽ ፡ አጥብቀን ፡ ይዘን ፡ ተመርኵዘን ፡ ያቡጊዳን ፡ አሠር ፡ ተከትለን I ንግባእኬ ፡ ነበ ፡ ጥንተ ፡ ንገር ፡ ብለን ፡ ሀለሐመን ፡ ጥለን I ፊደላችንን ፡ ሐሰትና ፡ ስሕተት ፡ በሌለበት ፡ በዚያው ፡ በዱሮው ፡ መንገድ ፡ በዱሮው ፡ አካሄድ ፡ በጥንቱ ፡ ተራ ፡ አበገደ ፡ ብለን ፡ እንጥፋለን ። (ተረት) ጥጃ ፡ ቢሳሳት ፡ ከናቱ ፡ ነገር ፡ ቢሳሳት ፡ ከጥንቱ I ሰይፍ ፡ ቢመስል ፡ ከፎቱ ። በዚኽም ፡ አካሄድ ፡ ሦስት ፡ መልክም ፡ ነገር ፡ አለበት I አንደኛው ፡ ከጥንቱ ፡ መንገድ ፡ ሰተት ፡ ብሎ ፡ መግባት ። ኹለተኛው ፡ ካለም ፡ ቋንቋ ፡ ኹሉ ፡ መስማማት I ፊደሉን ፡ ከኛ ፡ በቀር ፡ በሀ ፡ የሚገምር ፡ የለምና ። ሦስተኛው ፡ በፊደል ፡ ቍጥር ፡ አለመሳት I አለመሳሳት ፡ ነው ።

የግእዝና ፡ ያሟርኛ ፡ ትምርት ፡ ንባቡም ፡ ጥፈቱም ፡ በፊደሉ ፡ ላይ ፡ ይፈጸማል I የፊደሉን ፡ መልክ ፡ ይልቁንም ፡ ይኽን ፡ መዝገበ ፡ ፊደል ፡ ከሥር ፡ እስክ ፡ ጣፋ ፡ በቍጥር ፡ ባጠራር ፡ በጥፈት ፡ በንባብ ፡ ለይቶ ፡ ጠንቅቆ ፡ ካወቁት ፡ ሌላው ፡ አያቅትም I መጽሐፍን ፡ ኹሉ ፡ አለችግር ፡ ማንበብና ፡ መጣፍ ፡ ይቻላል ። ፊደልንም ፡ መቍጠር ፡ ማስቈጠር I መማር ፡ ማስተማር ፡ የሚገባ I በቃል ፡ በጥፈት ፡ በኹለት ፡ ወገን ፡ ነው ፡ እንጂ I ዕዉርና ፡ ሽባ ፡ ካልኾኑ ፡ በቀር ፡ በቃል ፡ ብቻ ፡ መማር ፡ አይበቃም I መምሩንም ፡ ተማሪውንም ፡ ጐደሎ ፡ ያሰኛል ። ሠምና ፡ ፈትል ፡ ካልተዋሐዱ ፡ በየራሳቸው ፡ ብርሃን ፡ እንደሌላቸው I ኹለተኛም ፡ መብል ፡ ያለመጥ ፡ እንጀራ ፡ ያለወጥ ፡ ብቻ ፡ ብቻውን ፡ እንዳያጠግብና ፡ እንዳይጣፍጥ I ትምርትም ፡ ጥፈት ፡ ከሌለበት ፡ እንደዚኽ ፡ ነው ። የግእዝም ፡ ቋንቋ ፡ ትምርቱና ፡ ጎይሉ ፡ የደከመበት ፡ ምክንያት ፡ ይኽ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ዓለም ፡ ኹሉ ፡ ዐውቆታል ። (ተረት) አይጥፍ ፡ መምር ፡ ክንፍ ፡ የለው ፡ ንስር I አይጥፍ ፡ ተማሪ ፡ ክንፍ ፡ የለው ፡ በራሪ I አይጥፍ ፡ ደብተራ ፡ ክንፍ ፡ የለው ፡ አሞራ ።

ይኽ ፡ ፊደል ፡ ለተማሪና ፡ ለቈጣሪ ፡ እንዳሟር ፡ ባሕራሳብ ፡ በሹልክልኪት ፡ መንገድ ፡ ቆሎ ፡ እንዲገኝና ፡ እንዲታወቅ I ትምርቱም ፡ ልጅ ፡ እንዳያሰቅቅ ፡ በብዙ ፡ ዐይነት ፡ ክፍል ፡ ተከፍሎ ፡ በስልት ፡ በስልቱ ፡ ተጥኖል ። አንዳንዱቱን ፡ ክፍል ፡ ይልቁንም ፡ ሥሩን ፡ መዠመሪያውን ፡ ክፍል ፡ ሳያበስኵና ፡ ሳያስተውሉ ፡ እጅ ፡ ሳያደርጉ ፡ ወደ ፡ ሌላው ፡ ማለፍ ፡ አይገባም I አለዚያ ፡ ግን ፡ ትምርቱና ፡ የትምርቱ ፡ ሥራ ፡ ፈጽሞ ፡ ግብዝ ፡ ይኾናል ።

በፊደሉም ፡ ውስጥ ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ የፊደሉን ፡ ጠባይ ፡ የሚያስታውቅ I መምር ፡ ለተማሮች ፡ የሚያንበውና ፡ ኹዋላም ፡ ተማሮች ፡ የሚያንቡት I እንደ ፡ ዚቅና ፡ እንደ ፡ ስርዋጽ ፡ ኹኖ ፡ የገባ ፡ አጣጭር ፡ ቁርጭኝ ፡ የቃል ፡ ተውሳክ ፡ ሐተታና ፡ ታሪክ ፡ አለ ። ዳግመኛም ፡ ፊደሉና ፡ የፊደሉ ፡ ጓዝ ፡ ሲጨረስ ፡ በፊደላዋሪያ ፡ ፈንታ ፡ ሕፃናት ፡ ሊማሩት ፡ የሚገባ ፡ ንባብና ፡ ምስጢር ፡ የሚያስታውቅ I ክሥን ፡ ፍጥረት ፡ እስካሠርቱ ፡ ቃላት ፡ በታናናሽ ፡ ክፍል ፡ የተጣፈ ፡ አጣጭር ፡ ቃል ፡ አለ ። ሦስተኛም ፡ ካሠርቱ ፡ ቃላት ፡ ቀጥሎ ፡ ለእጅ ፡ መኪና ፡ የሚኾን ፡ እንደ ፡ ጽርእና ፡ እንደ ፡ ላቲን ፡ በዋየል ፡ የሚሄድ ፡ ሦስተኛ ፡ ፊደል ፡ ከንመቅድሙና ፡ ከንጓዙ ፡ አለ ። አራተኛም ፡ ከርሱ ፡ ቀጥሎ ፡ ለሒሳብ ፡ ትምርት ፡ የሚጠቅሙ I ኤውሮፖች ፡ ታብል ፡ የሚሏቸው ፡ አራቱ ፡ የቍጥር ፡ ዐውዶች ፡ ወይም ፡ መደቦችና ፡ ሠንጠረዦች ፡ በዚኹ ፡ በግእዙ ፡ አኀዝ ፡ ተጥፈዋል ። አምስተኛም ፡ በመጨረሻው ፡ እጥር ፡ ጐልቄ ፡ ዘመንና ፡ ውዳሴ ፡ አምላክ ፡ አለ ። መላው ፡ የክፍሎች ፡ ቍጥር ፡ ጌታን ፡ ይክተሉት ፡ በንበሩ ፡ በቅዱሳት ፡ አንስት ፡ ምሳሌ ፡ ፴፮ ፡ ነው ። ሥራውም ፡ ንባብንና ፡ ትርጓሜን ፡ ባንድ ፡ ዐይነት ፡ ፊደል ፡ መጣፍ I ወይም ፡ አዛውሮ ፡ ትርጓሜን ፡ በጕልሕ I ንባብን ፡ በረቂቅ ፡ ማተም ፡ ባዋቆችና ፡ በሠራተኞች ፡ ዘንድ ፡ ሥራን ፡ የሚያስንቅፍ ፡ ስለ ፡ ኾነ I ፊደሉና ፡ የግእዙ ፡ ቃል ፡ ንባብ ፡ እንደ ፡ መኾኑ ፡ ስላባትነቱ ፡ በጕልሕ I ያማርኛውም ፡ ቃል ፡ ትርጓሜ ፡ እንደ ፡ መኾኑ ፡ ስለ ፡ ልጅነቱ ፡ በረቂቅ ፡ ፊደል ፡ ተመርቷል ።

ይኽም ፡ ፊደል ፡ የተጣፈበት ፡ ምክንያት I ከርሱ ፡ በኹዋላ ፡ የሚመጣ ፡ የግእዝን ፡ ቃላት ፡ በየፊደሉ ፡ ለይቶ ፡ ንባቡን ፡ በጥፈት ፡ የሚያሰናዳ I ፍችውንም ፡ አምልቶ ፡ አስፍቶ ፡ ብዙ ፡ ምስክር ፡ ሰጥቶ ፡ በብዙ ፡ ዐማርኛ ፡ የሚያስረዳ I ያማርኛንም ፡ ቃል ፡ ከግእዝ ፡ ቃላት ፡ የሚያዛምድና ፡ የሚያዋሕድ ፡ ሌላ ፡ ሐዲስ ፡ ታላቅ ፡ መጽሐፈ ፡ ግስ ፡ አለና I ለዚያ ፡ ለመጭው ፡ መፅ ፡ ፊታውራሪ ፡ ዐዋጅ ፡ ነጋሪ ፡ እንዲኾን ፡ ነው ። መቅድሙም ፡ ከዚያኛው ፡ መቅድም ፡ ተለቅሞ ፡ ተቀሥሞ ፡ በክፍል ፡ የመጣ ፡ ነው ። ፊደልነቱም ፡ በመዠመሪያው ፡ ገጽ ፡ ለውስደ ፡ ጽባሕ ፡ ወሠርክ ፡ እንደ ፡ ተባለ I ለልጅም ፡ ላዋቂም ፡ ለኹሉ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ለልጅ ፡ ብቻ ፡ አይደለም I እንዲያውም ፡ ስለ ፡ ብርታቱ ፡ ክልጆች ፡ ይልቅ ፡ ላዋቆች ፡ ይጠቅማል ። መብልዕስ ፡ ጽኑዕ ፡ ለልሂቅ ፡ እንደ ፡ ተባለ I (፩ብ ፡ ፭ ፡ ፲፬) ። ለልጅ ፡ ያሉትም ፡ ላዋቂ ፡ መትረፉ ፡ ከጥንት ፡ የቈየ ፡ ነው ። (ተረት) በልጅ ፡ አመክኝቼ ፡ ይበሏል ፡ እንጉቶ ።

(፭)

ፊደላት ፣ ግእዝ ፣ በበአሐዱ ።

አንዳንዱ ፣ ፊደል ፣ ግእዝ ፣ ግእዙ ፣ ብቻ ።

አ	መ
በ	ነ
ገ—ጐ	ሠ
ደ	ዐ
ሀ	ፈ
ወ	ጸ
ዘ	ፀ
ሐ	ቀ—ቈ
ጎ—ጘ	ረ
ጠ	ሰ
የ	ተ
ከ—ኰ	ጰ
ለ	ፐ

(፮)

በበክልኤቱ ።

ኹለት ፣ ኹለቱ ።

አበ
ገደ
ሀወ
ዘሐ
ጎጠ
የከ
ለመ
ነሠ
ዐፈ
ጸፀ
ቀረ
ሰተ
ጰፐ

ዲቃሎችና ፣ ዐማርኛች ፣ ካሥራኁዱ ፣ የተወለዱ ።

ጐ-ጐ
ከ-ቈ
ደጀ
ዘገዐ
ጠፈ
ከሸ
ነኘ
ሰሸ
ተቸ
ጀዘ
ፈ ሸ
ኘ (ኛ)
ሸቸ

(፯)

አኃዝ ፣ አው ፣ ጕልቍ ።

ቍጥር ፣ ካንድ ፣ እስካሥር ፣ በሦስት ፣ ዐይነት ፣ ፊደል ።

(ግእዝና ፣ ጽርእ ፣ ሀንድ)

አ	በ	ገ	ደ	ሀ	ወ	ዘ	ሐ	ጠ	የ	።
፩	፪	፫	፬	፭	፮	፯	፰	፱	፲	።
1	2	3	4	5	6	7	8	9	10	.

(፰)

ስመ ፣ ሰብዐ ፣ ፊደላት ፣ ወጕላቄሆን ።

የሰባቱ ፣ ፊደላት ፣ ስምና ፣ ቍጥር ፣ በግእዝና ፣ ባማርኛ ።

አልፍ ፣ አ ።	ዐይን ፣ ዐ ።
አ—(ግእዝ)	ዐ—ፍኛ ።
ኡ—(ካዕብ)	ዑ—ፍኛ ።
ኢ—(ሣሊ)	ዒ—ርኛ ።
ኣ—(ራብዕ)	ዓ—ፍኛ ።
ኤ—(ኃ)	ዔ—ፍኛ ።
እ—(ሳ)	ዕ—፯ኛ ።
ኦ—(ሳብዕ)	ዖ—፯ኛ ።

ከአልፉ ፣ አ ፣ ድምጥ ፣ የዐይኑ ፣ ዐ ፣ ድምጥ ፣ ይበረታል ፤ አልፍ ፣ አ ፣ እንደ ፣ ሆይ ፣ ሀ ፣ ነው ፤ ዐይን ፣ ዐ ፣ ግን ፣ እንደ ፣ ሐውት ፣ ሐ ፣ ይነገራል ፤ ኹሉም ፣ የኮረሮ ፣ ናቸው ፤ ጸታቸው ን ፣ ባፏፍኖው ፣ ክፍል ፣ ተመልከት ። መዋረሳቸውም ፣ ባፏኛው ፣ ክፍል ፣ ተጥቅል ።

(፯)

ከሎን ፣ ፊደላተ ፣ ግእዝ ፣ በበሰብዐ ።

መላው ፣ የግእዝ ፣ ፊደሎች ፣ ሰባት ፣ ሰባቱ ።

አ	ኡ	ኢ	ኣ	ኤ	እ	ኦ
በ	ቡ	ቢ	ባ	ቤ	ብ	ቦ
ገ	ጉ	ጊ	ጋ	ጌ	ግ	ጎ
ደ	ዱ	ዲ	ዳ	ዴ	ድ	ዶ
ሀ	ሁ	ሂ	ሃ	ሄ	ህ	ሆ
ወ	ዉ	ዊ	ዋ	ዌ	ው	ዎ
ዘ	ዙ	ዚ	ዛ	ዜ	ዝ	ዞ
ሐ	ሑ	ሒ	ሓ	ሔ	ሕ	ሖ
ጎ	ጉ	ጊ	ጋ	ጌ	ጎ	ጮ
ጠ	ጡ	ጢ	ጣ	ጤ	ጥ	ጦ
የ	ዩ	ዪ	ያ	ዬ	ይ	ዮ
ከ	ኩ	ኪ	ካ	ኬ	ክ	ኮ
ለ	ሉ	ሊ	ላ	ሌ	ል	ሎ

መ	ሙ	ሚ	ማ	ሜ	ም	ሞ
ነ	ኑ	ኒ	ና	ኔ	ን	ኖ
ሠ	ሡ	ሢ	ሣ	ሤ	ሥ	ሦ
ዐ	ዑ	ዒ	ዓ	ዔ	ዕ	ዖ
ፈ	ፉ	ፊ	ፋ	ፌ	ፍ	ፎ
ጸ	ጹ	ጺ	ጻ	ጼ	ጽ	ጾ
ፀ	ፁ	ፂ	ፃ	ፄ	ፅ	ፆ
ቀ	ቁ	ቂ	ቃ	ቄ	ቅ	ቆ
ረ	ሩ	ሪ	ራ	ሬ	ር	ሮ
ሰ	ሱ	ሲ	ሳ	ሴ	ስ	ሶ
ተ	ቱ	ቲ	ታ	ቴ	ት	ቶ
ጰ	ጱ	ጲ	ጳ	ጴ	ጵ	ጶ

(፰)

ጠባይዐ ፣ ሰብዑ ፣ ፊደላት ።

የሰባቱ ፣ ፊደላት ፣ ጠባይ ።

(ታሪክ)

ክካዕብ ፣ እስከ ፣ ሳብዕ ፣ ያሉ ፣ ስድስት ፣ ስድስቱ ፣ ፊደሎች I ጸና ፣ ጥም ፣ ሳይቀሩ ፣ ኹዋላ ፣ በዘመነ ፣ ሐዲስ ፣ በፍሬ ፣ ምናጦስ ፣ መጻሕፍት ፣ ክጽርእ ፣ ወደ ፣ ግእዝ ፣ ሲመለሱ ፣ ያን ፣ ጊዜ ፣ ተጨምረዋል ። ከዚያ ፣ በፊት ፣ ግን ፣ በመዠመሪያው ፣ ክፍል ፣ እንደ ፣ ጣፍነው ፣ ግእዝ ፣ ብቻ ፣ እንጂ ፣ ከግእዝ ፣ በቀር ፣ ነቍጣ ፣ ቅጥል ፣ ያለው ፣ ሌላ ፣ ዐይነት ፣ ፊደል ፣ አልነበረ ም I ቋንቋውም ፤ ስሙን ፣ ከፊደሉ ፣ ነሥዶ ፣ ግእዝ ፣ የተባለ ፣ በዚኽ ፣ ምክንያት ፣ ነው ፣ ይባላ ል ። ጸና ፣ ጥም ፣ ኹለቱ ፣ ስላንድ ፣ ናቸው I ጸ ፣ ሲላላ ፣ ፕ I ፕ ፣ ሲጠብቅ ፣ ደግሞ ፣ ጸ ፣ ይባ ል ፣ ነበረ ፣ ይሉናል I የተጨመሩም ፣ ከውጭ ፣ አገር ፣ ቋንቋ ፣ ለመስማማት ፣ ነው I ይኽውም ፣ ሊታወቅ ፣ በጸና ፣ በፐ ፣ የሚጣፍ ፣ ቃል ፣ ኹሉ ፣ በጽርእና ፣ በቅብጥ ፣ በሮማይስጥ ፣ ፕ ኹኖ ፣ ይገኛል ። ጸ ፣ የሳባ ፣ ፊደል ፣ ይባላል I ፐም ፣ የጽርእ ፣ ት ፣ ነው I ፕ ፣ መባሉ ፣ በግእዝ ፣ ብቻ ፣ እንጂ ፣ በሌላ ፣ አይደለም ። ፕ ፣ በዕብራይስጥም ፣ አለ I የፈ ፣ ድርብ ፣ ነው I አለነቍጣ ፣ ፈ ፣ የ ሚባለው ፣ ነቍጣ ፣ ሲኾንበት ፣ ፕ ፣ ይባላል ።

(ጠ ባ ይ)

ግእዝና ፣ ሳድስ I ካዕብና ፣ ሳብዕ I ግልስና ፣ ኃምስ I አሊኽ ፣ ሦስቱ ፣ ጥንድ ፣ ፊደሎች ፣ ኹለት ፣ ኹለቱ ፣ ርስ ፣ በርሳቸው ፣ ተወራራሾች ፣ ስለ ፣ ኾኑ ፣ በሸማኔ ፣ ዝሓ ፣ ይመስላሉ ። ጥን ዱ ፣ ዝሓ ፣ በኹለት ፣ መሕን ፣ ተጠልፎ ፣ ካርቡ ፣ ጥርስ ፣ ካንዳንዲቱ ፣ ጕድጓድ ፣ ቀበሎ ፣ እየገ ባ ፣ ሲሠራ ፣ በመቂናጦና ፣ በመርገጫ ፣ ወደ ፣ ላይ ፣ ወደ ፣ ታች ፣ እንዲል ፣ እነዚኽም ፣ እንደዚ ያ ፣ ናቸው I የድምጣቸው ፣ ስልት ፣ ድፋትና ፣ ቅናት ፣ ተብሎ ፣ በኹለት ፣ ስም ፣ ይጠራል ። የግ እዝ ፣ የኃምስ ፣ የሳብዕ ፣ ስልት ፣ ቅናት I የክዕብ ፣ የግልስ ፣ የሳድስ ፣ ስልት ፣ ድፋት ፣ ይባላል I በ ዚኹም ፣ ዐቢይና ፣ ንኡስ ፣ አለበት ። ራብዕ ፣ ግን ፣ አጣማጅ ፣ የሌለው ፣ ቀንጃ ፣ ስለ ፣ ኾነ ፣ የድ ምጡ ፣ ስልት ፣ እንዳራራይ ፣ ዜማ ፣ ለብቻው ፣ ነው I በጣም ፣ አፍ ፣ ያስከፍታል I ቃል ፣ ያገነታ ል I በሴት ፣ አንቀጽ ፣ ላንድም ፣ ለብዙም ፣ ለሩቆች ፣ ብቻ ፣ ዝርዝር ፣ ይኾናል ። ግእዝ ፣ በጥቂ ቱ ፣ አፍ ፣ ያስከፍታል I እንደ ፣ ራብዕ ፣ ቃል ፣ አያገነታም I ሳድስም ፣ የግእዝ ፣ ወራሽ ፣ ስለ ፣ ኾ ነ ፣ እንደ ፣ ትንፋሽ ፣ ነው I ጕሀና ፣ የለውም ። ካዕብና ፣ ሳብዕ ፣ እንደ ፣ ፉጨት ፣ ናቸው I አፍ ን ፣ ማጥበብና ፣ ማሾል ፣ ማሞጥሞጥ ፣ ይሰማማቸዋል ። ግልስ ፣ እንደ ፣ ግቅ ፣ ጥርስ ፣ ያስፈለ ቅቃል I ኃምስ ፣ ወደ ፣ ጎን ፣ አፍ ፣ ያስለቅቃል ። የቅጥላቸው ፣ ጠባይ ፣ ከየት ፣ መጠውና ፣ ሐ ተታው ፣ በሦስተኛው ፣ ፊደል ፣ ተጥፍል ።

(፷)

በበአሐዱ ፣ ወበበክልኤቱ ።

ቀንኛና ፣ ቅንጁ ፤ እንደ ፣ መገመሪያው ።

አ ፣	ኡኢ ፣	አኤ ፣	እአ ።	ለ ፣	ሉሊ ፣	ላሌ ፣	ልለ ።
በ ፣	ቡቢ ፣	ባቤ ፣	ብበ ።	መ ፣	መ·ሚ ፣	ማሜ ፣	ምሞ ።
ገ ፣	ጉጊ ፣	ጋጌ ፣	ግገ ።	ነ ፣	ኑኒ ፣	ናኔ ፣	ንኖ ።
ጐ ፣	ጉጓ ፣	ጌጕ ፣	— ።	ሠ ፣	ሡሢ ፣	ሣሤ ፣	ሥሦ ።
ደ ፣	ዱዲ ፣	ዳዴ ፣	ድዶ ።	ዐ ፣	ዑኢ ፣	ዓኤ ፣	ዕዖ ።
ሀ ፣	ሁሂ ፣	ሃሄ ፣	ሀሆ ።	ፈ ፣	ፉፊ ፣	ፋፌ ፣	ፍፎ ።
ወ ፣	ዉዊ ፣	ዋዌ ፣	ውዎ ።	ጸ ፣	ጹጺ ፣	ጻጼ ፣	ጽጾ ።
ዘ ፣	ዙዚ ፣	ዛዜ ፣	ዝዘ ።	ፀ ፣	ፁፂ ፣	ፃፄ ፣	ፅፆ ።
ሐ ፣	ሑሒ ፣	ሓሔ ፣	ሕሖ ።	ቀ ፣	ቁቂ ፣	ቃቄ ፣	ቅቆ ።
ጎ ፣	ጉጊ ፣	ጋጌ ፣	ጎኖ ።	ቈ ፣	ቊቂ ፣	ቋቌ ፣	— ።
ጐ ፣	ጉጓ ፣	ጌጕ ፣	— ።	ረ ፣	ሩሪ ፣	ራሬ ፣	ርሮ ።
ጠ ፣	ጡጢ ፣	ጣጤ ፣	ጥጦ ።	ሰ ፣	ሱሲ ፣	ሳሴ ፣	ስሶ ።
የ ፣	ዩዪ ፣	ያዬ ፣	ይዮ ።	ተ ፣	ቱቲ ፣	ታቴ ፣	ትቶ ።
ከ ፣	ኩኪ ፣	ካኬ ፣	ክኮ ።	ጸ ፣	ጹጺ ፣	ጻጼ ፣	ጽጾ ።
ኰ ፣	ኩኳ ፣	ኬኵ ፣	— ።	ፐ ፣	ፑፒ ፣	ፓፔ ፣	ፕፖ ።

(፮)

ደ ቃ ል ው ።

ዲ ቃ ሎ ች ።

ከንዚኽ ፣ ክ'ቫያ ፣ ስድስቱ ፣ ደግሞ ፣ አስቀድመን ፣ በመገ'መሪያው ፣ ክፍል ፣ እንዳሳየን ፤ መ ልክቶውንና ፣ ድምጣቸውን ፣ አካሄዳቸውን ፣ ለውጠው ፣ ካዕብና ፣ ሳብዕ ፣ ትተው ፣ በሕጹጽነት ፣ የሚጣፉ ፣ ሕጹጻን ፣ ዲቃሎች ፣ ያሏቸው ፣ አሥት ፣ ፊደሎች ፣ አሉ ። ፊደሎቹና ፣ ዲቃሎቹም ፣ እነዚኽ ፣ ናቸው ። ገጎክቀና ፣ ጐጐኰቈ ።

ገ)	ገ॰	ገ፡	ጓ	ጌ	ገ፡
ጎ)	ጎ॰	ጎ፡	ጏ	ጔ	ጎ፡
ከ)	ከ॰	ከ፡	ካ	ኬ	ክ፡
ቀ)	ቈ	ቀ፡	ቋ	ቌ	ቀ፡

ካዕብ ፣ መተዋቸው ፣ የካዕቡን ፣ ቃል ፣ ዐምስቱ ፣ ኹሉ ፣ ስለ ፣ ደረቡት ፣ ነው ፤ ባምስቱ ፣ ኹሉ ፣ የካዕብ ፣ ድምጥ ፣ አለ ፤ ይኽነንም ፣ የቅጥላቸው ፣ መንታነት ፣ ያስረዳል ። ሳብዕ ፣ መተዋ ቸውም ፣ የሳብዑን ፣ ቃል ፣ ግእዛቸው ፣ ስለ ፣ ደረበው ፣ ነው ፤ በግእዛቸው ፣ ላይ ፣ በያንዳንዱ ፣ ኹሉ ፣ የካዕብና ፣ የሳብዕ ፣ ድምጥ ፣ አለ ፤ ይኽነንም ፣ የቅጥሉ ፣ ቀለበትነት ፣ እንደነሆሎፎ ፣ እን ደንሮቆቶ ፣ መኾኑ ፣ ያስረዳል ። ያምስቱ ፣ ኹሉ ፣ ቅጥላቸው ፣ መንታና ፣ ቀለበት ፣ መኾኑ ፣ የድ ምጣቸውን ፣ ቱሳሔና ፣ ጉሠት ፣ ቅልቅልነት ፣ ያሳያል ። ከዚኽ ፣ የቀረዉን ፣ ሐተታ ፣ በሦስተኛ ው ፣ ፊደል ፣ ተመልከት ፤ በታው ፣ ከዚያ ፣ ስለ ፣ ኾነ ፣ በሰፊው ፣ ተጥቶል ።

ዳግመኛም ፣ በግኣኳቋ ፣ አምሳል ፣ ካሥራ ፣ ኹለቱ ፣ የግእዝ ፣ ፊደሎች ፣ (በደዘጠለመነፈጸረ ሰተ) ክየፊብዓቸው ፣ የተዲቀሉ ፣ ዐሥራ ፣ ኹለት ፣ ራብዖች ፣ ብቻ ፣ ይገኛሉ ። ከነዚያውም ፣ አራ ቱ ፣ እንደነዚኽ ፣ ለግእዝም ፣ ላማርኛም ፣ ቃል ፣ ይስማማሉ ። ስምንቱ ፣ ግን ፣ ዐማርኞች ፣ ናቸ ው ፤ ካማርኛውም ፣ ፊደሎች ፣ ከሰባቱ ፣ ራብዕ ፣ የተዲቀሉ ፣ ሰባት ፣ ራብዖች ፣ አሉና ፤ ኹሉም ፣ ዐሥራ ፣ ዘጠኝ ፣ ኹነው ፣ ባሥራ ፣ ሦስተኛው ፣ ክፍል ፣ ከናገባባቸው ፣ ተጥፈዋል ።

የገሾና ፣ የጨ ፣ የኸ ፣ አጣጣፍ ።

የገሾ ፣ አጣጣፍ ፣ ጥንቱ ፣ እንደዚኸ ፣ ነበረ ፣ ጋርጋይ I ዛሬም ፣ በባላገር ፣ እንዲኹ ፣ ይጣፋ ል I ፈረንጆችም ፣ በኸ፡ ፈንታ ፣ ይኸን ፣ ጋ፡ ፣ እየጣፉ ፣ አስመልኩና ፣ አስስሙ ፣ ሳድስ ፣ ይሎታ ል ። ዐይናሞችና ፣ ልባሞች ፣ ግን ፣ ቅጥሉ ፣ በላይ ፣ በታች ፣ ሲኾን ፣ ግልሱ ፣ ኃምሱ ፣ አይለይም ና ፣ በላይ ፣ ብቻ ፣ ይኹን ፣ ብለው ፣ የታችኛውን ፣ አስቀርተውታል ። በገ፡ ፈንታ ፣ ጀን ፣ ጅብ ፣ ጆሮ ፣ ቁንጆ ፣ ጀግና ፣ ጀመረ ፣ እያሉ ፣ መጣፍ ፣ አይገባም ። በጀ ፣ ፈንታ ፣ ደግሞ ፣ ዠን ፣ ል ዥ ፣ ውላዥ ፣ ቅናዥ ፣ ፍናዥ ፣ እያሉ ፣ የሚጥፉ ፣ አሉ ። የጨ ም ፣ አጣጣፍ ፣ ቅጥሉ ፣ በኹ ለት ፣ እግሮቹ ፣ ብቻ ፣ እንጂ ፣ በሦስተኛ ፣ እግሩ ፣ እንዳባቱ ፣ ነው I ከካዕብና ፣ ከሣልስ ፣ ከኃም ስ ፣ ምልክት ፣ በቀር ፣ ሌላ ፣ ቅጥል ፣ አይገባበትም ። በሦስተኛው ፣ እግሩ ፣ መቀጠልና ፣ ኃምሱ ን ፣ ጨ ፣ ማለት ፣ የተሳሳተ ፣ ነው I የቅጥሉ ፣ ገርሮ ፣ ወይም ፣ ቀለበት ፣ እንደ ፣ ጐጐኰቴ ፣ ግእ ዝ I ወይም ፣ እንደ ፣ ሎ ፣ ሳብዕ ፣ ቢያሰኘው ፣ እንጂ ፣ ኃምስ ፣ አያሰኘውም ። የኸም ፣ አጣ ጣፍ ፣ በጐንደሮች ፣ ዐዋጅ ፣ ከካዕብ ፣ እስከ ፣ ሳብዕ ፣ ኹ-ኺ—ኾ ፣ የሀ(ሐጎ) ቤት ፣ ነውና I ለከ ፣ ከግእዙ ፣ በቀር ፣ ምሉ ፣ ዐማርኛ ፣ የለውም ፣ ይባላል I ስሙንም ፣ ቀንዣ ፣ እንደ ፣ ግለት ፣ ድ ሆ ፣ (ኾ) ይሎታል ። ዐዋጁም ፣ ስሙም ፣ እምጎበ ፣ አልቦ ፣ የመጣና ፣ ባለማስተዋል ፣ የወጣ ፣ ነ ው I የጸሐፍቱ ፣ ልብ ፣ ያማርኛን ፣ ጠባይ ፣ መንገዱንና ፣ አካሄዱን ፣ መሣሪያ ፣ እንደሌለው ፣ እንደ ፣ ተርታ ፣ ሐኪም ፣ አጥብቆ ፣ አጥልቆ ፣ አልመረመረውም ። ማስረሻውን ፣ ዥዋላ ፣ በቦታ ው ፣ እናመጣዋለን ። ገጽ ፣ ፲፮ ።

(፲)

በዓኋኳቋ ፣ አንጻር ፣ ከግእዙም ፣ ከማርኛውም ፣ የሚገኙ ፣ አንዳንድ ፣ ዲቃሎች ፣ ፉብያች ፣ ብጮ ።

ከ ግ እ ዙ ።

ባ ዳ ዛ ጣ ላ ማ ና ፋ ጸፃ ራ ሰ ታ ።
ቧ ጁ ዟ ጧ ኋ ሻ ኗ ኟ ጷ ሯ ሷ ቷ ።

ከ ማ ር ኛ ው ።

ሻ ዣ ጣ ኻ ኛ ሻ ቻ ።
ሿ ዣ ጫ ኺ ኟ ሿ ቿ ።

(፱)

ያማርኛ ፣ ፊደል ፣ ከንዓዙ ።

«ዐማርኛ ፣ ማለት ፣ ያማራ ፣ ቋንቋ I ዐማራም ፣ ማለት ፣ (ዐም ፣ ሐራ) ነጻ ፣ ሕዝብ ፣ ጨ ዋ ፣ ሕዝብ I ነጻነት ፣ ያለው ፣ ባላባት ፣ ጥሩ ፣ የሰው ፣ ልጅ ፣ ማለት ፣ ነው ። ግዑዝ ፣ አግዓዚ ፣ ከ ማለት ፣ ጋራ ፣ ይሰማማል I ዐም ፣ የዕብራኒ ፣ የዖርያኒ I ሐራ ፣ የዅሉ ፣ ነው ። አንዳንድ ፣ ታሪክ ፣ ዐምሐራ ፣ ማለት ፣ ሕምያር ፣ ሖሜር ፣ ከማለት ፣ መጥቷል ፣ ይላል ። ሕምያር ፣ ከየመን ፣ ፈልሶ ፣ ወዳፍሪቃ ፣ መሬት ፣ የመጣ ፣ ሴማዊ ፣ ሕዝብ ፣ ነው I ሖሜርም ፣ የጡብና ፣ የሸክላ ፣ ዥቃ ፣ ን ው I የዅለቱም ፣ ፍች ፣ ቀይሕ ፣ ቀይሓዊ ፣ ማለት ፣ ነው I ጎምራዊ ፣ እንደ ፣ ማለት ። ሌላም ፣ አፈታት ፣ ይኖረዋል ። አማራ ፣ ተብሎ ፣ በአልፍ ፣ ሲጣፍ ፣ ግን ፣ ውብ ፣ ዕውቅ ፣ ዐዊቂ ፣ ባለአእ ምሮ ፣ ያሰኛል ። » ምሉ ፣ ዐማርኛ ፣ ያላቸው ፣ ፊደሎች ፣ ሰባት ፣ ብቻ ፣ ናቸው I ለቀሩት ፣ ፊደሎች ፣ ከራብዓቸው ፣ በቀር ፣ ያማርኛ ፣ ቅጥል ፣ የላቸውም ። ሰባት ፣ ያልናቸውም ፣ አስቀድመ ን ፣ በዅለተኛው ፣ ክፍል ፣ የጣፍናቸው ፣ ደዘጠ(ጸፀ)ከንስተ ፣ ናቸው ።

ሰ ባ ት ፣ ሰ ባ ቱ ።							ቀ ን ጃ ና ፣ ቀ ን ጁ ።				
ጅ	ጁ	ጂ	ጃ	ጄ	ጅ	ጆ	ጅ ፣	ጁጂ ፣	ጃጄ ፣	ጅጆ ፣
ዠ	ዡ	ዢ	ዣ	ዤ	ዥ	ዦ	ዠ ፣	ዡዢ ፣	ዣዤ ፣	ዥዦ ፣
ጨ	ጩ	ጪ	ጫ	ጬ	ጭ	ጮ	ጨ ፣	ጩጪ ፣	ጫጬ ፣	ጭጮ ፣
ኸ	ኹ	ኺ	ኻ	ኼ	ኽ	ኾ	ኸ ፣	ኹኺ ፣	ኻኼ ፣	ኽኾ ፣
ኘ	ኙ	ኚ	ኛ	ኜ	ኝ	ኞ	ኘ ፣	ኙኚ ፣	ኛኜ ፣	ኝኞ ፣
ሸ	ሹ	ሺ	ሻ	ሼ	ሽ	ሾ	ሸ ፣	ሹሺ ፣	ሻሼ ፣	ሽሾ ፣
ቸ	ቹ	ቺ	ቻ	ቼ	ች	ቾ	ቸ ፣	ቹቺ ፣	ቻቼ ፣	ችቾ ፣

ጨ ፣ የወጣ ፣ ከጠና ፣ ከጸ(ፀ) ፣ ነው I ከጠ ፣ ብቻ ፣ አይደለም I በግእዝ ፣ ጸ ፣ የሚባለው ፣ ባማርኛ ፣ ጠና ፣ ጨ ፣ ይኾናል ። (ማስረሻ) ጸመደ ፣ ጠመደ I ጸመ ፣ ጦመ I ጸልአ ፣ ጠላ ። ጸበ ጠ ፣ ጨበጠ I ጸልመ ፣ ጨለመ I ጸፈነ ፣ ጨፈነ ። ጸጉር ፣ ጠጉር I ጭገር I ጼው ፣ ጨው I ጸር ቅ ፣ ጨርቅ I የመሰለው ፣ ኹሉ ።

የሥና ፣ የሯ ፣ አጣጣፍ ።

ርያ ፣ ሪያ ፣ በማለት ፣ ፈንታ ፣ ሯ ፣ ወይም ፣ ሯ ፣ (መኾሯ ፣ ሯ ፤ መገሥመሯ ፣ ሯ) ማለት ፣ መልኩም ፣ ድምጡም ፣ የተሳሳተ ፣ ነው ፤ ለረ ፣ ከራብው ፣ በቀር ፣ ምሉ ፣ ያማርኛ ፣ ቅጥይ ፣ የለ ውም ፤ አለመኖሩም ፣ ከቢ ፣ እስከ ፣ ቷ ፣ ባሉት ፣ ባሥራንድ ፣ ውጓይሞቹ ፣ ይታወቃል ፤ ራብው ም ፣ ሯ ፣ በዝርዝር ፣ ሲጣፍ ፣ ሩዋ ፣ ያሰኛል ፣ አንጂ ፣ ርያ ፣ አያሰኝም ። ስላልተስመደ ፣ ነ ው ፣ እንጂ ፣ ሐና ፣ ሡዋ(ሷ) ፣ ጂና ፣ ሯ ፣ እንደነን ፣ ክግእዝ ፣ ቃላት ፣ ሊገቡ ፣ ይቻላል ። (ም ሳሌ) ፣ ተሓሻሐ ፣ አስተሓሻሐ ፤ ምሡዋ(ሷ)ዕ ፣ መሡዋ(ሷ)ዕት ፤ ምጂጽ ፣ ስጅጽ ፤ የመ ስለው ፣ ኹሉ ። ከቢ ፣ እስከ ፣ ቷ ፣ ያሉ ፣ ዐሥራ ፣ ኹለቱ ፣ ራብየኹ ፣ ፊደልንታቸው ፣ እንደ ፣ ጓጎ ኳቋ ፣ ለግእዝና ፣ ላግርኛ ፣ ለኹለቱም ፣ ሲኾን ፣ ክነዚኽ ፣ ክራቱ ፣ (ሯሡዋ(ሷ)ጂጅ) በቀር ፣ ለስ ምንቱ ፣ ግእዛዊ ፣ ቃል ፣ አይገኝምና ፤ ቢገኝም ፣ ጥቂት ፣ ስለ ፣ ኾነ ፣ ወዳግርኛ ፣ ተቈጥረዋል ።

ላግርኛ ፣ ቋንቋ ፣ ለፊደሉና ፣ ለቃሉ ፣ አባቱና ፣ እናቱ ፣ ሰፈዱ ፣ ወንፊቱ ፣ ግእዝ ፣ ስለ ፣ ኾ ነ ፣ ትምርቱ ፣ ብቻውን ፣ ሊነገር ፣ አይገባም ፤ ቢነገርም ፣ ጥፈቱና ፣ ቋንቋው ፣ አይጠራም ፤ ጸያ ፉ ፣ አይከተትም ፤ ትምርቱና ፣ ስልቱ ፣ ፍጹም ፣ አልጣ ፣ ይኾናል ።

ያማርኛም ፣ ሰልት ፣ እንደ ፣ ሕዝቡ ፣ አራት ፣ ክፍል ፣ ነው ፤ አንደኛው ፣ የቤተ ፣ ክህነት ፤ ኹለተኛው ፣ የቤተ ፣ መንግሥት ፤ ሦስተኛው ፣ የንጋዲ ፤ አራተኛው ፣ የባላገር ። የቤተ ፣ ክህነት ፣ ዐማርኛ ፣ በሰዋስው ፣ ተመሥርቶ ፣ ባገባብ ፣ የታነጠ ፣ በትርጓሜ ፣ የተቀረጠ ፣ በግእዝ ፣ አበባ ፣ የ ተጌጠ ፣ ነው ፤ ከግእዝ ፣ በቀር ፣ ሌላ ፣ ባእድ ፣ ቋንቋ ፣ አይገባበትም ። የቤተ ፣ መንግሥትም ፣ ዐ ማርኛ ፣ የግእዝ ፣ ትምርት ፣ ስላለበትና ፣ ሠራተኞቹ ፣ የክህናት ፣ ዉጣ ፣ ስለ ፣ ኾኑ ፣ እጅግ ፣ ስብ ቅል ፣ ነው ፤ ቃላትን ፣ ኹሉ ፣ እግዜር ፣ እንደ ፣ ማለት ፣ በማሳጠርና ፣ በማሳመር ፣ በማከናወን ፣ ይነገራል ። ዛሬ ፣ ግን ፣ አንዱን ፣ ስው ፣ ጌቶች ፣ በማለት ፣ ጸያፍ ፣ ግብጾበታል ፤ ያንቱታ ፣ ቃል ፣ ካንቱታ ፣ በቀር ፣ አካል ፣ አያበዛም ፤ ይኹም ፣ ጌታ ፣ በሉ ፣ ጠጡ ፤ ጌታ ፣ ሄዱ ፣ መጡ ፤ ማለቱ ን ፣ ጌቶች ፣ አለማሰኘቱን ፣ ያሳያል ። አንዱን ፣ ስውዬ ፣ ጌቶች ፣ ካሉት ፣ በዚኹ ፣ አንጻር ፣ ንጉሦ ች ፣ ራሶች ፣ ደኻዝማቾች ፣ ሊሎት ፣ ይገባል ። የንጋደኞችና ፣ የቀራፎች ፣ የመገዝገብ ፣ ጠፎች ፣ ዐማርኛ ፣ ግን ፣ እንደ ፣ ንፍሮና ፣ እንደ ፣ ልመና ፣ እኽል ፣ ቅይጥ ፣ ውጥንቅጥ ፣ ነው ፤ ሥራቸውና ፣ መማ ሪያቸው ፣ ከውጭ ፣ አገር ፣ ጋራ ፣ ስለ ፣ ኾነ ፣ በሽቀጡና ፣ በንግዱ ፣ ዕቃ ፣ መጠን ፣ በየጊዜው ፣ ሌ ላ ፣ ባዕድ ፣ ቋንቋ ፣ እየጨመረ ፤ ሳይቸግረውም ፣ እየተበደረ ፤ ያኑሎም ፣ እያዘናጉለ ፤ ብርውን ፣ ብ ዕር ፣ እያለ ፣ በድብልቅልቅነት ፣ ሲጣፍና ፣ ሲነገር ፣ ይኖራል ፤ ዛፌ ፣ እንደምናየው ፣ እንደምንሰ ማው ፣ ኹሉ ። የባላገሮች ፣ ዐማርኛ ፣ ሥረ ፣ ወጥ ፣ ነው ፤ ጥፈትና ፣ ትምርት ፣ ስላጣ ፣ መታደ ስ ፣ መለወጥ ፣ መሰብቀል ፣ መሻሻል ፣ የለውም ፤ በዚያው ፣ በዳሮው ፣ በጥንት ፣ ተፈጥሮው ፣ ይነ ገራል ። ዐማርኛ ፣ ምንም ፣ እንደ ፣ ገብስ ፣ ስሙና ፣ ጣዕሙ ፣ እንጂ ፣ ቢኾን ፣ የሕዝቡ ፣ ክፍል ፣ አራት ፣ ጸታ ፣ ስለ ፣ ኾነ ፣ እንዲኹ ፣ ባራት ፣ ስልት ፣ ይከፈላል ፤ ይኹም ፣ ያነኑ ፣ እንዱን ፣ ገብስ ፣ በሶ ፣ ጥረኖ ፣ ብቅል ፣ አሻሮ ፤ ወይም ፣ እንቀት ፣ ገንፎ ፣ ጥሕኒ ፣ ጥሕሎ ፣ እንደ ፣ ማለት ፣ ነው ። ይኽ ፣ አራቱ ፣ ይግሞ ፣ ታጥሮ ፣ ተደርቦ ፣ ከተምኖ ፣ ባላገርኛ ፣ ይባላል ፤ ይኽውም ፣ መልክም ፣ መናኛ ፣ እንደ ፣ ማለት ፣ ነው ።

እንዚኹም ፣ በሩቅ ፣ ሴት ፣ ዝርዝርና ፣ በስም ፣ በግብር ፣ በነገር ፣ ኹሉ ፣ ይገባሉ ።

«በዚኽ ፣ መጽሐፍ ፣ ውስጥ ፣ ላምስቱ ፣ ራብያች ፣ (ኛ ፣ ዣ ፣ ኻ ፣ ና ፣ ኛ) ዲቃላ ፣ ፊደል ፣ ስለ ፣ ታጣ ፤ ጁዋ ፣ ገዦዋ ፣ ኹዋ ፣ ኑዋ ፣ ኹዋ ፣ እያልን ፣ በዝርዝር ፣ ጥፈናቸዋል ። (ተረት) እን ዲያው ፣ ስትቀሪ ፤ ምንቸቱን ፣ አንቅሪ ። የጨነቀው ፣ ርጉዝ ፣ ያገባል »» ።

(ስ ም)		(ዝርዝር)		(ግብር)
ልብ ፤	—	ልቢ ፣	—	አስቢል ።
ሆድ ፤	—	ሆዲ ፣	—	ወዲል ።
ወዝ ፤	—	ወዚ ፣	—	ነተ·ብዚል ።
ወጥ ፤	—	ወጢ ፣	—	ጣፍጪል ።
ባል ፤	—	ባሏ ፣	—	ታድሏል ።
ስም ፤	—	ስሟ ፣	—	ተሰይሟል ።
ጎን ፤	—	ጎኑዋ ፣	—	ተጠግኑዋል ።
አፍ ፤	—	አፏ ፣	—	ለፍልፏል ።
ገጽ ፤	—	ገጿ ፣	—	ደንግጿ(ፃ)ል ።
ወር ፤	—	ወሯ ፣	—	ተዝምሯል ።
ራስ ፤	—	ራሷ ፣	—	ርሷል ።
ፊት ፤	—	ፊቷ ፣	—	በርቷል ።
ወዳጅ ፤	—	ወዳጁዋን ፣	—	ይዋጁዋል ።
አጋዥ ፤	—	አጋዡዋን ፣	—	ይቤዡዋል ።
አገጭ ፤	—	አገጪን ፣	—	ይገጪል ።
አኳኋን ፤	—	አኳኋኑዋ ፣	—	ት·ኳናም ።
አዳኝ ፤	—	አዳኙዋን ፣	—	ይዳኙዋል ።
ክሳሽ ፤	—	ክሳሿን ፣	—	ይሸሿል ።
ፀማች ፤	—	ፀማቿን ፣	—	ያስመቿል ።

(ማስረጃ) ዐማርኛና ፣ ትግሬ ፣ ትግሪኛ ፣ ክባታቸው ፣ ክግእዝ ፣ ጉያ ፣ ሳይወጡ ፣ ጀሸኸ ፣ በማለት ፣ ክዐረብና ፣ ክዕብራይስጥ ፤ ገሸኘች ፣ በማለት ፣ ክሮማይስጥና ፣ ክልጆቹ ፣ ይሰማማሉ ፤ ጨ ፣ በማለት ፣ ግን ፣ ክማንም ፣ ከማን ፣ የማይገጥሙ ፣ ብቸኞች ፣ ናቸው ። ሸን ፣ ከጥንታዊ ፣ ግእዝ ፣ ወርሰውታል ። ጀ ፣ የዐረቦች ፣ ገ ፣ ነው ፤ ያማርኛም ፣ ፊደል ፣ በጀ ፣ ምክንያት ፣ ዐረቢ ፣ ይባላል ፤ ዐረብ ፣ ገ ፣ ሲል ፣ ጂም ፣ ጀመል ፣ ይላል ። ባማርኛም ፣ ገና ፣ ጀ ፣ ይወራረሳሉ ፤ እንጌ (ጀ)ራ ፤ ግራ ፣ ነገረ ። ግ ፣ ጊ ፣ (ጅ ፣ ጂ)ራፍ ፤ ገረፈ ። አረገ(ጀ) ። ኘ ፣ የሚባለውም ፣ በዐረብ ፣ በጥንታዊው ፣ ግእዝ ፣ ጎርም ፣ ጎ ፣ ነው ፣ እንጂ ፣ ካፍ ፣ አይደለም ፤ ጌ(ኬ)ር ፣ በማለት ፣ ፈ ንታ ፣ እልኽይር ፣ እንዲል ፣ (ማር ፣ ይስሐ ፣ መቅድም) ። ክን ፣ ኘ ፣ ማለት ፣ የዕብራይስጥና ፣ ያ ማርኛ ፣ የትግሪኛም ፣ ነው ። የጎና ፣ የኘ ፣ ድምጥ ፣ ምንም ፣ አንድ ፣ ቢኾን ፣ ምስጢራቸው ፣ እ ንደ ፣ መልክቸው ፣ ልዩ ፣ ነው ፤ ከ ፣ በግእዝ ፣ ላራቱ ፣ ሰራዊት ፣ ለቅርቦች ፣ ብቻ ፣ ገርገር ፣ ም እላድ ፣ እንዲኾን ፣ ኘ ፣ ደግሞ ፣ ባማርኛ ፣ እንደዚኹ ፣ ነው ፤ ላንዲቱ ፣ ሴት ፣ ብቻ ፣ ኪ ፣ ተለው ጠ ፣ ሽ ፣ ይኾናል ። (ያቀከ ፣ ኪ ፣ ክሙ ፣ ክን) ዐወቀኘ ፣ ቀሽ ፣ ቃችኹ ። (አቡከ ፣ ኪ) አባትኘ ፣ ትሽ ። ባይዘረገርም ፣ የግእዙን ፣ አሠር ፣ ተክትሎ ፤ (ክልኤት ፤ ክዋላ ፤ ኮሎ ፤ እክል) ኹስት ፤ ኹ ዋላ ፤ ኹ—ኹሉ ፤ እኽል ። (ኮነ ፣ ይከውን ፣ ይኩን ፣ ክሮን ፣ ክዋኔ) ኘነ ፣ ይኾናል ፣ ይኹን ፣ መ ኾን ፣ አኳኋኑን ። (ገዝ ፣ ገዜ) ይኘ ፣ ይኘ ፣ እያሰኘ ፣ በዚያው ፣ በገንዘቡ ፣ በኘ ፣ ይጣፋል ። ኘ ን ፣ ለሀሐጎ ፣ ለሙጠ ፣ አባትህ ፣ አወቀህ ፤ ሆነ ፣ ሁነታ ፤ ሑለት ፣ ኋላ ፣ ሁሉ ፣ እህል ፣ ይህ ፣ እያ ሉ ፣ መጣፍ ፣ ልማድና ፣ ልብ ፣ ወለድ ፣ ነው ፣ እንጂ ፣ የቋንቋው ፣ መንገድ ፣ አይደለም ፤ ይኘ ፣ ብሎ ፣ ይህ ፤ ነበረ ፤ ደነባ ፤ ገነባ ፣ ብሎ ፣ ወምበር ፣ ደምብ ፣ ግምብ ፣ እምቢ ፣ አምባ ፣ ሳምባ ፣ ላምባ ፣ ግምባር ፣ ማለት ፣ ፍጹም ፣ ስሕተት ፣ ነው ፤ ነን ፣ በ ፣ ሲከተለው ፣ ወትሮ ፣ እንዲኘ ፣ ያ ላስታል ። ሌላ ፣ ፊደል ፣ ሲከተለው ፣ ግን ፤ ስንት ፣ አንድ ፣ አንተ ፣ ች ፣ ዐንገት ፣ አንደበት ፣ አን ጋፋ ፣ እያለ ፣ እንደ ፤ ፈረንሳዊ ፣ ኤን ፣ ሳይንክና ፣ ሳይጐረድ ፣ ጨርሶም ፣ ሳይዋጥ ፣ እያለ ፣ እንደ ሌለ ፣ ኹኖ ፣ ይነገራል ። አና ፣ ሀም ፣ ሲወራረሱ ፣ አልፍ ፣ አ ፣ ሆይ ፣ ሀኝ ፣ ብቻ ፤ ዐይን ፣ ዐ ፣ ሐውትንና ፣ ጎርምን ፣ ኹለቱን ፣ ይወርሳል ። ይኽም ፣ ሀለወ ፣ አለ ፤ ሆከ ፣ አወከ ፤ ሀገር ፣ አ ገር ። ሐከመ ፣ ሐገመ ፣ ዐከመ ፣ ዐገመ ፤ ሐረረ ፣ ዐረረ ። ጎብረ ፣ ዐበረ ፤ ጎደረ ፣ ዐደረ ፤ ጎጥአ ፣ ዐ ጣ ፤ እያለ ፣ ሌላውን ፣ ኹሉ ፣ ያሳያል ። የቋንቋና ፣ የጥፈት ፣ ትምርት ፣ ፍፈውና ፣ ጣዕሙ ፣ የፊደ ል ፣ አገባብ ፣ ማወቅ ፣ ነው ፤ አጣጣሉን ፣ ብቻ ፣ ማሳመርና ፣ ማከናወን ፣ አያስመሰግንም ። ባለሕ ጉን ፣ ቋንቋ ፣ ዘእንበለ ፣ ሕግ ፣ እየጣፋ ፣ ማንበብ ፣ ምንም ፣ ለጣፊው ፣ ሕጉ ፣ ቢኾን ፣ በሕግ ፣ ዐዋቆች ፣ ዘንድ ፣ መነቀፉና ፣ ማስነቀፉ ፣ አይቀርም ፤ በግድ ፣ ሕገ ፣ ወጥ ፣ ያስኛል ። የቋንቋችን ም ፣ ሕግ ፣ ሌማዊ ፣ እንደ ፣ ኘነ ፣ ዓለም ፣ ኹሉ ፣ ዐውቆታል ። ይኽነንም ፣ ቃል ፣ የውጭ ፣ አ ገር ፣ ቋንቋ ፣ ያዩ ፣ ሰዎች ፤ ይልቁንም ፣ ወጣቶችና ፣ ብር ፣ ነቀሎች ፣ ቶሎ ፣ ይረዱት ፣ ይመስለ ኛል ። ሸ ፣ የሚባለውም ፣ ንጉሡ ፣ ሠ ፣ እንጂ ፣ ሳቱ ፣ ስ ፣ አልነበረም ፤ ሠውት ፣ ሠና ፣ ሳ ት ፣ ስ ፣ በቦታና ፣ በድምጥ ፣ ተዛውረው ፣ ተፋልሰው ፣ አለቦታቸው ፣ ተጥፈዋል ። መፋለሳቸውም ፣

በዚኘ ፣ ይታወቃል ፤ ንጋሚ ፣ ንጋሽ ፤ ሚመት ፣ ሹመት ፤ ሦክ ፣ ሾኽ ፤ የመስለው ፣ ኹሉ ። በጽርእ ፣ ቋንቋ ፣ ሸ ፣ የሚሉ ፣ ፊደል ፣ ሸ ፣ የሚያሰኝ ፣ ቃል ፣ ስለሌለ ፤ አባ ፣ ሰላማ ፣ መጻሕፍትን ፣ ክጽር እ ፣ ወደ ፣ ግእዝ ፣ ሲመልስ ፣ ሸን ፣ ያን ፣ ጊዜ ፣ አውጥቶት ፣ ክዚያ ፣ ወዲኘ ፣ በግእዝ ፣ ቃላት ፣ ውስጥ ፣ መጣፉና ፣ መነገሩ ፣ ቀርቷል ። ብርቱ ፣ የነበረው ፣ የዐና ፣ የሐም ፣ ድምጥ ፣ የደከመና ፣ የሰለተ ፤ ጥንቃቄውና ፣ ልዩነቱ ፣ ቀርቶ ፣ እንደ ፣ አና ፣ እንደ ፣ ሀ ፣ የኘነ ፣ ክዚያ ፣ ወዲኘ ፣ ነው ፤ በትግሬና ፣ በትግሪኛ ፣ ግን ፣ እንደዚያው ፣ እንደ ፣ ጥንት ፣ ድምጡ ፣ ይነገራል ።

«ከትግሪኛ ፣ ይልቅ ፣ ትግሬ ፣ ጥሩ ፣ ቋንቋ ፣ ነው ፤ ለግእዝ ፣ በጣም ፣ ይቀርባል ። ሕዝቡ ፣ ብቻውን ፣ ነዋሪ ፣ ስለ ፣ ኘነ ፣ በውስጡ ፣ ክሌም ፣ ቋንቋ ፣ በቀር ፣ ሌላ ፣ ሞ ግሪ ፣ የለበትም ፤ ግ እዝን ፣ መደብ ፣ አድርጎ ፣ ክዐረብና ፣ ክዕብራይስጥ ፣ ክሱርስት ፣ ጋራ ፣ ይሰማማል ። በግእዝ ፣ መ ጻሕፍት ፣ የሌሉ ፣ ብዙ ፣ ቃላት ፣ ይገኙበታል ፤ ክማርኛም ፣ ጋራ ፣ የሚገጥም ፣ ብዙ ፣ ቃል ፣ አለበ ት ። ትግሪኛ ፣ ግን ፣ ባማርኛና ፣ በትግሬ ፣ መካከል ፣ የቆመ ፣ ማእከላዊ ፣ ነው ፤ ፊደሉም ፣ ክት ግሬና ፣ ከግእዝ ፣ ይልቅ ፣ ወዳማርኛ ፣ ያደላል ። የንባቡ ፣ መልክ ፣ ተኮሮና ፣ አጣጥሞ ፣ ሲያዩት ፣ ሲሰሙት ፣ የተበላሸ ፣ ግእዝና ፣ ያልተከናወነ ፣ ዐማርኛ ፣ መስሎ ፣ ይታያል ፤ ግእዝ ፣ የማያውቅ ፣ ዐማራ ፣ ጣዕሙን ፣ ሊቀምሰው ፣ አይችልም ፤ አንጋገሩ ፣ እጅግ ፣ ያስቸግራል» ።

ከካዕብ ፣ እስከ ፣ ሳብዕ ፣ ያሉ ፣ ቅጥሎች ፣ ምኖችና ፣ የምን ፣ ምሳሌዎች ፣ እንደ ፣ ኹኑ ፤ የ ግእዝና ፣ ያማርኛም ፣ ጠባይ ፣ ዐመሉ ፣ ዋየሉ ፣ እንዲት ፣ እንደ ፣ ኘነ ፣ በሠላሳኛው ፣ ክፍል ፣ በ ሦስተኛው ፣ ፊደል ፣ በመቅድሙ ፣ ውስጥ ፣ ተመልክት ።

(፲፩)

በበሠለስቱ ፡ ወበበአሐዱ ።

የሦስትና ፡ ያንድ ፡ ፊደል ፡ ንባብ ፤ አንደርሻ ፡ አካሄድ ።

አቡጊ ፡	ዳ ፡	ሄወዘ ።	ነሠሜ ፡	ፋ ፡	ጼቅሮ ።
በጉዲ ፡	ሃ ፡	ቄዝሐ ።	ሠዐፊ ፡	ጻ ፡	ቁርሶ ።
ገዱሂ ፡	ዋ ፡	ዜሕጠ ።	ዐፃጺ ፡	ቃ ፡	ሬስቶ ።
ደሁዊ ፡	ዘ ፡	ሔጥዮ ።	ፈጸቂ ፡	ራ ፡	ሴትኖ ።
ሀወዚ ፡	ሓ ፡	ጤይከ ።	ጸቂሪ ፡	ሳ ፡	ቴጎያ ።
ወዙሐ ፡	ጣ ፡	ዬክሰ ።	ቀሩሲ ፡	ታ ፡	ጎፅጰ ።
ዘሐጡ ፡	ያ ፡	ኬልሞ ።	ረሱቲ ፡	ኃ ፡	ፄጵፓ ።
ሐጠዩ ፡	ካ ፡	ሌምኖ ።	ሰቱኒ ፡	ፃ ፡	ጼፐአ ።
ጠዩኪ ፡	ላ ፡	ሜንሦ ።	ተኁሂ ፡	ጳ ፡	ፔእበ ።
የኩሊ ፡	ማ ፡	ኔሥያ ።	ጎፀጼ ፡	ፓ ፡	ኤጠጎ ።
ኩለሚ ፡	ና ፡	ሚዕፎ ።	ፀጼፒ ፡	አ ፡	ቤግዶ ።
ለሙኒ ፡	ሣ ፡	ሜፍጸ ።	ጰፑኢ ፡	በ ፡	ጌደሆ ።
መኑሚ ፡	ዓ ፡	ፈጾቆ ።	ፐኡቢ ፡	ጋ ፡	ዴሀዎ ።

ግእዝ ፡ ካዕብ ፤ ሣልስ ። ራብዕ ፤ ኃምስ ፤ ሳድስ ። ሳብዕ ፤ ሳምን ፤ ታስዕ ። ዓሥር ፤ ዓሥራዊ ፡ ዓሥራይ ፤ ዓሠረኛ ።

(፲፪)

ፍኖተ ፡ ፊደል ፡ ከልእ ፡ ኅዉሠ ፡ ዘርዕ ፡ ወቱሱሐ ፡ መልክእ ፡ በበስብዕ ፤ ዘያነቅሐሙ ፡ ለውሉድ ፡ እምንዋመ ፡ እበድ ፤ እስመ ፡ ስምዐ ፡ ለአቡጊዳ ፡ እሙን ፡ መጥበቤ ፡ ሕፃናት ፡ አብዳን ፤ በከመ ፡ ጽሑፍ ። ወሐረቱኒ ፡ ስያፍ ፡ አምሳለ ፡ ፍርዝ ፡ (ሠንጠረዥ) ።

ኹለተኛ ፡ የፊደል ፡ መንገድ ፡ በስያፍ ፡ አካሄድ ።

አ	ቡ	ጊ	ዳ	ሄ	ወ	ዘ		ነ	ሠ	ሜ	ፋ	ጼ	ቅ	ሮ
በ	ጉ	ዲ	ሃ	ቄ	ዝ	ሐ		ሠ	ዐ	ፊ	ጻ	ቁ	ር	ሶ
ገ	ዱ	ሂ	ዋ	ዜ	ሕ	ጠ		ዐ	ፋ	ጺ	ቃ	ሬ	ስ	ቶ
ደ	ሁ	ዊ	ዛ	ሔ	ጥ	ዮ		ፈ	ጼ	ቂ	ራ	ሴ	ት	ኖ
ሀ	ወ	ዚ	ሓ	ጤ	ይ	ከ		ጸ	ቁ	ሪ	ሳ	ቴ	ጎ	ያ
ወ	ዙ	ሐ	ጣ	ዬ	ክ	ለ		ቀ	ሩ	ሲ	ታ	ጎ	ፅ	ጰ
ዘ	ሐ	ጠ	ያ	ኬ	ል	ሞ		ረ	ሱ	ቲ	ኃ	ፄ	ጵ	ፓ
ሐ	ጠ	ዩ	ካ	ሌ	ም	ኖ		ሰ	ቱ	ኒ	ፃ	ጼ	ፕ	አ
ጠ	ዩ	ኪ	ላ	ሜ	ን	ሦ		ተ	ኁ	ኂ	ጳ	ፔ	እ	በ
የ	ኩ	ሊ	ማ	ኔ	ሥ	ያ		ኁ	ፀ	ጺ	ፓ	ኤ	ጠ	ጎ
ኩ	ሉ	ሚ	ና	ሚ	ዕ	ፎ		ፀ	ጼ	ፒ	አ	ቤ	ግ	ዶ
ለ	ሙ	ኒ	ሣ	ሜ	ፍ	ጸ		ጸ	ፑ	ኢ	በ	ጌ	ድ	ሆ
መ	ኑ	ሚ	ዓ	ፈ	ጾ	ቆ		ፐ	ኡ	ቢ	ጋ	ዴ	ሀ	ዎ

(፲፫)

ስመ ፡ ፊደል ፡ ወትርጓሜሁ ። = የፊደል ፡ ስም ፡ ከንትርጓሜው ።

አ ፡	አልፍ ፤	ቀንድ ፡ የቀንድ ፡ ከብት ፤ (አብ) ።
በ ፡	ቤት ፤	በቁሙ ፡ ቤት ፤ (ባዕል) ።
ገ ፡	ገምል ፡	ግመል ፤ ገመል ፤ (ግሩም) ።
ደ ፡	ድ(ን)ልት ፤	መገጢያ ፡ (ዘላለም) (ድልው) ።
ሀ ፡	ሆይ(ሀው፡ይ) ፤	ኑዋሪ ፡ ኹሞኝ ፡ (ህልው) ።
ወ ፡	ዋዌ(ዋው፡) ፤	ወገል ፡ ዘለበት ፤ (ዋሕድ) ።
ዘ ፡	ዛይ(ዛይን) ፤	ጌጥ ፡ ሽልማት ፤ (ገዝር) ።
ሐ ፡	ሐው፡(ይ)ት ፤	ሕያው ፤ ሕይወት ።
ጎ ፡	ጎርም ፤	ልዩ ፡ ብቸኛ ፤ ጎር ።
ጠ ፡	ጠይት ፤	ሠናይት ፤ ሥጋ ፤ (ጠቢብ) ።
የ ፡	የማን ፤	ቀኝ ፡ እጅ ።
ከ ፡	ካፍ ፤	ውስጥ ፡ እጅና ፡ እግር ፤ (ከሃሊ) ።
ለ ፡	ላዊ ፡ ላው፡ይ ፤	ጠማማ ፤ ጥምጥም ፤ (ልዑል) ።
መ ፡	ማይ ፡ ሜም ፤	ውሀ ፤ ፈሳሽ ፤ (ምዑዝ) ።
ነ ፡	ነሐስ ፡ ናስ ፤	ዝቦ ፡ እባብ ፤ (ንጉሥ) ።
ሠ ፡	ሠውት ፤	ሠዊት ፤ ሰብል ፤ (ሠዓሊ) ።
ዐ ፡	ዐይን ፤	በቁሙ ፤ ምንጭ ፤ (ዐቢይ) ።
ፈ ፡	ፈፍ ፡ (ፈ፡) ፤	አፍ ፤ አፋፍ ፤ ፈፋ ፤ (ፍቁር) ።
ጸ ፡	ጸደይ ፤	የዘር ፡ ወራት ፤ (ጻድቅ) ።
ፀ ፡	ፀጸ(ፀጻ) ፤	ፀሓያዊ ፤ (እሳታዊ) ።
ቀ ፡	ቆፍ ፤	ዝንጀሮ ፤ (ቅዱስ) ።
ረ ፡	ርእስ ፤	ራስ ፤ ርስ ፡ ቅል ።
ሰ ፡	ሳት ፡ (ሰዓት) ፤	ክረምት ፡ (በቁሙ) (ስቡሕ) ።
ተ ፡	ታው(ታዊ) ፤	ትእምርተ ፡ መስቀል ፤ (ትጉህ) ።
ጸ ፡	ጸይት ፡ (ጼት) ፤	በይት ፡ (ቤት) በ ።
ፐ ፡	ፒ ፡ (ፔ) ፤	ፊ ፡ (ፉ) ፈ ።

አበገደ ፤ ሀወዘሐ ፤ ጎጠየኸ ። ለመኔሠ ፡ ዐፈጸፀ ፤ ቀረሰተ ። ጸፐቶፐ ።

ጸፈቆሊጠስ ፤ ፓንዋማንጠስ (ፕሄፍማዶስ) ።

ያፅና ፡ ያጽ ፡ የጼ ፡ የጼ ፡ ፈደል ፡ ንባብ ።

በሥጋዊ ፡ ትርጓሜና ፡ አፈታት ፡ ዝሙም ፡ የፍጥረት ፡ ስሞች ፡ ናቸው ፤ በመን
ፈሳዊ ፡ አፈታት ፡ ግን ፡ የፈጠሪ ፡ ስሞች ፡ ወይም ፡ የስሙ ፡ ቅዋሎች ፡ ይኸናሉ ።

(፲፬)

ጉልቄ ፡ ፊደላት ፡ ወጸዋትዊሆን ፡ ምስለ ፡ ክፍላቲሆን ፡ እስከ ፡ ታው ፡ እምአልፍ ፡ ዘይትገሰስ ፡ ወዘይትለከፍ ፡ በጎምስቱ ፡ ሕዋሳት ፡ አፍ ፤ እስመ ፡ በ ፡ እምኔሆን ፡ ቀጣን ፡ ወገዛፍ ።

የፊደላት ፡ ዝሉ ፡ ቍጥራቸውና ፡ ስልታቸው ፡ ከንክፍላቸው ።

ሙላው ፡ የግእዝ ፡ ፊደላት ፡ በየራሳቸው ፡ ንጥሎ ፡ ተርትሮ ፡ በትኖ ፡ ዝርዝሮ ፡ ሲቈጥሯቸው ፡ (ከወ—ፀጸ) ኻያ ፡ ስድስት ፡ ዘር ፡ ይኾናሉ ፤ ጎን ፡ ከሐ ፡ ፀን ፡ ከጸ ፤ ጸን ፡ ከበ ፡ ፐን ፡ ከፈ ፡ ደርቦ ፡ በአሌፋት ፡ መንገድ ፡ በሥን ፡ ፍጥረት ፡ ፍቅድ ፡ ሲቈጥሯቸው ፡ ግን ፡ መደበኞቹና ፡ ዋነኞቹ ፡ ከአልፍ ፡ እስከ ፡ ታው ፡ (ከበ—ፀፀ) ኻያ ፡ ዝለት ፡ ብጾ ፡ ይኾናሉ ። «በሀ ፡ የሚነገር ፡ ሴማዊ ፡ ቃል ፡ እጅግ ፡ አለልክ ፡ ስለ ፡ በዛ ፡ የሀ ፡ ድምጥና ፡ መልክ ፡ ፫ ዐይነት ፡ ዝኖ ፡ ፪ቱ ፡ መደብ ፡ ይኖው ፡ ድርብ ፡ ይባላል ። ይኖ ፡ ጎ ፡ በግእዝ ፡ እንዳለ ፡ በዐረብም ፡ አለ ፤ በዕብራይስጥም ፡ የክፍ ፡ ድርብ ፡ ዝኖ ፡ ይነገራል ፤ ክፍ ፡ ነቍጣ ፡ ሲኾንበት ፡ ክ ፡ ሲቀርበት ፡ ኽ ፡ ይባላል ። ፐ ፡ ደግሞ ፡ እንደዚኹ ፡ ክፈ ፡ ተደርቦ ፡ ይነገራል ፤ ፪ኛ ፡ ፀም ፡ በዐረብና ፡ በዕብራይስጥ ፡ አለ» ። እሊኽም ፡ ኻያ ፡ ዝለቱ ፡ ፊደላት ፡ አራቱ ፡ ድርቦች ፡ (ጎዕጸፐ) ሳይቀሩ ፡ ከግእዝ ፡ ዘቸው ፡ እስከ ፡ ሳብዓቸው ፡ እንደ ፡ ክራር ፡ እንደ ፡ በገና ፡ አውታር ፡ ተሰድረው ፡ እየብቻቸው ፡ ተይዘው ፡ ሲንዘሩና ፡ ሲዎጹ ፡ ድምጥ ፡ የሚሰጡ ፡ ስለ ፡ ዝኑ ፤ የድምጣቸውን ፡ ስልት ፡ ልዩ ፡ ልዩንቱን ፡ ለማስታወቅ ፡ እንዳምስት ፡ ጣት ፡ ባምስት ፡ ጸታ ፡ ተከፍለው ፡ ባምስቱ ፡ ሕዋሳተ ፡ አፍ ፡ በጕረሮና ፡ በትናጋ ፡ በምላስና ፡ በከንፈር ፡ በጥርስ ፡ ይነገራሉ ።

ጸታቸውና ፡ ክፍላቸውም ፡ ከዚኽ ፡ ቀጥሎ ፡ እንደ ፡ ተጣፈው ፡ ነው ።

፩	በጕረሮ ፡	የሚነገሩ ፡	፭ ፤	— አ ፡ ዐ ፡ ሀ ፡ ሐ ፡ ኀ ።
፪	በትናጋ ፡	የሚነገሩ ፡	፬ ፤	— ገ ፡ የ ፡ ክ ፡ ቀ ።
፫	በምላስ ፡	የሚነገሩ ፡	፭ ፤	— ደ ፡ ጠ ፡ ስ ፡ ን ፡ ተ ።
፬	በከንፈር ፡	የሚነገሩ ፡	፮ ፤	— በ ፡ ወ ፡ መ ፡ ፈ ፡ ጸ ፡ ፐ ።
፭	በጥርስ ፡	የሚነገሩ ፡	፯ ፤	— ዘ ፡ ሠ ፡ ሰ ፡ ጸ ፡ ፀ ፡ ረ ።

(፲፭)

መቅድመ ፡ አኃዝ = የአኃዝ ፡ መቅድምና ፡ መግቢያ ።

ፊደላችንና ፡ የፊደል ፡ ቍጥራችን ፡ በሀለሐ ፡ አካሄድ ፡ ተፋልሶ ፡ ከላይ ፡ እስከ ፡ ታች ፡ መሳሳቱን ፡ ክጥቂት ፡ ሰዎች ፡ በቀር ፡ ዝሉ ፡ ሳያውቀው ፡ ይኖር ፡ ነበር ። የፊደሉም ፡ ቁጥር ፡ በዚ

ያው ፣ በስሕተቱ ፣ ከሀ ፣ እስከ ፣ ፐ ፣ ፷፪ ብቻ ፣ ነበረ ፤ ዛሬ ፣ ግን ፣ ባቡጊዳ ፣ አካሄድ ፣ ፫ ፊደላ ት ፣ ጐቄኤ ፣ ተጨምረውለት ፣ (ፀ) እልፍ ፣ መልቲል ፤ እስከ ፣ እልፍም ፣ በፊደል ፣ መቀጠር ፣ የጥንት ፣ ልማድ ፣ ነው ፣ እንጂ ፣ ያኹን ፣ ልብ ፣ ወለድ ፣ አይደለም ፤ የሱም ፣ ፊደል ፣ ኹሉ ፣ እ ንደዚኽ ፣ ነው ፤ በፊደል ፣ እስከ ፣ እልፍ ፣ ይቈጥራል ። ጐ ፣ ስለ ፣ ቀለበቱ ፣ የ፱፻ ፣ አኃዝ ፣ መ ኾኑ ፣ ጎርም ፣ ጎ ፣ የሐ ፣ ተወራጅ ፣ ነውና ፣ በተራ ፣ ቍጥር ፣ ዘጠንኛነት ፣ ስላለው ፣ ነው ። ቄም ፣ ስለ ፣ ቀለበቱ ፣ ያ፲፻ ፣ አኃዝ ፣ መባሉ ፤ ቆፍ ፣ ፻ ነውና ፤ የርሱን ፣ ያባቱን ፣ እሠር ፣ ተከትሎ ፣ ነ ው ። እ ፣ ደግሞ ፣ እልፍ ፣ መባሉ ፣ በራሱ ፣ ላይ ፣ ስለ ፣ ተቀዳኝት ፣ ስላንዲቱ ፣ ቅንጣት ፣ ነቍጣ ፣ ነው ፤ የአልፍ ፣ አ ፣ ጠባይ ፣ በዕብራይስጥም ፣ እንደዚኽ ፣ ነው ፤ ብቻውን ፣ አሐዱ ፣ ይባል ፣ የነ በረው ፣ በራሱ ፣ ላይ ፣ ነቍጣ ፣ ሲኾንበት ፣ አንድ ፣ እልፍ ፣ ይባላል ። ዕብራውያን ፣ ግን ፣ እልፍ ፣ የሚሉት ፣ እንዳረቦች ፣ ዐሥሩን ፣ መዶ ፣ ነው ፤ የግእዝም ፣ እልፍ ፣ ጥንታዊው ፣ እንደዚኽ ፤ ነበ ረ ፤ ይኸውም ፣ በአኃዙ ፣ አካሄድ ፣ ይታወቃል ፤ ፻ ብሎ ፣ ፻ ፣ በማስቱ ። ዐሥሩን ፣ መዶ ፣ ወይ ም ፣ አንዱን ፣ ሺሕ ፣ አምኣት ፣ ብሎ ፣ ዐሥሩን ፣ ሺሕ ፣ አንድ ፣ እልፍ ፣ ማለት ፤ ከጽርእና ፣ ከቅ ጥጥ ፣ የመጣ ፣ የሐዲስ ፣ ግእዝ ፣ ልማድ ፣ ነው ።

(፲፯)

ጐልቍ ፣ ወስመ ፣ ጐልቍ ፣ በአኃዝ ፣ ወበፊደል ።

ቍጥርና ፣ የቍጥር ፣ ስም ፣ በአኃዝና ፣ በፊደል ፣ ካንድ ፣ እስከ ፣ ምእልፊት ።

አ — ፩ ፤ አሐደ ፣ አሐዱ ። አንድ ፣ አንዱ ፤ አንደኛው ።

በ — ፪ ፤ ክልኤት ፣ ክልኤቱ ። ኹለት ፣ ኹለቱ ፤ ኹለተኛው ።

ገ — ፫ ፤ ሠለስት ፣ ቱ ። ሦ(ሠወ)ስት ፣ ቱ ፤ ሦስተኛው ።

ደ — ፬ ፤ አርባዕት ፣ ቱ ። አራት ፣ ቱ ፤ አራተኛው ።

ሀ — ፭ ፤ ኀምስት ፣ ቱ ። ዐምስት ፣ ቱ ፤ ዐምስተኛው ።

ወ — ፮ ፤ ስድስት ፣ ቱ ። በቁሙ ፤ ስድስተኛው ።

ዘ — ፯ ፤ ሰብዐት ፣ ቱ ። ሰባት ፣ ቱ ፤ ሰባተኛው ።

ሐ — ፰ ፤ ሰመንት ፣ ቱ ። ስምንት ፣ ቱ ፤ ስምንተኛው ።

ጠ — ፱ ፤ ተስዐት ፣ ቱ ። ዘጠኝ ፣ ኙ ፤ ዘጠነኛው ።

የ — ፲ ፤ ዐሠርት ፣ ቱ ። ዐሥር ፣ ሩ ፤ ዐሥረኛው ።

ከ — ፳ ፤ ዕሥራ ፣ (ሀ) ። ካያ = ኻያ ፤ ኹለት ፣ ዐሥር ።

ለ — ፴ ፤ ሠላሳ ፣ (ሀ) ። በቁሙ ፤ ሦስት ፣ ዐሥር ።

መ — ፵ ፤ አርብዓ ። አርባ ፤ አራት ፣ ዐሥር ።

ነ — ፶ ፤ ኀምሳ ። ዐምሳ ፤ ዐምስት ፣ ዐሥር ።

ሠ — ፷ ፤ ስሳ ፤ ስደሳ ። በቁሙ ፤ ፷፤ ። ወይም ፣ ሥልሳ ፤ ፫፸ ።

ዐ — ፸ ፤ ሰብዓ ። ስባ ፤ ሰባት ፣ ዐሥር ።

ፈ — ፹ ፤ ሰማንያ ። ሰማኒያ ፤ ስምንት ፣ ዐሥር ።

ጸ — ፺ ፤ ተስዓ ። ዘጠና ፤ ዘጠኝ ፣ ዐሥር ።

ቀ — ፻ ፤ ምእት ፣ (ቱ) ። መዶ ፤ ዐሥር ፣ ጊዜ ፣ ዐሥር ።

ረ — ፼ ፤ ክልኤ ፣ ቱ ፣ ምእት ። ኹለት ፣ መዶ ፤ ኻያ ፣ ጊዜ ፣ ዐሥር ።

ሰ — ፻፻ ፤ ሠለስቱ ፣ ምእት ። ሦስት ፣ መዶ ፤ ሠላሳ ፣ ጊዜ ፣ ዐሥር ።

ተ — ፼፻ ፤ አርባዕቱ ፣ ምእት ። አራት ፣ መዶ ፤ አርባ ፣ ጊዜ ፣ ዐሥር ።

ኀ — ፭፻ ፤ ኀምስቱ ፣ ምእት ። ዐምስት ፣ መዶ ፤ ዐምሳ ፣ ጊዜ ፣ ዐሥር ።

ፀ — ፮፻ ፤ ስድስቱ ፣ ምእት ። ስድስት ፣ መዶ ፤ ስሳ ፣ ጊዜ ፣ ዐሥር ።

ፐ — ፯፻ ፤ ሰብዐቱ ፣ ምእት ። ሰባት ፣ መዶ ፤ ሰባ ፣ ጊዜ ፣ ዐሥር ።

ኰ — ፰፻ ፤ ሰመንቱ ፣ ምእት ። ስምንት ፣ መዶ ፤ ስማኒያ ፣ ጊዜ ፣ ዐሥር ።

ጐ — ፱፻ ፤ ተስዐቱ ፣ ምእት ። ዘጠኝ ፣ መዶ ፤ ዘጠና ፣ ጊዜ ፣ ዐሥር ።

ቈ — ፲፻ ፤ ዐሠርቱ ፣ ምእት ። ዐሥር ፣ መዶ ፤ ፻ ጊዜ ፣ ዐሥር ፤ ፩ ሺሕ ።

እ — ፼ ፤ እልፍ ፤ ምእተ ፣ በበ፼ ። በቁሙ ፤ ፻ ጊዜ ፣ ፻ ፤ ዐሥር ፣ ሺሕ ።

የእ — ፲፼ ፤ አእላፍ ። ዐሥር ፣ እልፍ ፤ ወይም ፣ መዶ ፣ ሺሕ ።

ቀእ — ፻፼ ፤ አእላፋት ። ፻፼ ፤ ወይም ፣ ሺሕ ፣ ጊዜ ፣ ሺሕ ፤ (፩ ሚልዮን) ።

ቈእ — ፲፻፼ ፤ ትእልፊት ። ሺሕ ፣ ፼ ፤ ወይም ፣ እልፍ ፣ ጊዜ ፣ ሺሕ ፤ (፲ሚ) ።

እእ — ፼፼ ፤ ትእልፊታት ። ፼ጊዜ ፣ ፼ ፤ ወይም ፤ ፻፼ ፣ ጊዜ ፣ ሺሕ ፤ (፻ሚ) ።

ቈእእ — ፲፻፼፼ ፤ ምእልፊት ። ሺሕ ፣ እልፍ ፣ ጊዜ ፣ እልፍ ፤ (ሺሕ ፣ ሚ) ።

እእእ — ፼፼፼ ፤ ምእልፊታት ። እልፍ ፣ እልፍ ፣ ጊዜ ፣ እልፍ ፤ እልፉን ፣ እልፍ ፣ አንድ ፣ እያሉ ፣ እስከ ፣ እልፍ ፤ (፼ሚሊዮን) ።

(፲፯)

ሥርዐተ ፡ ነጥብ = የነጥብ ፡ አገባብ ።

ቃልን ፡ ከቃል ፡ በየጎርመቱና ፡ በየስልቱ ፡ ለያይተው ፡ ከፋፍለው ፡ የሚያሳዩ ፡ የጥፈትና ፡ የ ቃል ፡ ምልክቶች ፡ ፩ ናቸው ፤ ኹለቱ ፡ ስላንድ ፡ ይቁጠራሉ ። መልክቸውና ፡ ስማቸውም ፡ ከዚ ኽ ፡ ቀጥሎ ፡ እንደ ፡ ተጣፈው ፡ ነው ።

መልክቸው ።		ስማቸው ።
፡	—	ነቊጥ ፡ ወይም ፡ ነጥብ ።
፣ ፤	—	ንኡስ ፡ ሠረገ ፡ ወይም ፡ ነጠላ ።
፤	—	ዐቢይ ፡ ሠረገ ፡ ወይም ፡ ድርብ ።
።	—	ነጥብ ፡ ወይም ፡ ነቊጥ ።

አ ገ ባ ብ ቸ ው ።

ነቊጥ ፡ የቃል (፡) መለያ ፡ ነው ፤ በያንዳንዱ ፡ ቃል ፡ በጎርመት ፡ ኹሉ ፡ ይገባል ። የጥንቱ ፡ ነቊጥ ፡ እንደ ፡ ዜማ ፡ ይዘት ፡ አንድ ፡ ቅንጣት ፡ ብቻ ፡ (.) ነበረ ፡ ይባላል ፤ ፪ኛም ፡ ባንዱ ፡ ነ ቊጥ ፡ ፈንታ ፡ እንዳ፲ቱ ፡ ያለ ፡ (|) ዘንግ ፡ ነበረ ፤ ቮኛ ፡ ግን ፡ በዘንጉ ፡ ፈንታ ፡ ፪ ነቊጥ ፡ ኹ ኮዋል ። ነቊጥ ፡ የዐረቢ ፤ ነጥብ ፡ የግእዝ ፡ ቃል ፡ ነው ፤ ይኸውም ፡ አንዳንዱ ፡ ጠብታ ፡ ነው ፡ እንኚ ፡ ኹለቱና ፡ አራቱ ፡ አይደለም ። ሲበዛ ፡ ነቊጣት ፡ ነጥባት ፡ ወይም ፡ ነጠብጣብ ፡ ያሰኛል ና ፤ ኹለቱን ፡ አራቱን ፡ ነቊጥ ፡ ነጥብ ፡ ማለት ፡ በዚያው ፡ ባንዱ ፡ ነቊጣ ፡ በጥንታዊው ፡ ልማ ድ ፡ ነው ፡ እንኚ ፡ በለዋስው ፡ ሕግ ፡ አይደለም ። ባማርኛ ፡ ፪ ነጥብ ፡ ፬ ነጥብ ፡ ተብሎ ፡ ከቅጽ ል ፡ ጋራ ፡ ይነገራል ፤ ጣፎችና ፡ ባለመጣፎች ፡ ግን ፡ ነቊጥን ፡ ለኹለቱ ፡ ብቻ ፤ ነጥብን ፡ ላራ ቱ ፡ ብቻ ፡ ሰጥተው ፡ አለቅጽል ፡ ፪ቱን ፡ ነቊጥ ፤ ፬ቱን ፡ ነጥብ ፡ ብለው ፡ በተለየ ፡ ስም ፡ ው ስ ጠ ፡ ብዙ ፡ አድርገው ፡ ይጠሩታል ። ባለቅኔዎችም ፤ ቃልከ ፡ ነቊጥ ፡ እንዘ ፡ ክልኤቲ ፡ ልሳንከ ፡ አሐቲ ፡ ይእቲ ። ፍቅደ ፡ ነጥብ ፡ በዓላተ ፡ ወልድ ፡ ተሰዐቱ ፡ ውእቱ ፡ እያሉ ፡ በውስጠ ፡ ብዙነ ት ፡ ያገቡታል ። ነጥብን ፡ ፪ቱ ፡ ማለት ፡ ፭ ቀይ ፡ ሲጨመርበት ፡ ነው ። ነጠላ ፡ ሠረገ ፡ (፣፤) ጠባዩ ፡ አንድ ፡ ሲኾን ፡ መልኩ ፡ ፪ ነው ፤ ልዩ ፡ ልዩነት ፡ ባለው ፡ ባጣጭ ርና ፡ በማይ ጫፈር ፡ ቃል ፡ ይገባል ። አነ ፡ ዘጳውሎስ ፤ ወአነ ፡ ዘአጵሎስ ፤ ወአነ ፡ ዘኬፋ ፤ ወአነ ፡ ዘክርስቶ

ስ ። ነቢያት ፡ ቀደሙ ፡ አእምሮ ፤ ወሐዋርያት ፡ ተስዉ ፡ አሠሮ ። ሚካኤል ፡ አርመመ ፤ ወገብር ኤል ፡ ተደመ ። አው ፡ በጎልዮ ፤ አው ፡ በነቢብ ፤ አው ፡ በገቢር ፤ የመሰለው ፡ ኹሉ ። ድር ብ ፡ ሠረገ (፤) በፍጹም ፡ ቃል ፡ ማኽል ፡ እየራሱ ፡ በሚታስርና ፡ በሚነገር ፤ ባስረጅና ፡ ባፍራ ሽ ፡ ይገባል ። ወምድርሰ ፡ ኢታስተርኢ ፤ ወኢኮነት ፡ ድሉተ ፤ ወጽልመት ፡ መልዕልተ ፡ ቀላይ ፤ ወመንፈሰ ፡ እግዚ ፡ ይጸልል ፡ መልዕልተ ፡ ማይ ። ወይቤ ፡ እግዚ ፤ ለይኩን ፡ ብርሃን ፤ ወኮነ ፡ ብርሃን ። ንበር ፡ ማእከሌነ ፡ ወንግረነ ፤ እስመ ፡ ኪያከ ፡ አልሀቀ ፡ እግዚ ። ፈርሀ ፡ ወደንገፀ ፤ ባ ሕቱ ፡ ኢጉየ ፡ ወኢገገጸ ። ነጥብ ፡ (።) ንኡስ ፡ ምዕራፍ ፡ ነው ፤ አንባቢን ፡ አንደ ፡ ልጓም ፡ ኹኖ ፡ ይገታል ፤ አንዱ ፡ ፍጹም ፡ ቃል ፡ ዐጭር ም ፡ ረኽምም ፡ ቢኽን ፡ ተሳቢው ፡ ተከቶ ፡ ነገ ሩ ፡ ሲጨረስ ፡ እንደ ፡ ጐልላት ፡ በጣፍ ፡ በመጨረሻ ፡ ይገባል ። ረኽም ፡ ቃል ፡ ወምድርሰ ፡ እንዳልነው ፡ ያለ ፡ ነው ፤ ዐጭር ፡ ቃል ፡ በቀዳሚ ፡ ገብረ ፡ እግዚ ፡ ሰማያተ ፡ ወምድረ ። የመሰለ ው ፡ ኹሉ ። ያማርኛውም ፡ እንደ ፡ ግእዙ ፡ ነው ፤ ለብቻው ፡ የተለየ ፡ ዐዋጅ ፡ የለውም ። በትግ ሪኛም ፡ ወንጌል ፡ ሠረዘች ፡ እንደሚገባቸው ፡ ተጥፈዋል ፤ አልተሳሳቱም ።

በነዚኽ ፡ ባ፩ቱ ፡ ላይ ፡ ደግሞ ፡ ሌላ ፡ ዐይነት ፡ ምልክት ፡ ከኤውሮፖች ፡ መጣፍ ፡ ማም ጣትና ፡ መጨመር ፡ ያሻናል ። ስለሚያሹንም ፡ ምልክቶች ፡ ባ፲፬፻፺፱ ፡ ዓመት ፡ የታተመ ፡ የከረ ን ፡ ስዋስው ፡ በመጨረሻው ፡ ገጽ ፡ እንዲኽ ፡ ይላል ። ((ወስኮ ፡ ጥበብ ። ኤሮፓውያን ፡ በመ ጣፎቻቸው ፡ የሚያደርጓቸው ፡ ምልክቶች ፡ የተጣፈውን ፡ የመጣፉን ፡ ምስጢር ፡ አስችግር ፡ በ ገር ፡ ያሳውቃሉና ፤ በሌላ ፡ መጣበብ ፡ ትተን ፡ እንሱኑ ፡ በጥፈታችን ፡ ውስጥ ፡ እንዳሉ ፡ ማግባ ት ፡ እጅግ ፡ የሚያሻና ፡ የሚያስፈልግ ፡ ነው ።

ም ል ክ ቶ ቹ ም ፡ እ ኒ ኽ ፡ ና ቸ ው ።

ትእምርተ ፡ ደጊመ ፡	ቃለ ፡	»	
ትእምርተ ፡	ቃለ ፡	ሐተታ ፡	?
»	»	አንክሮ ፡	! በዘየንብሩ ፡ ክልኤሆሙ ፡ ?!
»	»	ሥላቅ ፡	!

አንባቢ ፡ በገር ፡ ያውቀዋል ፡ ተብሎ ፡ ሊጻፍ ፡ በማያሻ ፡ ነገር ፡ የሚደረግ ፡ ምልክት ፡ ይኽ ፡ . . . ነው ።

ከተነገሩቱ ፡ ፍጹማን ፡ ቃላት ፡ ባሳሳብ ፡ የማይተላበር ፡ ፍጹም ፡ ቃልን ፡ ከቃል ፡ የሚለይ ፡ ምልክት ፡ ይኽ ፡ ( ) ነው ።

ያንዱን ፡ ደራሽ ፡ ጥቅስ ፡ ወይም ፡ ስሯጽ ፡ ቃልን ፡ ለመለየት ፡ ከመገሥመርያው ፡ እስክ ፡ መጨረሻው ፡ የሚደረግ ፡ የስሯጽ ፡ ምልክት ፡ ይኽ ፡ « » ነው)) ።

ትእምርተ ፡ ቃለ ፡ ሐተታ ፡ ከለው ፡ በቀርፋ ኹሉም ፡ በግድ ፡ የሚፈለጉ ፡ ናቸው ፤ የጥያቄ ው ፡ ቃል ፡ ምልክት ፡ ግን ፡ ሳይኾንፉ ፡ እንደ ፡ መበደር ፡ ነው ፤ ለግእዙም ፡ ላማርኛውም ፡ የታ

ወቅና ፣ የተለየ ፣ የጥያቄ ፣ አገባብ ፣ (ሁ—ኑ ። ን —ወይ) አላቸውና ፤ ጥፈታቸውና ፣ ንባባቸው ፣ ሌላ ፣ ምልክት ፣ ሳይሻ ፣ ያው ፣ ይበቃው ፣ ነበር ። ነገር ፣ ግን ፣ ባማርኛ ፣ ያልሠለጠኑ ፣ ያማርኛው ን ፣ አገባብ ፣ በጥፈትና ፣ ባነጋገር ፣ ብዙ ፣ ጊዜ ፣ ይተዉታልና ፤ አንባቢና ፣ ጣፊ ፣ ለይቶ ፣ እንዲያ ውቀው ፣ ላማርኛው ፣ ብቻ ፣ ቢገባ ፣ አይከፋም ። የአንክሮና ፣ የሥላቅ ፣ ምልክት ፣ ከኦና ፣ ከሆ ይ ፣ ከኹለቱ ፣ ጋራ ፣ ሊጣፍ ፣ ይገባዋል ። ነጠብጣብ ፣ ስለ ፣ ቀሪው ፣ ፊደል ፣ ነውና ፤ ቍጥሩ ፣ በዚያው ፣ በቀሪው ፣ ልክ ፣ ይገባል ። ጎግ ፣ ማ . . ። ዳዊት ፣ መዝሙረ ፣ . . . ። አምላክ ፣ ወል ደ ፣ . . . . ፣ እንደ ፣ ማለት ። ይኸም ፣ ኹለቱ ፣ ዐይነት ፣ ቀርናዊ ፣ ( ) « » ምልክት ፣ ነጠብጣ ብም ፣ . . . ሳይቀር ፣ እየተረሳ ፣ ቀርቶ ፣ እንጂ ፣ በዱሮ ፣ መጻሕፍት ፣ ይገኛል ፤ ሌላም ፣ ብዙ ፣ ምልክት ፣ ቀርቶብናል ፤ ይልቁንም ፣ በወንጌል ፣ አጣጣፍ ። ዳግመኛም ፣ የተጣፈውን ፣ ቃል ፣ መ ልሶ ፣ በመጣፍ ፣ ፈንታ ፣ የሚደረግ ፣ ይኸ ፣ — ነው ። ሥጋ ፣ ስብእ ፤ — ፣ አምላክ ፤ — ፣ሳሕም ። ፪ ሺኽን ፣ እንደ ፣ ሒላሊት ፣ በኽነ ፣ በ፪ ፣ ቃል ፣ ማኽል ፣ እየገባ ፣ ትክክልነትን ፣ ያሳያል ። ስም ጽ=ለምጥ ፤ ቡሖ=ሊጥ ፤ የመስለው ፣ ኹሉ ። የሚጠብቀውም ፣ ቃል ፣ እንደ ፣ ዜማ ፣ ይዘት ፣ አንዳንዲት ፣ ነቍጣ ፣ ይፈልጋል ፤ ነደ ፣ ነድ ፤ ቄረ ፣ ቍር ፤ ተን ፣ ተን ።

በዘመናችን ፣ ግን ፣ ስንኳን ፣ ሌላ ፣ ዐይነት ፣ ሊጨመር ፣ ያው ፣ ክጥንት ፣ የቄየው ፣ ፊደል ና ፣ ንባብ ፤ የጥፈቱ ፣ ሥርዐት ፤ የፊደሉ ፣ አገባብ ፣ እንደ ፣ ጥንቱ ፣ አልተጠበቀም ፤ አልተጠነቀ ቀም ። ጥፈቱም ፣ አለመምርና ፣ አለትምርት ፣ በመላ ፣ በግምት ፣ በልማድ ፣ በድፍረት ፣ ስለ ፣ ኽ ን ፤ ሥርዐቱ ፣ ኹሉ ፣ ፊደሉም ፣ ሳይቀር ፣ መጕደልና ፣ ማነስ ፤ መናድና ፣ መፍረስ ፤ መጥፋት ፣ መበላሸት ፣ ገሥጮል ። በወዲያኛው ፣ ባስመራ ፣ ማኅተም ፣ በስዊድን ፣ ማኅበር ፣ ከትግሬና ፣ ከትግሪኛ ፣ መጽሐፍ ፣ ሦስቱ ፣ ፊደላት ፣ (ሠ ፣ ኀ ፣ ዐ) እንደ ፣ ወጡ ፤ በወዲኽም ፣ ከማርኛው ፣ መጽሐ ፍ ፣ በኒኽ ፣ በሦስቱ ፣ ላይ ፣ ኹለት ፣ ፊደላት ፣ (ዐ ፣ ሐ) ተጨምረው ፣ ፭ቱ ፣ እንዲወጡ ፣ በብ ዙ ፣ ሰዎች ፣ ልብ ፣ ሐሳብና ፣ ምኞት ፣ ተንሥዶ ፣ እንደ ፣ ደጀ ፣ ጠኒ ፣ ይኮላላል ፤ አንዳንድ ፣ ጊ ዜም ፣ እየፈላና ፣ እየገነፈለ ፣ በግልጥ ፣ ይነገራል ፤ ሥራውንም ፣ እንኳ ፣ የዠመሩት ፣ ሰዎች ፣ ይ ኖራሉ ፤ ወሰው ፣ ያለላቸው ፣ የሰም ፣ እንጂ ።

የግእዙም ፣ መጽሐፍ ፣ ከነትርጓሜው ፤ ግእዝ ፣ የሌለውም ፣ ያማርኛው ፣ መጽሐፍ ፣ አለን ቍጥና ፣ አለመረገ ፣ ስድ ፣ እየታተመ ፣ መልኩ ፣ ጠፍቶ ፤ ደፍራችኹና ፣ ተሸራችኹ ፣ አትዩኝ ፣ አታንቡኝ ፣ ይላል ። አንዳንድ ፣ ሰዎች ፣ ግን ፣ ዐዲስ ፣ ሥልጣኔ ፣ ይሉታል ። (በዚኽ ፣ መጽሐፍ ፣ ውስጥ ፣ ንኡስ ፣ መረዘች ፣ ስለ ፣ ታጡ ፣ በርሳቸው ፣ ፈንታ ፣ ድርብ ፣ መረዝ ፣ ገብቷል) ።

(፲፫)

ግጥም ፣ ተማሪና ፣ መምር ፣ ስለ ፣ ፊደላት ፣ ስምና ፣ ግብር ።

ተ ማ ሪ ።

ልጆች ፣ የምስራች ፣ ደስ ፣ ይበላችኹ ፣
እንደ ፣ መልአክ ፣ ኹኜ ፣ በማበሥራችኹ ፤
የማበሥራችኹም ፣ ኹለት ፣ ፍሬ ፣ ቃል ፣
መዐዛው ፣ የኦሪት ፣ ጣዕሙ ፣ የወንጌል ።

ባማርኛ ፣ ይበተር ፣ በግእዝ ፣ መዝገብ ፣
ተጥፎ ፣ እንዳይታይ ፣ እንዳይነበብ ፤
ተደብቆ ፣ ሲኖር ፣ የፊደላት ፣ ወሬ ፣
ከስማቸው ፣ ጋራ ፣ ተገለጠ ፣ ዛሬ ፤
ቄሩሮ ፣ ባወጣው ፣ የትምርት ፣ ወዳጅ ፣
በመዝገበ ፣ ፊደል ፣ ኹሉም ፣ ተገኝ ፣ እንጅ ።

ዐማራና ፣ ትግሬ ፣ የግእዝ ፣ ልጆች ፣
እግዜር ፣ ያነጣችኹ ፣ የቀለም ፣ ቀንዶች ፤
ከመዝገበ ፣ ፊደል ፣ ጥበብ ፣ እንድትዘግቡ ፣
ወዳቡጊዳ ፣ ቤት ፣ ግቡ ፣ ተሰብሰቡ ።

ባቡጊዳችንም ፣ እንዳያሽሞጥጥ ፣
ሀለሐመን ፣ ተዉት ወዲያ ፣ ይቀመጥ ።
በቀኖር ፣ በተራ ፣ በኹለት ፣ ባህል ፣
ልዩ ፣ ስለ ፣ ኽነ ፣ ከሳለም ፣ ፊደል ፤
የግእዝ ፣ ሊቃውንት ፣ ጉባኤ ፣ አድርገው ፣
ምንም ፣ ባያወግዙት ፣ እንደ ፣ ውጉዝ ፣ ነው ።

ስንሻው ፣ የነበር ፣ ስንመኘው ፣ ቀድሞ ፣
በግእዝ ፣ ቋንቋችን ፣ ተጥፎ ፣ ታትሞ ፤
ወፈያቸው ፣ ስማቸው ፣ ከተገለጠማ ፣
ኑ ፣ እናወድሳቸው ፣ በቅኔ ፣ በዜማ ።

ቅኔውም ፣ ዜማውም ፣ የዱሮ ፣ ግእዝ ፣
ከበሮዉም ፣ እኛ ፣ መዝሙሩም ፣ ሐዋዝ ።

እንደ ፣ ኤርምያስም ፣ ሳንንሰቀሰቅ ፣
እንዳዜ ፣ ዳዊትም ፣ እንብ ፣ ሳናፈልቅ ።

አንዱንም ፣ አንዱንም ፣ በስሙ ፣ ጠርተን ፣
የአሌፋት ፣ መዝሙር ፣ እንዘምራለን ።

አልፍ ፣ ቤት ፣ ገምል ፣ ድልት ፣ ሆይ ፣
ዋዊ ፣ ዛይ ፣ ሐውት ፣
አዕማደ ፣ ምስጢር ፣ የምትባሉት ፤
በናንተ ፣ ላይ ፣ ቁመን ፣ ስናዋቅር ፣ ጣራ ፣
እንዳንወድቅባችኹ ፣ ደግፉን ፣ አደራ ።

ጎርምና ፣ ጠይት ፣ የማን ፣ ካፍ ፣ ላውይ ፣
ማይ ፣ ሚም ፣
ንሐስ ፣ ሠውት ፣ ዐይን ፣ ፈፍ ፣ ጸደይ ፣ ዐጸ ፣ ፀም ፤
አርድእት ፣ ለማድረግ ፣ ሕዝብ ፣ አሕዛቡን ፣
እንደ ፣ ሐዋርያት ፣ አሳችኹ ፣ ሥልጣን ።

ቆፍና ፣ ርእስ ፣ ሳት ፣ ታው ፣ መጠረሻው ፣
ጸና ፣ ጥም ፣ ኹለቱ ፣ ከታው ፣ ጋራ ፣ ዐብረው ፤
ከአልፍ ፣ እስከ ፣ ጸፐ ፣ ኻያ ፣ ስድስታችኹ ፣
በልባችን ፣ ሸንጎ ፣ ጉባኤ ፣ አድርጋችኹ ፤
እንድትወስኑልን ፣ ግእዝ ፣ ክማርኛ ፣
አማጥነናችኹዋል ፣ በትምርት ፣ ዳኛ ።
የትምርቱም ፣ ዳኛ ፣ አቅንቶ ፣ ፈራጅ ፣
ጎይስ ፣ ሥላሴ ፣ ነው ፣ የሰሎሞን ፣ ልጅ ።

ልጆቻችኹንም ፣ ስንቂጥራቸው ፣
እንደ ፣ አዳም ፣ ልጆች ፣ ሠላሳ ፣ ኖቸው ፤
ሰባቱ ፣ ዐማርኛ ፣ አራቱ ፣ ግእዝ ፣
ዐሥራ ፣ ዘጠኙ ፣ ግን ፣ ያማርኛ ፣ ጓዝ ።

መዝሙሩ ፣ ይቄየን ፣ እንስማ ፣ ስብክት ፣
የሚሰበክውን ፣ ስለ ፣ ፊደላት ፤
የፊደልን ፣ ትውልድ ፣ ታሪክና ፣ ዜና ፣
ሊሰብክ ፣ ሊያስተምር ፣ መምህር ፣ ቁሟልና ።

መ ም ር ።

አጽምዑ ፡ ሕፃናት ፡ ሕዝብየ ፡ ሕገ ፡ ስብከትየ ፤ ወጽልዉ ፡ እዝንክሙ ፡ ኅበ ፡ ቃለ ፡ አፉየ ፤ እስመ ፡ ናሁ ፡ እከሥት ፡ ለክሙ ፡ በምሳሌ ፡ አፉየ ፤ ወእነግር ፡ ኵሎ ፡ አምሳለ ፡ ዘእምትካት ፡ በእንተ ፡ አሌፋት ፡ ወፈደላት ።

የተላከ ፡ ክግስ ፡ ክመገገበ ፡ ቃል ፡ ትርጓሜና ፡ አፈታት ፡ ሐተታ ፡ ፊደል ፤ ይድረስ ፡ ክወዳጂ ፡ ክሕፃናት ፡ ልብ ፡ ክግእዝ ፡ ስራዊት ፡ ካግርኛ ፡ ሕገብ ፤ ከናቴም ፡ ከጠቢያው ፡ ካፍሪቃ ፡ ባላልጋ ፡ እጀቷን ፡ ወደግዜር ፡ ክምትዘረጋ ።

ስላምታ ፡ አቀርባለኹ ፡ ለፊደል ፡ ጸሐፍት ፡ ላታሞችም ፡ ሳይቀር ፡ እጅ ፡ በመንግት ።

እጅ ፡ መንሻዬም ፡ የግር ፡ ወስላ ፡ ፊደል ፡ መስፈሪያው ፡ ዕብራይስጥ ፡ ጉንደ ፡ የሚባል ።

ያቡጊዳን ፡ ሥራ ፡ የምታግርሩ ፡ እንዲጣፍጣችኹ ፡ ቅመሱ ፡ ተማሩ ።

ስለ ፡ ተጠማችኹ ፡ የፊደልን ፡ ዜና ፡ ክሥሩ ፡ ከምንጩ ፡ ላመጣው ፡ ነውና ፤ ምናልባት ፡ ስትቀምሱት ፡ ስታጣጥሙት ፡ ጠላ ፡ ነው ፡ ብላችኹ ፡ ስም ፡ እንዳትሰጡት ።

ጥሩውን ፡ ቃል ፡ ውሀ ፡ ጠላ ፡ ነው ፡ ብትሉ ፡ ይታዘባችኹዋል ፡ የሚቀምሰው ፡ ኹሉ ።

የስብክት ፡ መፀዛ ፡ የሰባኪው ፡ ጣዕም ፡ ለይቶ ፡ ማስታወቅ ፡ ክፉና ፡ መልካም ።

በልበ ፡ ሕፃናት ፡ በአፈ ፡ ደቂቅ ፡ ፊደል ፡ ሥር ፡ እንዲሰድ ፡ ታሪኩ ፡ እንዲጸድቅ ፤ ልጆች ፡ እየጠቀስኮ ፡ ከምድር ፡ ክሰማይ ፡ እስኪ ፡ ልናገረው ፡ የልጅን ፡ ጠባይ ።

ያባትንም ፡ ሥራ ፡ በልጆቹ ፡ ላይ ፡ እንዲት ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ገልጬ ፡ ላሳይ ።

ሰውና ፡ መላእክት ፡ ያንድ ፡ አባት ፡ ልጆች ፡ ታናሽና ፡ ታላቅ ፡ ወንድማማቾች ፤ ታላቁ ፡ ሽፍቶ ፡ ካባቱ ፡ ቢዋጋ ፡ ብኵርናው ፡ ተሰጠ ፡ ለታናሹ ፡ ሥጋ ።

ታናሹም ፡ ቢሸፍት ፡ አልሄደም ፡ ብኵርና ፤ ቃል ፡ ወረሰው ፡ እንጂ ፡ በሕገ ፡ ስብእና ።

ለሰው ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፡ የቃል ፡ በኵርነቱ ፤ ለመላእክትም ፡ ነው ፡ በሰማይ ፡ ላሉቱ ።

በዲያብሎስ ፡ ቦታ ፡ ስለ ፡ ገባ ፡ አዳም ፡ ወሊድ ፡ ነው ፡ በኵራቸው ፡ ለመላእክትም ።

ዲያብሎስ ፡ ቢገፋው ፡ ወድቆ ፡ ክመሬት ፡ ተበላሽቶ ፡ ነበር ፡ ይኸ ፡ በኵርነት ፤ ክሥግው ፡ ቃል ፡ በቀር ፡ ለርሱ ፡ የሚመች ፡ አልተገኝምና ፡ ክላይም ፡ ክታች ።

የሰው ፡ ልጅ ፡ እስኪባል ፡ በኹዋላ ፡ ዘመን ፡ ስሙ ፡ እንጂ ፡ መልአክ ፡ ነው ፡ በብሉይ ፡ ኪዳን ፤ ትንቢትና ፡ ራእይ ፡ ለአበው ፡ ሲሰብክ ፡ አርኣያው ፡ የመልአክ ፡ ቃሉ ፡ የአምላክ ፤ ክሔናክ ፡ ገሥሮ ፡ ነቢያት ፡ ይጠሩ ፤ የርሱን ፡ መልአክነት ፡ እንዲመሰክሩ ።

በሃይማኖት ፡ ገመድ ፡ በልጅነት ፡ ሐብል ፡ እንደ ፡ ክንዓን ፡ ሕዝብ ፡ እንደ ፡ እስራኤል ፡ መንግሥተ ፡ ሰማይን ፡ ዐብረው ፡ ለሚወርሱ ፡ ለሰው ፡ ለመላእክት ፡ በኵር ፡ የለም ፡ አሰርሱ ።

በእሳት ፡ ጉባኤ ፡ በመሬት ፡ ማኅበር ፡ ለክህናተ ፡ ሰማይ ፡ ለክህናተ ፡ ምድር ፡ የፊደል ፡ የጥፊት ፡ የቋንቋ ፡ መምር ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ እግዚአብሔር ።

ፊት ፡ በብሉይ ፡ ኪዳን ፡ ኹዋላም ፡ በሐዲስ ፡ አፍ ፡ እያስከፈተ ፡ መጣፍ ፡ የሚያጉርስ ፤

እውንተኛው ፡ መምር ፡ የትምርቱ ፡ አባት ፡ እንድ ፡ እግዜር ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ በላይ ፡ በታች ፡ ቤት ።

እግዜር ፡ መምር ፡ ኹኖ ፡ ያዳምን ፡ ዘር ፡ ኹሉ ፡ በመንፈሱ ፡ ሲቃኝ ፡ ሲያስተምር ፡ በቃሉ ፤ ያቆመለትን ፡ ሕግ ፡ በተፈጥሮ ፡ ዕውቀት ፡ ፈታዊ ፡ ልቡናው ፡ ቢዘነጋበት ፤ ፊደልን ፡ ጥፈትን ፡ ባርኮ ፡ የሰጠው ፡ በሦስተኛው ፡ ትውልድ ፡ በሄኖስ ፡ ጣት ፡ ነው ።

ይኸነንም ፡ ታሪክ ፡ እንዳንለው ፡ አሌ ፡ እንሆ ፡ ምስክር ፡ መጽሐፈ ኩፋሌ ፤ ሔኖክም ፡ ይነግራል ፡ ገልጦ ፡ እያሳመረ ፤ ፊደል ፡ ክርሱ ፡ በፊት ፡ ቀድሞ ፡ እንደ ፡ ነበረ ።

ኹዋላም ፡ ባለቤቱ ፡ ደብረ ፡ ሲና ፡ ወርዶ ፡ ሃይማኖት ፡ ለማሞቅ ፡ እሳቱን ፡ እንድዶ ፤ ጽላትና ፡ ታቦት ፡ ቀርጠ ፡ እያስቀረጠ ፡ ወሠርቱ ፡ ቃላትን ፡ በጺ ፡ ጥፎ ፡ ሰጠ ።

ለባለጀ ፡ ሙሴም ፡ ሲሰጠው ፡ እጅ ፡ በጅ ፡ ስማ ፡ ስማ ፡ ብሎ ፡ አስነገረ ፡ ወዋጅ ።

በቃሉ ፡ ንጉድጓድ ፡ በመንፈሱ ፡ ድምጥ ፡ ዓለም ፡ ኹሉ ፡ እስኪርድ ፡ እስኪንቀጠቀጥ ።

የሙሴ ፡ እጆችና ፡ የጆቹ ፡ ጣቶች ፡ የጽላት ፡ የቃላት ፡ አምሳል ፡ መርገፎች ።

ሙሴ ፡ ፵ ቀን ፡ ምሉ ፡ ኦሪትን ፡ ሲማር ፡ ፈጣሪው ፡ ቃል ፡ በቃል ፡ ይነግረው ፡ ነበር ።

በጣም ፡ ስለ ፡ ገባው ፡ ጥፈቱ ፡ ትምርቱ ፡ የብርሃን ፡ ቀለም ፡ ቀንድ ፡ ተግለ ፡ በፊቱ ፤ ተገልበጠ ፡ እያለ ፡ ውስደ ፡ ጽልመት ፡ በክርስቶስ ፡ አምላል ፡ እስኪሸፍኑት ።

የተማረውንም ፡ ጽላቱን ፡ ቢገድፍ ፡ ወዲያው ፡ ቶሎ ፡ ሰጠው ፡ ዘኢያገድፍ ፤ ዘኢያገድፉም ፡ የወርቅ ፡ ታቦት ፡ ኹስቱ ፡ ኪሩቤል ፡ የተሣሉበት ።

ጽላትና ፡ ታቦት ፡ አርኣያና ፡ አምሳል ፤ በተለየ ፡ አካሉ ፡ ሰው ፡ ለኾነው ፡ ቃል ።

ሰው ፡ ከመኾን ፡ በፊት ፡ ሰውን ፡ ሊባርክ ፡ ወደ ፡ ደብረ ፡ ሲና ፡ እንዲወርድ ፡ አምላክ ፡ አስቀድሞ ፡ ስብኳል ፡ ነቢዩ ፡ ሔኖክ ፡ ለንግቱሳላ ፡ ለናህ ፡ ለላሜክ ።

ስንኳን ፡ በዚኽ ፡ ዓለም ፡ በገነንጋዔው ፡ ቦታ ፡ በሰማይም ፡ አስ ፡ የጥፈት ፡ ገበታ ፤ ፊደልና ፡ ጥፈት ፡ በሰማይ ፡ እንዳሉ ፡ ብሉይና ፡ ሐዲስ ፡ ይመሰክራሉ ።

አንድ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ያለሙ ፡ መምር ፡ የሰማዩ ፡ ሥርዐት ፡ ተሠርቷል ፡ በምድር ።

ክአጽሞው ፡ አንሥቶ ፡ እስክዚኽ ፡ ድረስ ፡ የስብከቱ ፡ መግቢያ ፡ መቅድምና ፡ ራስ ።

በሴምና ፡ በካም ፡ በያፌት ፡ ነገድ ፡ ከሦስት ፡ ተከፍሎ ፡ የፊደል ፡ ትውልድ ፤ በዛፍ ፡ ይመሰላል ፡ ዐጽቁ ፡ ስስ ፡ በዛ ፡ ከርሱ ፡ ፍሬ ፡ በልተን ፡ አእምሮ ፡ እንድንገዛ ።

ከማዕደንም ፡ ጋራ ፡ ሲያመዛዝኑት ፡ ላቂያና ፡ ብልጣ ፡ አለው ፡ ከስድስቱ ፡ ዐይነት ።

ወርቅ ፡ ነው ፡ ወርቅ ፡ ነው ፡ የግእዝ ፡ ፊደል ፡ ሰባት ፡ እጅ ፡ የጠራ ፡ ክሰባት ፡ ዛሕል ፤ ልኩና ፡ ሚዛኑ ፡ በፍጥረት ፡ ቍጥር ፡ ክአሌፍ ፡ እስክ ፡ ታው ፡ ኻያ ፡ ኹለት ፡ ልጥር ፤ ፩ዱ ፡ ልጥር ፡ ፊደል ፡ ፩ መክሊት ፡ ወርቅ ፡ እንደ ፡ ሙሴ ፡ ተቀዋም ፡ ባለሰባት ፡ ዐጽቅ ።

በዕለታት ፡ አምሳል ፡ ክሰባት ፡ ተከፍሎ ፡ ሰባት ፡ ቤት ፡ ይባላል ፡ ፊደላችን ፡ ወሎ ።

የትውልዱም ፡ ሐረግ ፡ የሚሳብበት ፡ ሰባቱ ፡ ሰማያት ፡ ሰባቱ ፡ ሀብታት ።

ሰባት ፡ ቤት ፡ መባሉም ፡ ስሙ ፡ ፩ ሲኾን ፡ ፈጽሞ ፡ ያስረዳል ፡ ፍጹምንቱን ፤ ፍጹም ፡ እንደ ፡ ኾነም ፡ ይኸ ፡ ሰባት ፡ ቍጥር ፡ አምላክ ፡ ነቢያት ፡ ርሱ ፡ ይመስክር ።

ልጅነት ፣ የያዘው ፣ ምላሳችን ፣ መንካ ፣
ከቋንቋችን ፣ በፊት ፣ ሌላ ፣ ቋንቋ ፣ አይንካ ።
ግእዝ ፣ ክግርኛ ፣ አስተባብሮ ፣ ሲያውቅ ፣
ከውጭ ፣ አገር ፣ ቋንቋ ፣ ያን ፣ ጊዜ ፣ ይንጠቅ ፤
ትምርቱንም ፣ ይጎዳው ፣ እንደ ፣ ምርኮ ፣ ክብት ፣
ባማርኛው ፣ መንገድ ፣ በግእዙ ፣ ስልት ፤
የጥበቡን ፣ መጽሐፍ ፣ ሥራ ፣ መሥሪያውን ፣
አንብቦ ፣ ተርጉሞ ፣ ቶሎ ፣ እንዲያስማን ።

የትምርቱ ፣ አካሄድ ፣ እንዲኸ ፣ ቢሻሻል ፣
የሦስቱ ፣ ዓመት ፣ ሥራ ፣ በሦስት ፣ ወር ፣ ያልቃል ።
በጌታችን ፣ እምሳል ፣ በሐዋርያት ፣
በተከታዮቹም ፣ በስብዓ ፣ አርድእት ፤
ሦስት ፣ ዓመት ፣ ከሦስት ፣ ወር ፣ ተግቶ ፣ የሚሠራ ፣
ሳያገኝ ፣ አይቀርም ፣ የሚበቃ ፣ እገመራ ።
ዕንቊላሉ ፣ ምኞት ፣ እሳቱ ፣ ፈሊጥ ፣
ከተዳፈንበት ፣ ክልባችን ፣ ውስጥ ፣
በንይስ ፣ ሥላሴ ፣ ይፍረጥ ፣ ይገለጥ ፤
የረጋውም ፣ ወተት ፣ ይገፋ ፣ ይናጥ ፤
የትምርቱን ፣ ቅቤ ፣ ሕፃኑ ፣ እንዲውጥ ፤
ጐበዝም ፣ ተቀብቶ ፣ እንዲቅለጠለጥ ።

ክሴማዊው ፣ እሳት ፣ ክግእዝ ፣ ፊደል ፣
ተማሪው ፣ ተጋፍጠ ፣ እስኪቀጣጠል ፤
እየቈሰቈሱት ፣ መምህራን ፣ በቃል ፣
ትምርቱ ፣ እስኪጋጋም ፣ ዕውቀቱ ፣ እስኪበስል ፤
ፍሕሙ ፣ እስኪመርትና ፣ እስኪህቅ ፣ በገል ፣
ከመጢስ ፣ ከመንደድ ፣ ማነው ፣ ገዡም ፣ የሚል ።
መልኩንስ ፣ በሰው ፣ መልክ ፣ ማነው ፣ የማያይ ፣
የሰው ፣ መስታዮቱ ፣ ሰው ፣ አይደለሞይ ።
የብድሩ ፣ ቋንቋ ፣ የልቆው ፣ ትምርት ፣
አይበቃንምና ፣ ለነግ ፣ ለማልስት ፤
ያማርኛው ፣ ጓድጓድ ፣ የግእዙ ፣ ወዘቀት ፣
አፈ ፣ መምር ፣ ኹሉ ፣ ደስፋ ፣ ይከፈት ፤
በየውስጡ ፣ ያለው ፣ ጥሩ ፣ ሐሳብ ፣ ምንጭ ፣
ይፈልፍል ፣ ይገንፍል ፣ ይውጣ ፣ ወደ ፣ ውጭ ፤
ትምርታችን ፣ ይጐረፍ ፣ ቋንቋችን ፣ ይፍሰስ ፤

ኹለት ፣ ኹለት ፣ ኹኖ ፣ ለምን ፣ ተሠራና ።
ዐማርኛችንስ ፣ በጥፈት ፣ ጐዳና ፣
ክባቱ ፣ ክግእዝ ፣ መቹ ፣ ይለይና ።
የትምርቱስ ፣ ችጋር ፣ የውቀቱ ፣ ቀጠና ፣
ፊደል ፣ በግሳንስ ፣ መቹ ፣ ይለቅና ።
በሴማውያን ፣ ዘንድ ፣ በያፌት ፣ ልጆች ፣
ይኸ ፣ ነገር ፣ ቢሰማ ፣ ያሰኛል ፣ ሞኞች ።

ብርሃንና ፣ ሰላም ፣ የወፌ ፣ ማሲንቆ ፣
የፊደልን ፣ አውታር ፣ ብዛቱን ፣ ጠይቆ ፤
የተገባ ፣ ምላሽ ፣ የሚሰጠው ፣ ቢያጣ ፣
ፊደል ፣ እናሳንስ ፣ ማለት ፣ ስላመጣ ፤
የተማሪ ፣ ቤቱን ፣ ከማስፋት ፣ በቀር ፣
ሌላ ፣ ምክር ፣ አያሻም ፣ የፊደል ፣ ነገር ።
በዚያው ፣ ሥራ ፣ መሥራት ፣ ቀኝ ፣ እያለልን ፣
ለምን ፣ እንሄዳለን ፣ ግራ ፣ ግራውን ።

ምክርስ ፣ የሚያስፈልግ ፣ በሙሉው ፣ ፊደል ፣
የትምርቱን ፣ መጽሐፍ ፣ ማውጣት ፣ በየክፍል ፣
ለተማሪ ፣ ቤቱም ፣ ደረጃ ፣ መሥራት ፣
በፊደሉ ፣ ቍጥር ፣ ካንድ ፣ እስከ ፣ ሰባት ፤
የትምርቱንም ፣ ሕግ ፣ ማደስ ፣ መለወጥ ፣
ከፊደል ፣ ገሥሮ ፣ ትምርቱ ፣ እንዲሠልጥ ፤
የቋንቋውን ፣ ቅንጣት ፣ ቃልና ፣ ንባብ ፣
በፊደሉ ፣ ተራ ፣ መልቀም ፣ መሰብሰብ ፤
የፊደሉም ፣ ተራ ፣ ሥሩ ፣ መንሻው ፣
መቹ ፣ እንደ ፣ ቅኔያችን ፣ ጣፋ ፣ መድረሻው ።
ዐዲስ ፣ መንገድ ፣ ይውጣ ፣ ባዲሱ ፣ ንጉሥ ፣
ሰው ፣ ክደረሰበት ፣ ቶሎ ፣ እንድንደርስ ።
ዙሪያ ፣ ጥምጥም ፣ ኹኖ ፣ የዱሮው ፣ መንገድ ፣
ዕውቀት ፣ ወጥሮብናል ፣ በርሱ ፣ እንዳንሄድ ።
ከፊደል ፣ ላይ ፣ ዘሎ ፣ በሐዲስ ፣ ላይ ፣ ፊጥ ፣
ጥርስ ፣ ሳያወጡ ፣ ዳቦ ፣ እንደ ፣ መግመጥ ።
ቃል ፣ ትምርቱም ፣ ይኹን ፣ ሰዋስው ፣ ርባታ ፣
በመልካ ፣ መልኩና ፣ በውዳሴው ፣ ፈንታ ።
ቋንቋውን ፣ ሳያውቁ ፣ መጮኽ ፣ መለፍለፍ ፣
ገደል ፣ ያስመስላል ፣ ወይም ፣ ፎኖግራፍ ።

የፊደል ፣ ዘይቤ ፣ ባሥር ፣ ቃል ፣ ሲፈታ ፣
የቋንቋ ፣ ደብኘት ፣ የቃል ፣ ኹሉ ፣ ጐታ ፤
የመጻሕፍት ፣ ምንጭ ፣ የምስጢራት ፣ ንቅ ፣
ቢቀዳ ፣ ቢቀዳ ፣ ውሃው ፣ የማያልቅ ።
ምስጢረ ፣ ሥላሴ ፣ ምስጢረ ፣ ሥጋዌ ፣
ኅቡኡ ፣ ረቂቁ ፣ የአምላክ ፣ ህላዌ ፤
በፊደል ፣ መነጽር ፣ ይታየናል ፣ ገዝፎ ፣
አልፋና ፣ ዖሜጋን ፣ ለብሶ ፣ ተገኖናፎ ።
አልፋ ፣ የአካላት ፣ ያ ፣ የመለኮት ፤
ትርጓሜው ፣ ቅድምና ፣ ጥንት ፣ ወተፍጸሜት ።
የሀም ፣ ሦስትነት ፣ እንደ ፣ ሦስት ፣ ቅዳሴ ፣
ወይም ፣ እንደ ፣ አዳም ፣ አርኣያ ፣ ሥላሴ ፤
ያዳም ፣ አርኣያነት ፣ እሙን ፣ የታመነ ፣
ለባዊ ፣ ነባቢ ፣ ሕያው ፣ ስለ ፣ ኹነ ።
በአልፋ ፣ ገሥሮ ፣ በያ ፣ መጨረስ ፣
የጽርኣውያን ፣ ሕግ ፣ የስብኣ ፣ ጢሮስ ።
እኛም ፣ በሴም ፣ ቋንቋ ፣ እንደ ፣ ባህላችን ፣
ጽርኡን ፣ ክግእዙ ፣ እያስማማን ፤
ሥሩንና ፣ ጫፉን ፣ ገጥመን ፣ በንፈታው ፣
አልፋ ፣ ወያ ፣ ማለት ፣ አሌፍ ፣ ወታው ፣ ነው ።

አንድ ፣ አ ፣ እንዳይበቃው ፣ ለትግሬ ፣ ላማራ ፣
አልፋ ፣ ወያ ፣ ብሎ ፣ ኹለቱንም ፣ ጠራ ።
ሠወስቱ ፣ ሀ(ሐ)ደግሞ ፣ ሠወስት ፣ ምስክር ፣
ለብስቡ ፣ ለሐዲስ ፣ ለቋንቋ ፣ ምስጢር ።
ባንዱ ፣ የሚጣፈው ፣ በሌላው ፣ ሲጣፍ ፣
ቋንቋው ፣ ተበላሽቶ ፣ ይኸናል ፣ ጸያፍ ።
የጸሓፊ ፣ ደዌ ፣ ያታሚ ፣ መከራ ፣
ጠንቅቆ ፣ አለማወቅ ፣ የፊደልን ፣ ሥራ ።
እንዳገኙ ፣ መጣፍ ፣ በድፍረት ፣ በመላ ፣
የቋንቋ ፣ ደረመን ፣ የመጽሐፍ ፣ ቢስ ፣ ገላ ።
ንባብ ፣ የሚያሳክክ ፣ ምስጢር ፣ የሚቁምጥ ፣
መልክአ ፣ ትርጓሜ ፣ የሚለዋውጥ ።

እስነጥብም ፣ መጣፍ ፣ የንባብ ፣ ቁጥኝ ፣
ጣፊዉን ፣ መጣፉን ፣ ቢያክ ፣ ቢያክ ፣ የሚያስኝ ።
ሠና ፣ ስ ፣ ጸና ፣ ዐም ፣ አራቱ ፣ ቀለም ፣
አዳምና ፣ ሔዋን ፣ ሐዋንና ፣ አዳም ፤
ማንም ፣ ሰው ፣ ተንሥዶ ፣ እንዳይለያቸው ፣
እግዜር ፣ በጥበቡ ፣ ያጣመራቸው ።
ከበገና ፣ አውታሮች ፣ ከሥሩ ፣ ኻርማች ፣
ኹለቱ ፣ ሊቃውንት ፣ ኹለቱ ፣ እማሬት ፤
ምንም ፣ አንድ ፣ ቢኸን ፣ የድምጣቸው ፣ ስልት ፣
በውስጥ ፣ አለውና ፣ ልዩ ፣ ልዩነት ፤
ኹሉም ፣ ካልተገኙ ፣ በኹለትነት ፣
አንዳንዱ ፣ እንዳይበቁ ፣ ለበገናነት ፣
ፊደልም ፣ እንዲኸ ፣ ነው ፣ በቋንቋ ፣ ሥርዐት ፤
ከሄኖስ ፣ ገሥሮ ፣ ከሰብአ ፣ ትካት ።
ከሠርቱ ፣ ቃላትም ፣ አንዱ ፣ ቃል ፣ ቢጐድል ፣
ትምርቱና ፣ ሕጉ ፣ ሕጹጽ ፣ ይባላል ።
እንምን ፣ አለበት ፣ እንኹሉ ፣ ቀኙ ፣
በትግሪኛ ፣ መንፈስ ፣ ፊደልን ፣ ሲቃኙ ፤
ከግእዝ ፣ ስይተን ፣ በማርኛን ፣ ኹሉ ፣
ባኀ ፣ አ ፣ ባኀ ፣ ሀ ፣ (ሰ ፣ ጸ) እንጣሩ ፣ የሚሉ ፤
አላወቁም ፣ ይኸን ፣ ቋንቋ ፣ እንዲበላሽ ፣
ንባቡም ፣ ምስጢሩም ፣ እንዲኸን ፣ ፈራሽ ።
እንደነሶምሶን ፣ ዐይኑ ፣ ከወጣማ ፣
ጥፈቱም ፣ ቋንቋዉም ፣ ይኸናል ፣ ጨለማ ።
ዐወቀች ፣ ዐወቀች ፣ ዐወቀች ፣ ቢሊት ፣
መጣፉን ፣ ዐጠበች ፣ የሚሉት ፣ ተረት ፤
ላየው ፣ ላስተዋለው ፣ ላይናማ ፣ ደብተራ ፣
ሠምና ፣ ወርቅ ፣ ነው ፣ ክዚኽ ፣ ምኞት ፣ ጋራ ።
የፊደልን ፣ ገላ ፣ ደፍሮ ፣ ለመሞረጥ ፣
ሐኪም ፣ መኽን ፣ ያሻል ፣ በአፍኣ ፣ በውስጥ ፤
አፍኣው ፣ ዐማርኛ ፣ ውስጡ ፣ ግእዝ ፣ ነው ፣
ትምርቱ ፣ እንደ ፣ ገደል ፣ ያልተደፈረው ።
ለቋንቋ ፣ በሽታ ፣ ለጥፈት ፣ ሕማም ፣
ከትምርት ፣ በቀር ፣ መድኀኒት ፣ የለም ።
እንደ ፣ ምን ፣ ይቻላል ፣ በቀንኛ ፣ ፊደል ፣
የቋንቋውን ፣ ሞክሼ ፣ ማወቅ ፣ መነጠል ።
ጥንቱን ፣ ፊደላችን ፣ ሴማዊው ፣ በገና ፣

ጕርፋ ፣ ማዕበሉ ፤ አፍሪቃን ፣ ያልብስ ፤
ኤውሮፓንም ፣ ያርካ ፣ እስያን ፣ ያርስ ፤
ወዳሜሪካንም ፣ ይጋልብ ፣ ይገሥግሥ ፤
እኛንም ፣ ያጥምቀን ፣ እንደ ፡ ዮርዳኖስ ፤
ቀድሞ ፣ የተጣፈው ፣ በጥቁር ፣ ክርታስ ፣
መጽሐፈ ፡ ዕዳችን ፣ እንዲደመሰስ ፣
በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ።
(አሐዱ ፡ አምላክ ፤ አሜን)

(፲፱)


ሀየንተ ፡ ፊደል ፡ ሐዋርያ ።

የፊደላዋሪያ ፡ ለውጥ ፡ ወይም ፡ ምትክ ። (ተረት) ምትክ ፡ ራሱን ፡ አያክ) ።

ዕለታተ ፡ ሰንበት = የሳምንት ፡ ቀኖች ።

እሑድ ። ሰኑይ ። ሠሉስ ። ረቡዕ ። ኀሙስ ። ዐርብ ። ቀዳም ።

= ። ሰ ኑ ። ማግሰኞ ። ሮ ብ ። ቍ ሙ ስ ። = ። ቅ ዳ ሜ ።



ዘከመ ፡ ፈጠረ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዓለመ ፡ ወኵሎ ፡ ዘውስቴቱ ፡ በሰዱስ ፡ ዕለት ።
እግዜር ፡ ዓለምንና ፡ በውስጡ ፡ ያለውን ፡ ኹሉ ፡ በስድስት ፡ ቀን ፡ እንደ ፡ ፈጠረ ።

ግዋም ፡ ስለ ፡ ፈጣሪና ፡ ስለ ፡ ፍጥረት ፡ (ስላሠርቱና ፡ ስለ ፡ ስድስቱም ፡ ቃላት) ፊሰ ፡
ጕበና ፡ ቤት ፡ የንበሩ ፡ ኦርቶደክሳዊው ፡ ሊቅ ፡ አለቃ ፡ ዕንቈ ፡ ባሕርይ ፡ የገጠሙት ።

አፉቱ ፡ ባሕርያት ፡ ሰባቱ ፡ ሰማያት ፡
ሕያዋን ፡ መላእክት ፡ ብርሃንና ፡ ጽልመት ፤
እነዚኽ ፡ ስምንቱ ፡ ተፈጥረዋል ፡ እሑድ ፡
በረቂቁ ፡ ባሕርይ ፡ በሥላሴ ፡ ፈቃድ ።
ውሀን ፡ ከቦ ፡ ከፍለው ፡ ጌዱን ፡ እጅ ፡ አጽንተው ፡
በንፋስ ፡ ተራዳ ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ ዘርግተው ፡
በዕለተ ፡ ሰኑይ ፡ ፈጠሩ ፡ ሥላሴ ፤
በአሪት ፡ ዘፍጥረት ፡ እንደ ፡ ጣፈው ፡ ሙሴ ።
አዝርዕቱም ፡ እትክልቱም ፡ ከዕፀዋት ፡ ጋራ ፡
ማግሰኞ ፡ ተገኙ ፡ በመለኮት ፡ ሥራ ።
ዐሓይን ፡ ጨረቃን ፡ ኮከብን ፡ ጨምሮ ፡
ረቡዕ ፡ ፈጠረ ፡ በቃሉ ፡ ተናግሮ ።

ጎሙስ ፡ ክባሕር ፡ ውስጥ ፡ የፈጠራቸው ፡
እንስሳት ፡ አራዊት ፡ አዕዋፍ ፡ ናቸው ።
የጎሙስን ፡ ፍጥረት ፡ በመልክ ፡ የሚመስሉ ፡
ዐርብም ፡ ክየብስ ፡ ላይ ፡ ፈጠረ ፡ በቃሉ ።
ደግሞ ፡ በዚኹ ፡ ቀን ፡ በሦስተኛው ፡ ሰዓት ፡
አዳምን ፡ ፈጠረው ፡ ሊያኖረው ፡ በገነት ።
ቀዳሚት ፡ ዐረፈ ፡ ሥራውን ፡ ቢጨርስ ፡
ድካም ፡ የሌለበት ፡ የዘላለም ፡ ንጉሥ ።
ፈጥሮ ፡ ስሚገዛን ፡ ስሚመግበን ፡
ክብርና ፡ ምስጋና ፡ ጎይልና ፡ ሥልጣን ፤
ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን ፡ ወአሜን ።

(፳)

ክፍላተ ፡ ዘመን ፡ ወጊዜ ፤ አው ፡ መስፈርታት ፡ ወአምጣናት ።

የዘመንና ፡ የጊዜ ፡ ክፍሎች ፤ ወይም ፡ መስፈሪያዎችና ፡ ልኮች ።

ቀመር ። ዓመት ። ወርኅ ። ሰንበት ። ዕለት ። ሰዓት ። ደቂቃ ። ክልኢት ።

(ቀመር) ባመት ፡ የሚቈጠር ። (ዓመት) ፫፻፷፭ ፡ ቀን ። ክፉብ ። (ወርኅ) ፴ ፡ ቀን ። (ሰንበት) ፯ ፡
ቀን ። (ዕለት) ፷፬ ፡ ሰዓት ። (ሰዓት) ፷ ፡ ደቂቃ ። (ደቂቃ) ፷ ፡ ክልኢት ። (ክልኢት) ፩ ፡ ቅጽበት ።

(፳፩)

ክፍላተ ፡ ዓመት ፡ ወከዋክብተሆሙ = ያመት ፡ ክፍሎችና ፡ ኮከቦቻቸው ።

መጸው ። ሐጋይ ። ጸደይ ። ክረምት ።

ምልክኤል ። ሕልመልሜሌክ ። ሚላኤል ። ናርኤል ። (ሔኖክ)

ወዕለታቲሆሙኒ ፡ በበተሰዓ ፡ ወአሐዱ ፡ ዕለት ፡ ወራብዕት ።

ቀኖቻቸውም ፡ (ጸአ ፡ ጸአ) ፻፷ ፡ ፻፷ ፡ ቀን ፡ ተሩብ ፡ ናቸው ።

መጸው ፡ እምአመ ፡ ዕሥራ ፡ ወሰዱሱ ፡ ለመስከረም ፡ እስከ ፡ አመ ፡ ዕሥራ ፡ ወሰዱሱ ፡ ለኅዳሥሥ ፤ ወእምድኅሬሁ ፡ ሐጋይ ። ዝኒ ፡ በክፍለ ፡ አፍ

— ፴፱ —

ፈቅያ ፡ እንተ ፡ ባቲ ፡ ኢትዮጵያ ፤ ወእከ ፡ በክፍለ ፡ ኤውሮፓ ፡ ወእስያ ።

መጸው ፡ ከመስከረም ፡ ኗኄ ፡ እስከ ፡ ታኅሣሥ ፡ ኗኄ ፡ ነው ፤ ክዚያ ፡ በኹዋላ ፡ በጋ ። ይኽም ፡ ኢትዮጵያ ፡ ባለችበት ፡ በአፍሪቃ ፡ ክፍል ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ በኤውሮፓና ፡ በእስያ ፡ ክፍል ፡ አይደለም ።

(፩፬)

ሰመንቱ ፡ ማእዝናት ፡ ዐቢያን ፡ ወንኡሳን = ፭ቱ ፡ ማኅፀናት ።

ዐቢያን = ታላላቆች ።

ምሥራቅ ። ምዕራብ ። ሰሜን ። ደቡብ ።

ንኡሳን = ታናናሾች ።

መስዕ ። አዜብ ። ባሕር ። ሊባ ።

(፩፫)

ኅምስቱ ፡ ክፍላተ ፡ ዓለም = ፭ቱ ፡ የዓለም ፡ ክፍሎች ።

አፍሪቃ ። እስያ ። ኤውሮፓ ። ዖሲያንያ ። አመሪቃ ፤ ካ ።

(፩፬)

ስመ ፡ ኅምስ ፡ ሐዋስ ፡ ወግብራቲሆን = ያ፭ቱ ፡ ሕዋሳት ፡ ስምና ፡ ግብር ።

(ስም)		(ግብር)		(ሥራ)		
ዐይን ።	—	ርእይ ።	—	ማየት ።	—	ያይን ።
እዝን ።	—	ሰሚዕ ።	—	መስማት ።	—	የዠሮ ።
አንፍ ።	—	አጼንዎ ።	—	ማሽተት ።	—	ያፍንፉ ።
አፍ ።	—	ጥሚም ።	—	መቅመስ ።	—	ያፍ ።
እድ ።	—	ገሲስ ።	—	መዳሰስ ።	—	የድ ።

በንዚኽ ፡ ላይ ፡ ደግሞ ፡ እግርና ፡ አባለ ፡ ዘር ፡ ሲጨመሩ ፡ ፯ ይኾናሉ ።

— ፴፰ —

(፩፭)

አስማተ ፡ ሰብዐቱ ፡ ከዋክብት ፡ ዐበይት ፡ እለ ፡ ይነሥኡ ፡ ብርሃነ ፡ እምፀሓይ ።

ከፀሓይ ፡ ብርሃን ፡ የሚቀበሉ ፡ የ፯ቱ ፡ ታላላቅ ፡ ከዋክብት ፡ ስሞች ።

ዐጣርድ ። ዙህራ ። መሪሕ ። መሽተሪ ። ዙሐል ። ኡራኑስ ። ነይጡን ።

እንደ ፡ ፈላስፎች ፡ ቊጥር ፡ ግን ፡ በንዚኽ ፡ ላይ ፡ ምድር ፡ ስትጨመር ፡ ፰ ይኾናሉ ።

(፩፯)

አስማተ ፡ ዐሠርቱ ፡ ወክልኤቱ ፡ አውራኅ ፡ ወከዋክብቲሆሙ ።

ያ፲፪ቱ ፡ ወር ፡ ስምና ፡ ኮከብ ።

		(ወር)	(ኮከብ)	(ፍች)
፩	—	መስከረም ፤	ሚዛን ፡	በቁሙ ።
፪	—	ጥቅምት ፤	ዐቅራብ ፡	ጊንጥ ።
፫	—	ኅዳር ፤	ቀውስ ፡	ቀስተኛ ።
፬	—	ታኅሣሥ ፤	ጀደይ ፡	የፍየል ፡ ጠቦት ።
፭	—	ጥር ፤	ደለው ፡	ማሕየብ (መቅኛ) ።
፮	—	የካቲት ፤	ሑት ፡	ዓሣ ።
፯	—	መጋቢት ፤	ሐመል ፡	አውራ ፡ በግ ።
፰	—	ሚያዝያ ፤	ተውር ፡	(ኦር) በሬ ።
፱	—	ግንቦት ፤	ጀውዛ ፡	ጥንድ ።
፲	—	ሠኔ ፤	ሸርጣን ፡	ጕርምጥ ።
፲፩	—	ሐምሌ ፤	አሰድ ፡	አንበሳ ።
፲፪	—	ነሐሴ ፤ (ጳግሜ)	ሰንቡላ ፡	ሽቷም ፤ ባለሽቱ ።

ራቅያ ፡ እንተ ፡ ባቲ ፡ ኢትዮጵያ ፤ ወአከ ፡ በክፍለ ፡ ኤውሮፓ ፡ ወእስያ ።

መጸው ፡ ክመስክረም ፡ ፳፯ ፡ እስከ ፡ ታኅሣሥ ፡ ፳፯ ፡ ነው ፤ ክዚያ ፡ በኹዋላ ፡ በጋ ። ይኸም ፡ ኢትዮጵያ ፡ ባለችበት ፡ በአፍሪቃ ፡ ክፍል ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ በኤውሮፓና ፡ በእስያ ፡ ክፍል ፡ አይደለም ።

(፳፱)

ሰመንቱ ፡ ማእዝናት ፡ ዐቢያን ፡ ወንኡሳን = ፭ቱ ፡ ማዝኖች ።

ዐቢያን = ታላላቆች ።

ምሥራቅ ። ምዕራብ ። ሰሜን ። ደቡብ ።

ንኡሳን = ታናናሾች ።

መስዕ ። አዜብ ። ባሕር ። ሊባ ።

(፴)

ኅምስቱ ፡ ክፍላተ ፡ ዓለም = ፭ቱ ፡ የዓለም ፡ ክፍሎች ።

አፍሪቃ ። እስያ ። ኤውሮፓ ። ያሲያንያ ። አመሪቃ ፤ ከ ።

(፴፩)

ስመ ፡ ኅምስ ፡ ሕዋስ ፡ ወግብራቲሆን = ያ፭ቱ ፡ ሕዋሳት ፡ ስምና ፡ ግብር ።

(ስም)		(ግብር)		(ሥራ)		
ዐይን ።	—	ርእይ ።	—	ማየት ።	—	ያይን ።
እዝን ።	—	ሰሚዕ ።	—	መስማት ።	—	የጆሮ ።
አንፍ ።	—	አጼንዎ ።	—	ማሽተት ።	—	ያፍንጫ ።
አፍ ።	—	ጥዒም ።	—	መቅመስ ።	—	ያፍ ።
እድ ።	—	ገሲስ ።	—	መዳሰስ ።	—	የጅ ።

በነዚኽ ፡ ላይ ፡ ደግሞ ፡ እግርና ፡ አባለ ፡ ዘር ፡ ሲጨመሩ ፤ ፯ ይኾናሉ ።

(፴፫)

አስማተ ፡ ሰብዐቱ ፡ ከዋክብት ፡ ዐበይት ፤ እለ ፡ ይነሥኡ ፡ ብርሃነ ፡ እምፀሓይ ።

ክፀሓይ ፡ ብርሃን ፡ የሚቀበሉ ፡ የ፯ቱ ፡ ታላላቅ ፡ ከዋክብት ፡ ስሞች ።

ዐጣርድ ። ዙህራ ። መሪሕ ። መኽተሪ ። ዙሐል ። ኡራኑስ ። ነይጡን ።

እንደ ፡ ፈላስፎች ፡ ቊጥር ፡ ግን ፡ በነዚኽ ፡ ላይ ፡ ምድር ፡ ስትጨመር ፡ ፰ ይኾናሉ ።

(፴፬)

አስማተ ፡ ዐሠርቱ ፡ ወክልኤቱ ፡ አውራኅ ፡ ወከዋክብተሆሙ ።

ያ፲፪ቱ ፡ ወር ፡ ስምና ፡ ኮከብ ።

		(ወር)	(ከከብ)	(ፍች)
፩	—	መስከረም ፤	ሚዛን ፡	በቁሙ ።
፪	—	ጥቅምት ፤	ዐቅራብ ፡	ጊንጥ ።
፫	—	ኅዳር ፤	ቀውስ ፡	ቀስተኛ ።
፬	—	ታኅሣሥ ፤	ጀዲይ ፡	የፍየል ፡ ጠቦት ።
፭	—	ጥር ፤	ደለው ፡	ማሕየብ (መቅኛ) ።
፮	—	የካቲት ፤	ሑት ፡	ዓሣ ።
፯	—	መጋቢት ፤	ሐመል ፡	አውራ ፡ በግ ።
፰	—	ሚያዝያ ፤	ተውር ፡	(ዕር) በሬ ።
፱	—	ግንቦት ፤	ጀውዛ ፡	ጥንድ ።
፲	—	ሠኔ ፤	ሸርጣን ፡	ጕርምጥ ።
፲፩	—	ሐምሌ ፤	አሰድ ፡	አንበሳ ።
፲፪	—	ነሐሴ ፤ (ጳግሜ)	ሰንቡላ ፡	ሽቷም ፤ ባለሽቱ ።

(፷፯)

ርእሰ ፡ ዐሠርቱ ፡ ቃላት = ያሠርቱ ፡ ቃላት ፡ ራስ ።

አፍቅሮ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አምላክከ ፡ በኵሉ ፡ ልብከ ፡ ወበኵሉ ፡ ነፍስከ ፡ ወበኵሉ ፡ ኀይልከ = ፈጣሪኽ ፡ እግዜርን ፡ በፍጹም ፡ ልብኽና ፡ በፍጹም ፡ ሰውነትኽ ፡ በፍጹም ፡ ኀይልኽ ፡ ውደደው ፡ (ዘዳ ፮ ፡ ፭ ። ፯ ፡ ፲፪) ።



ዘከመ ፡ ወሀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለሙሴ ፡ ጽላተ ፡ ሕግ ፡ ወት
እዛዝ ፡ ጽሑፋተ ፡ እንተ ፡ ክልኤ ፡ ፍና ፡ በደብረ ፡ ሲና ።

እግዜር ፡ ለሙሴ ፡ የሕግና ፡ የትእዛዝ ፡ ጽላት ፡ እንደ ፡ ሰጠው ፡ (ዘፀ፴፩ ፡ ፲፰ ። ፴፪ ፡ ፲፭ ፡ ፲፮) ።

«ሕግ ፡ አታድርግ ፡ አታድርግ ፤ ትእዛዝ ፡ አድርግ ፡ አድርግ ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ ነው» ።

ዐሠርቱ ፡ ቃላት ፡ አሪት ፡ (ዘፀ፳ ፡ ፫ ፡ ፯ ፡ ፰ ፡ ፲፪—፲፯ ። ዘሌ፲፱ ፡ ፲፰) ።

(፩)አነ ፡ ውእቱ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክከ ፤ ኢታምልክ ፡ ባዕደ ፡ አምላክ ፡ ዘእንበሌየ = ፈጣሪኽ ፡ እግዜር ፡ እኔ ፡ ነኝና ፤ ከኔ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ አምላክ ፡ አታምልክ ። (፪) ኢትምሐል ፡ ስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፈጣሪከ ፡ በሐሰት = ባለሰት ፡ የፈጣሪኽን ፡ የግዜርን ፡ ስም ፡ ጠርተኽ ፡ አትማል ። (፫) ተዘከር ፡ ዕለተ ፡ ሰንበት ፡

(፷፯)

ሩቅና ፡ ቅርብ ፡ ወንድና ፡ ሴት ፡ አንድና ፡ ብዙ ፡ ተለይተው ፡ የሚታወቁበት ፡ ፤ የርባታ ፡ መደብ ፤ ወይም ፡ መፅ ፡ ሰራዊት ። የብዙዎቱ ፡ ወንደኞችና ፡ ሴቶች ፡ ዐማርኛቸው ፡ አንድ ፡ ነው ፤ እንደ ፡ ግእዙ ፡ ልዩነት ፡ የለውም ። (ቀዳማይና ፡ ትንቢት ፡ ዘንድና ፡ ትእዛዝ ፡ አንቀጽ)

ያንድ ፤ —	አነ ፡	እኔ ፡	ጸሐፍኩ ፡	ጣፍኩ ። (ያለፈ)
»	አንተ ፡	አንተ ፡	ጸሐፍከ ፡	ጣፍክ ።
»	አንቲ ፡	አንች ፡	ጸሐፍኪ ፡	ጣፍሽ ።
»	ውእቱ ፡	(ያ) ርሱ ፡	ጸሐፈ ፡	ጣፈ ።
»	ይእቲ ፡	(ያች) ርሲ ፡	ጸሐፈት ፡	ጣፈች ።
የብዙ ፤ —	ንሕነ ፡	እኛ ፡	ጸሐፍነ ፡	ጣፍን ፡ ን ።
»	አንትሙ ፡	እናንት ፡	ጸሐፍክሙ ፡	ጣፋችኹ ።
»	አንትን ፡	»	ጸሐፍክን ፡	»
»	እሙንቱ ፡	እኒያ ፡	ጸሐፉ ፡	ጣፉ ።
»	እማንቱ ፡	»	ጸሐፉ ፡	»

የጥፊ ፡ ዝርዝር ፤ ወይም ፡ ርባታ ።

	(መጽሐፍ)	(መጣፍ)
ያንድ ፤ —	መጽሐፍየ ፤	መጣፌ ።
»	መጽሐፍከ ፤	መጣፍኽ ።
»	መጽሐፍኪ ፤	መጣፍሽ ።
»	መጽሐፉ ፤	መጣፉ ።
»	መጽሐፋ ፤	መጣኟ ።
የብዙ ፤ —	መጽሐፍነ ፤	መጣፋችን ።
»	መጽሐፍክሙ ፤	መጣፋችኹ ።
»	መጽሐፍክን ፤	»
»	መጽሐፎሙ ፤	መጣፋቸው ።
»	መጽሐፎን ፤	»

ሌላዉን ፡ ኹሉ ፡ አንቀጽና ፡ ጥቂ ፡ አንዲኽ ፡ አያልኽ ፡ አርባ ።

እጽሕፍ ፡ እጥፋለኹ ። እጽሐፍ ፡ እጥፍ ፡ ዘንድ ፤ እንድጥፍ ፤ ልጥፍ ። እጽሐፍ ፡ ልጣፍ ። ጽሑፍ ፤ ፎት ፤ መጣፍ ። ጸሓፊ ፡ (ፊት ፡ ፍያን ፡ ያት) የሚጥፍ ፡ ጣፊ ።

ወሰዓላት = የሰንበትንና ፣ የበዓሎችን ፣ ቀን ፣ ዐስበኽ ፣ አክብር ፣ (ዘሌ፳፫ ፣ ፪—፰) ። (፬) **አክብር ፣ አባከ ፣ ወእመከ** = አባትና ፣ እናትኽን ፣ አክብር ። (፭) **ኢትቀትል** = ንፍስ ፣ አትግደል ። (፮) **ኢትዝሙ** = አትሴስን ፤ አታመንዝር ። (፯) **ኢትስርቅ** = አት ስረቅ ፤ አትቀማ ። (፰) **ኢትኩን ፣ ስምዐ ፣ በሐሰት** = ባሰት ፣ አትመስክር ። (፱) **ኢ ትፍቲ ፣ ቤተ ፣ ካልእከ ፤ ወኢትፍቲ ፣ ብእሲተ ፣ ካልእከ ፤ ወኢገብሮ ፣ ወ አመቶ ፤ ወላሕሞ ፣ ወአድጎ ፤ ወኵሎ ፣ ዘካልእከ** = የባልንጀራኽን ፣ ቤት ፤ ሚ ስቱን ፤ ሎሌውን ፣ ገረዱን ፤ ላሙን ፣ አህያውን ፤ የርሱን ፣ ገንዘብ ፣ ኽሉ ፣ አትመኝ ፤ አትውደድ ።

(፲) **አፍቅር ፣ ቢጸከ ፣ ከመ ፣ ነፍስከ** = ባልንጀራኽን ፣ እንደ ፣ ራስኽ ፣ ውደድ ።

ክኔ ፣ በቀር ፣ ሌላ ፣ አምላክ ፣ አታምልክ ፤ ባሰት ፣ አትማል ፤ ሰንበት ፣ በዓላትን ፣ አክብር ፣ ያላቸው ፣ እኒኽ ፣ ሦስቱ ፣ እግዜርን ፣ በፍጹም ፣ ልቡና ፣ በመውደድ ፣ ይፈጸማሉ ። የቀሩት ፣ ስ ድስቱ ፣ ባልንጀራን ፣ በፍጹም ፣ ልቡና ፣ በመውደድ ፣ ይፈጸማሉ ፣ (ማቴ፳፪ ፣ ፴፯—፵) ።

(፳፱)

ያለቃ ፣ ዕንቈ ፣ ባሕርይ ፣ ግጥም ፣ ስላ፲ቱና ፣ ስለ ፣ ፯ቱ ፣ ቃላት ፤ ስለ ፣ መርገፎቹም ።

ከፀሠርቱ ፣ ቃላት ፣ መ፫መፈያው ፣ አንዱ ፣ በፍጹም ፣ ልቡና ፣ እግዜርን ፣ ውደዱ ።

ከመጽሐፍ ፣ ቃል ፣ ወጥቶ ፣ በስንበት ፣ የሠራ ፣ ፈፍት ፣ አያገኝም ፣ ከሰማይ ፣ መክራ ።

አባትና ፣ እናቱን ፣ በምግብ ፣ የማይረዳ ፣ ተበድሮ ፣ በልቶ ፣ አልከፈለም ፣ ዕዳ ።

አልታገሥ ፣ ብሎ ፣ የሰው ፣ ነፍስ ፣ ገዳይ ፣ በምድር ፣ ርስት ፣ ያጣል ፣ ስንኳን ፣ በሰማይ ።

ዝሙት ፣ የወደደ ፣ ሞቱን ፣ ማሰብ ፣ ትኖ ፣ እንስሳ ፣ ነው ፣ እንጂ ፣ ምን ፣ ይባላል ፣ ከኖ ።

የሰው ፣ ገንዘብ ፣ ሲሰርቅ ፣ ልቡ ፣ የማይሰጋ ፣ ሲገረፍ ፣ ይኖራል ፣ በእሳት ፣ አለንጋ ።

በሐሰት ፣ መስክሮ ፣ በሐሰት ፣ የማለ ፣ ክብርሃን ፣ ጨለማ ፣ ይሻለኛል ፣ አለ ።

ክሰው ፣ ሚስት ፣ የሚሄድ ፣ ጠላት ፣ ነው ፣ ለራሱ ፣ ወዲኽም ፣ በሥጋው ፣ ወዲኽም ፣ በነፍሱ ።

የሰውን ፣ ክብት ፣ አይኖ ፣ መውደድ ፣ መመኘት ፣ ከሾንኔ ፣ በቀር ፣ አያሰጥም ፣ ሀብት ።

መንግሥት ፣ ስማያት ፣ አትገኝም ፣ ነፍን ፣ ሰውን ፣ ካልወደዱ ፣ እንደ ፣ ራስ ፣ አድርን ።

ስለ ፣ ፯ቱ ፣ ቃላት ።

«ማቴ ፭ ፣ ፳፪ ፣ ፳፰ ፣ ፴፪ ፣ ፴፬ ፣ ፴፱ ፣ ፵፬» ስድስቱ ፣ ቃላትን ፣ ጽፎልናል ፣ ክፍሎ ፣ ወንድም ፣ ከማሳዘን ፣ ተጠበቁ ፣ ብሎ ።

ለኔ ፣ ትኹን ፣ ብሎ ፣ ሴትን ፣ መመልከት ፣ እጅግ ፣ ፍጹም ፣ በደል ፣ ታላቅ ፣ ኀጢአት ።

ሳትመንዝርበት ፣ ሚስቱን ፣ የሚፈታ ፣ ይፈረድበታል ፣ በላይኛው ፣ ቦታ ።

በውነት ፣ እንኳ ፣ ቢኾን ፣ መሐላ ፣ ይቅር ፤ ይሻለናልና ፣ የላይኛው ፣ ክብር ።

ክፉ ፣ ለሠራ ፣ ሰው ። በጎ ፣ የመለስ ፣ ዘላለም ፣ ይኖራል ፣ ጸጋ ፣ እንደ ፣ ለበሰ ።

ጠላትን ፣ ቢወዱ ፣ ይወዳል ፣ ፈጣሪ ፣ ርሱ ፣ ስለ ፣ ኾነ ፣ የኹሉ ፣ አሳዳሪ ።

የ፯ቱ ፣ ቃላት ፣ መርገፍ ።

ሌሎቹም ፣ መጻሕፍት ፣ ብለውናል ፣ ሲያዙ ፣ የምድሩን ፣ ትታችኹ ፣ የሰማዩን ፣ ያዙ ።

አኹን ፣ ምን ፣ አለና ፣ እንደ ፣ ሰው ፣ ደንቆሮ ፣ ለምድር ፣ የሚለውጥ ፣ የሰማዩን ፣ ኑሮ ።

ኹሉን ፣ ያታልላል ፣ የዚኽ ፣ ዓለም ፣ ተድላ ፣ ጥቂት ፣ ላይሰንብት ፣ ላይገኝ ፣ ለኹሎ ።

የሥጋ ፣ መክራ ፣ ይፈጸማል ፣ በድሜ ፤ ለንፍስ ፣ መክራ ፣ የለውም ፣ ፍጻሜ ።

ገሃነም ፣ ክገቡ ፣ አይገኝም ፣ ተስፋ ፤ ለትሉ ፣ እንቅልፍ ፣ የለው ፣ እሳቱም ፣ አይጠፋ ።

የኹዋላ ፣ መክራ ፣ አይወርድም ፣ ከራስ ፤ ደኽን ፣ እያሰበ ፣ ሰው ፣ ኹሉ ፣ ያልቅስ ።

ያለቃ ፣ ዕንቈ ፣ ባሕርይ ፣ ግጥም ፣ ይኽ ፣ የጣፍንው ፣ ብቻ ፣ አይደለም ፤ ከዚኽ ፣ ሌላ ፣ ደግ ሞ ፣ ስላምስቱ ፣ አዕማድ ፣ የገጠሙት ፣ ፲ ዕንቍ ፣ ግጥም ፣ አላቸው ፤ እኛ ፣ ግን ፣ አዕማዱን ፣ ስ ላልጣፍናቸው ፣ በዚኽ ፣ ምክንያት ፣ ትተነዋል ። ግጥማቸውንም ፣ ሰው ፣ ኹሉ ፣ ያውቀዋል ።



«ምስጢረ ፣ ምጽአት ፣ ወመንግሥተ ፣ ሰማይ» አኒ ፣ ውእቱ ፣ አልፋ ፣ ወ ዖ ፤ ቀዳማዊ ፣ ወደኃራዊ ፤ ርእስ ፣ ወማኅለቅት ። ወናሁ ፣ እመጽእ ፣ ፍጡ ነ ፤ ወዕሴትየኒ ፣ ምስሌየ ፤ ከመ ፣ እፍድዮ ፣ ለኵሉ ፣ በከመ ፣ ምግባሩ ፣ (ራእ፳፪ ፣ ፲፫ ፣ ፲፪ ። ፳፪፡፬ ። ፩ተሰ ፣ ፬ ፣ ፲፭—፲፰ ። ፭ ፣ ፩ ፣ ፪) ።

ግልስ ፡ በኃምስ ፡ የ ፤ በራብዕ ፡ በሳድስ ፡ አና ፡ ሀ ፡ አሉ ። ይኸ ፡ ክካዕብ ፡ እስከ ፡ ሳብዕ ፡ ያለ ፡ ቅጥል ፡ ኹሉ ፡ ስባርነትና ፡ ዐንካስነት ፡ ሳይቀር ፡ በነዚኽ ፡ ፈንታ ፡ የገባ ፡ ነው ። ለድኅና ፡ ለቅዳሴ ፡ ዜማ ፡ ለምልክቱ ፡ ሥረይ ፡ እንዳለው ፤ ለፊደልም ፡ ድምጥ ፡ ለጠባዩና ፡ ለቅጥዩ ፡ ሥረዮቹ ፡ እነዚኽ ፡ ናቸው ፤ ቅጥል ፡ ኹሉ ፡ ምልክት ፡ ኹኖ ፡ የነዚኽን ፡ ያራቱን ፡ ጠባይ ፡ ያሳያል ፤ ጠባያቸውም ፡ ይኽ ፡ ነው ። የወ ፡ ጠባይ ፡ ራሱን ፡ እየጐረደ ፡ ሳድስና ፡ ግእዝ ፡ ይኾን ፡ የነበረውን ፡ በኹዋላው ፡ ያለውን ፡ ፊደል ፡ ክዕብና ፡ ሳብዕ ፡ ግድረግ ፡ ነው ። (ማስረጃ) **ፈነወ ፡** ብሎ ፡ **ይ ፈንው ፡ ይፈንው ፡** በማለት ፡ ፈንታ ፡ **ይፈኑ ፡ ይፈኑ ፤ ተፈነወ ፡** ብሎ ፡ **ይትፈነ ው ፡ ይትፈነው ፡** በማለት ፡ ፈንታ ፡ **ይትፈኖ ፡ ይትፈኖ ።** ሐዊር ፡ ቀዊም ፡ ብሎ ፡ **ሐወረ ፡ ቀወመ ፡** በማለት ፡ ፈንታ ፡ **ሐረ ፡ ቆመ ፤ የሐውር ፡ ይቀውም ፡** ብሎ ፡ ግልባዩን ፡ **ይሕውር ፡ ይቅውም ፡** በማለት ፡ ፈንታ ፡ **ይሑር ፡ ይቁም ፤** የመስለው ፡ ኹሉ ። የወዲያኛው ፡ ትግሬም ፤ **ቀርቡ ፡ መጽኡ ፡ ፈርሀ ፡ ደንገፁ ፡** ሲል ፤ **ቀርበው ፡ መጽአው ፡ ፈርሀው ፡ ደንገፀው ፡** ይላል ። ዐማርኛም ፤ ግእዙ ፡ **ባረከ ፡ ቀደሰ ፡ አ ኀዘ ፡ ገሰሰ ፡** የሚለውን ፤ ባረከው ፡ ቀደሰው ፡ ያዘው ፡ ዳሰሰው ፡ እያለ ፡ በው ፡ ይዘረዝራል ፤ ይኽም ፡ የትግሬና ፡ ያማርኛ ፡ አካሄድ ፡ የጥንታዊው ፡ ያሮጌው ፡ ግእዝ ፡ ነው ፡ ይባላል ። ፊደል ፡ ኹሉ ፡ ወ ፡ በፊቱ ፡ ከሌለ ፡ አለወ ፡ መሪነት ፡ ብቻውን ፡ ካዕብና ፡ ሳብዕ ፡ ሊኾን ፡ አይችልም ። የወ ፡ ጠባይ ፡ በዕብራይስጥም ፡ እንደዚኽ ፡ ነው ። ዋ ፡ ደግሞ ፡ ብቻውን ፡ ለራብዕ ፡ ዲቃሎች ፡ ለሸቪቱ ፡ ሀመል ፡ ይኾናል ፤ ይኽንን ፡ ኹዋላ ፡ በቦታው ፡ እናመጣዋለን ። የየ ፡ ጠባይ ፡ ደግሞ ፡ እንደዚኽ ፡ ነው ፤ ራሱን ፡ እየጐረደ ፡ ሳድስና ፡ ግእዝ ፡ ይኾን ፡ የነበረውን ፡ በካልኣይና ፡ በሣልሳይ ፡ አንቀጽ ፡ ግልስ ፤ በቀዳማይ ፡ ኃምስ ፡ ያደርጋል ። (ማስረጃ) **ሠዪም ፡ ገዪሥ ፡** ብሎ ፤ **ሠየመ ፡ ገየሠ ፡** በማለት ፡ ፈንታ ፡ **ሚመ ፡ ጌሠ ፡ ይሚም ፡ ይጊሥ ።** ሠነ የ ፡ ብሎ ፡ **ይሜንይ ፡ ይሠንይ ፡** በማለት ፡ ፈንታ ፡ **ይሜኒ ፡ ይሠኒ ፤** የመስለው ፡ ኹሉ ። **ይሜኒ ፡** ባለውም ፡ የ ፡ አለበት ፤ **ይሠየንይ ፡** እንደ ፡ ግለት ፡ ነው ። ፊደል ፡ ኹሉ ፡ የ ፡ በፊቱ ፡ ከሌለ ፡ አለየ ፡ መሪነት ፡ ብቻውን ፡ ግልስና ፡ ኃምስ ፡ ሊኾን ፡ አይችልም ። «በንኡስ ፡ አንቀጽ ፡ ግን ፡ ያውም ፡ በቀተለ ፡ ቤት ፡ ግልስ ፡ ይኾን ፡ የነበረውን ፡ ሳድስ ፡ ያደርጋል ፤ (ማስረጃ) **ሐቅይ ፡ ሰቅይ ፡ ወድይ ፡ ፈድይ ፤** የመስለው ፡ ኹሉ» ። አና ፡ ሀ ፡ ደግሞ ፡ ጠባያቸው ፡ አንድ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ኹለቱ ፡ ስላንድ ፡ ይቈጠራሉ ፤ ጠባያቸውም ፡ በቀዳማይና ፡ በሣልሳይ ፡ አንቀጽ ፡ ግእዝ ፡ ይኾን ፡ የነበረውን ፡ ሳድስ ፡ ግድረግ ፤ ሳድስ ፡ ይኾን ፡ የነበረውን ፡ ራብዕ ፡ ግድረግ ፡ ነው ። (ማስረጃ) **መጺእ ፡** ብሎ ፡ **መጸአ ፡ ይምጸእ ፡** በማለት ፡ ፈንታ ፡ **መጽአ ፡ ይምጻእ ፤ በልዐ ፡ ይብላዕ ፤ ፈርሀ ፡ ይፍራሀ ፤ ነጽሐ ፡ ይንጻሕ ፤ በ ዝኀ ፡ ይብዚኅ ፤** የመስለው ፡ ኹሉ ። ዐማርኛውንም ፡ መጣ ፡ በላ ፡ ፈራ ፡ ነጣ ፡ በዛ ፤ የሚያሰ ኙት ፡ አና ፡ ሀ(ዐ ፡ ሐ ፡ ኀ) እንደ ፡ ኾኑ ፡ አስተውል ። አ ፡ ከሀ ፡ ተለይቶ ፡ የማስደረግ ፡ ልማድ ፡

(፴)

መ ቅ ድ መ ፡ ፊ ደ ል ፡ ግ ል ስ ።

ዓዲ ፡ ናቄርብ ፡ ወንሜልስ ፡ ለከ ፡ ዘንተ ፡ ፊደለ ፡ አምኃ ፡ ጥበብ ፡ ወጋዳ ፤ አ አንበሳ ፡ ዘእምነገደ ፡ ይሁዳ ፤ ወዕጎለ ፡ ዳዊት ፡ አንበሳ ፡ መዋኤ ፡ አራዊት ፡ ወእንስሳ ፤ ጎይለ ፡ ሥላሴ ፡ ንጉሥ ፡ ነዊኅ ፡ መንፈስ ፡ ወመምህረ ፡ ሕግ ፡ ሐዲስ ፤ ዘየሐውር ፡ እም ጎይል ፡ ውስተ ፡ ጎይል ፡ እንዘ ፡ ይመርሖ ፡ ልዑል ፤ እስመ ፡ አ ንተ ፡ ውእቱ ፡ በሱረ ፡ ስም ፡ ዐቢይ ፡ ወዘርዐ ፡ መንግሥት ፡ ሠ ናይ ፤ ዘወድቀ ፡ ውስተ ፡ ምድር ፡ ሠናይት ፡ እግዝእተ ፡ ዐውርቱ ፡ ምእት ፤ ወኅጠተ ፡ ሥርናይ ፡ ቡሩክ ፡ ሥጋሁ ፡ ለወልደ ፡ አምላክ ፤ እሳታዊ ፡ መብልዕ ፡ ርሱን ፡ ወመስቴ ፡ መኰንን ።

የቮኛ ፡ ፊደል ፡ መቅድም ።

ባገራችንና ፡ በክፍላችን ፡ በመሬታችን ፡ ውስጥ ፡ የታወቀና ፡ ያልታወቀ ፤ የተገኘና ፡ ያልተገኘ ፤ ገና ፡ ሊፈለግ ፡ የሚገባው ፡ ብዙ ፡ ዐይነት ፡ ገንዘብ ፡ ዐሳባና ፡ ድልብ ፡ እንዳለበት ፤ በቋንቋችንም ፡ ውስጥ ፡ ጉባኤው ፡ ሰፍቶ ፡ ተማሪው ፡ ተንጋግቶ ፡ በጥፊትና ፡ በጥያቄ ፡ እየቈፈረ ፡ እየመረመረ ፡ ይፍረጥ ፡ ይገለጥ ፡ የሚለው ፡ ስላጣ ፤ እንደንቍላል ፡ ድፍን ፡ እንደ ፡ ባር ፡ ማሽላ ፡ ሽፍን ፡ ኹኖ ፡ ባለመታወቅ ፡ እንደሳት ፡ ተዳፍኖ ፡ የሚኖር ፡ ብዙ ፡ ትምርት ፡ አለ ። ኹሉን ፡ ቈፍሮ ፡ ለማውጣት ፡ ብዙ ፡ ሠራተኛ ፡ ዐጋዥ ፡ ረዳት ፡ ታላላቅ ፡ መማሪያ ፡ የተማሪ ፡ ቤት ፡ ስለሌለ ፤ ከምሉ ፡ በክፍሉ ፡ ከብዙ ፡ በጥቂቱ ፡ ያየንውን ፡ የሰማነውን ፡ ጎሊናችን ፡ በውቀት ፡ እኛችን ፡ በጥፊት ፡ የደረሰበትን ፡ መርምረንና ፡ ተመራምረን ፡ ዘግነን ፡ ቈንጥረን ፡ የፊደልን ፡ ጠባይ ፡ የድምጡንና ፡ የቅጥሉን ፡ ነገር ፡ እንጥፋለን ፤ እኩሉንም ፡ ካኹን ፡ አስቀድሞ ፡ ባለፉት ፡ ክፍሎች ፡ በታችኞቹ ፡ ጥፈነዋል ፤ የቀረውም ፡ ዐዲስ ፡ መንገድና ፡ እንግዳ ፡ ልማድ ፡ በታላቁ ፡ ግስ ፡ ተጥቅል ። የግእዝና ፡ ያማርኛ ፡ የሌላውም ፡ የሴም ፡ ቋንቋ ፡ ዐመሎች ፡ ወይም ፡ ዋየሎች ፡ ያናቸው ፤ ወና ፡ የ ፡ አ(ዐ)ና ፡ ሀ(ሐኀ) ፤ እነዚኽ ፡ አራቱ ፡ ያሉበት ፡ ግስ ፡ ቤቱን ፡ ሳይለቅ ፡ ድምጥና ፡ አካሄድ ፡ ይለውጣል ። ከአ ፡ እስከ ፡ ፐ ፡ ባሉ ፡ በፊደላት ፡ ኹሉ ፡ በካዕብ ፡ በሳብዕ ፡ ወ ፤ በ

ይ ፣ ክዕብ ፣ ተደርቧል ። የድምጣቸው ፣ ስልት ፣ እንደ ፣ በቅሎ ፣ እንደ ፣ ፈናፍንት ፣ ዐንጉል ፣ ከ ኹሉ ፣ አለኹ ፣ የሚል ፣ ዲቃላ ፣ መኾን ፣ ስለዚኽ ፣ ነው ። እንደዚኽ ፣ ያለው ፣ ድምጥ ፣ በጽርእ ና ፣ በሮማይስጥም ፣ ዲፍቶንግ ፣ ይባላል ፤ ክዑብ ፣ ድምዕ ፣ ምንትው ፣ ድምዕ ፣ ማለት ፣ ነው ።

ቮኛም ፣ በጓኋኳቋ ፣ አንጻር ፣ ለሚገኙ ፤ ክቢ ፣ እስክ ፣ ታና ፣ እስክ ፣ ጅ ፣ ላሉት ፣ እነጓኋኳቋ ም ፣ ሳይቀሩ ፣ ለመላው ፣ ለጅቮቱ ፣ ዲቃሎች ፣ ለራብዖች ፣ ብቻ ፣ ፍጹም ፣ ዐመላቸው ፣ ወይም ፣ ዋየላቸው ፣ ዋ ፣ ነው ፤ ቅጥላቸው ፣ ኹሉ ፣ ህየንተ ፣ ዋ ፣ ኹኖ ፣ በዋ ፣ ፈንታ ፣ ገብቷል ። ዋ ፣ ደ ግሞ ፣ ቅጥሉ ፣ የአ ፣ ምሳሌ ፣ ስለ ፣ ኽነ ፣ **ዉአ** ፣ ተብሎ ፣ ስለ ፣ ኹለት ፣ ዋየል ፣ ይቁጠሬል ። ቅጥላቸው ፣ ቀርቶ ፣ በዝርዝር ፣ ፊደል ፣ ሲጣፉ ፣ ግን ፣ ቢታቹ ፣ የነበሩት ፣ **በኡ ፣ ቱኡ ፣ ቹ ኡ** ፣ ያሰኛሉ ፤ ይኽነን ፣ ደግሞ ፣ ዘርዝሮ ፣ ሲጥፉት ፣ **በዉአ ፣ ተዉአ ፣ ቮዉአ** ፣ ያሰኛ ልና ፤ ቅጥላቸው ፣ እንደ ፣ ጓኋኳቋ ፣ በፀ ፣ ወገን ፣ መኾኑ ፣ ስለዚኽ ፣ ነው ። ልብ ፤ ልቢ ፣ ዐስቢ ል ፣ የተባለውም ፣ ቃል ፣ በዝርዝር ፣ ሲጣፍ ፤ ዐስበ ፣ አል ፣ አለ ፣ ወይም ፣ ዐስበዎ ፣ አል ፣ ያሰኛ ል ፤ አል ፣ አለ ፣ ማለት ፣ ህለወ ፣ ህሎ ፣ ካለው ፣ የወጣ ፣ ነው ። አልና ፣ ዐሰበ ፣ በየራሳቸው ፣ የቆ ሙ ፣ ፀ ልዩ ፣ ቃሎች ፣ ሊኾኑ ፣ በመካከላቸው ፣ ኹለቱ ፣ ዋየሎች ፣ **(ዉአ)** ገጥመው ፣ ተባብረ ው ፣ ምንታዊያቸውን ፣ ስላጠፉት ፣ ፩ ቃልና ፣ ፩ ጎርመት ፣ ኹነው ፣ ዐስቢል ፣ ተብለው ፣ በተዋሕ ዶ ፣ ይጠፋሉ ፤ ምስጢራቸውም ፣ እንዳይለያይ ፣ እንዳይቀላቀል ፣ ቢ ፣ ዘበኛ ፣ ኹኖ ፣ ይጠብቃ ል ። በዚኽ ፣ ባንዱ ፣ ራብዕ ፣ የኹሉ ፣ አካሄድ ፣ ይታወቃልና ፤ ኹሉን ፣ መናገር ፣ አያሻም ። (ተ ረት) አንድ ፣ ዐረግ ፣ ቢስቡ ፣ ዱር ፣ ይሰበስቡ ። የግእዝ ፣ ዐመል ፣ ከሮማይስጥ ፣ ዋየል ፣ መ ግጠሙና ፣ መተባበሩም ፣ ከዚኽ ፣ ቀጥሎ ፣ እንደ ፣ ተጣፈው ፣ ነው ። **ዉ—ሀ** ፤ **ዬ—i** ፤ **አ—ል** ፤ **ዬ—é** ፤ **ህ—e** ፤ **ዎ—o** ። የኤውሮፖች ፣ ፊደል ፣ ፭፯ ፣ ዘር ፣ እንደ ፣ ኽነ ፣ የኛም ፣ በዚኹ ፣ ልክ ፣ ፭፯ ፣ ዘር ፣ ነውና ፤ ግእዝ ፣ ግእዙን ፣ ከነድቦቹ ፣ በነዚኽ ፣ በ ኽቱ ፣ ዋየል ፣ ሲያስኬዱት ፣ በዝርዝር ፣ አጣጣፍ ፣ ፪፻፫ ፣ ይኽን ፣ የነበረው ፣ ተጠቅልሎ ፣ ፬፯ ፣ ይኽናል ። ድቦቦች ፣ ያልናቸው ፣ ፲፭ ፣ ናቸው ፤ ፬ቱ ፣ ዲቃሎችና ፣ ፯ቱ ፣ ዐማርኞች ። ፪፻፫ ፣ ካ ልነውም ፣ ፭፫ቱ ፣ ዐማርኛ ፣ ነው ። አኃዝ ፣ ግን ፣ በዚኽ ፣ አካሄድ ፣ ለመቀልጠፍ ፣ ያው ፣ የተለ መደው ፣ ዓለም ፣ ኹሉ ፣ የተቀበለው ፣ ባለዘሮው ፣ (1—10) ህንዳዊው ፣ ቍጥር ፣ ይሻላል ። ይ ኽነንም ፣ አኃዝ ፣ ዐረቦች ፣ ማእከል ፣ ኹነው ፣ ከህንድ ፣ ወደ ፣ ኤውሮፓ ፣ ስላሳለፉት ፤ አካሄዱ ም ፣ እንዳረብ ፣ ፊደል ፣ ከቀኝ ፣ ወደ ፣ ግራ ፣ ስለ ፣ ኽነ ፣ ኤውሮፖች ፣ ዐረብ ፣ ይሉታል ፤ ገንዘ ብነቱ ፣ ግን ፣ የህንዶች ፣ ነው ፤ ያወጣውም ፣ አንድ ፣ ነጋዲ ፣ ነው ፣ ይባላል ። ዳግመኛም ፣ በጅ ፣ መኪና ፣ የሚሰካው ፣ የኤውሮፖች ፣ ፊደል ፤ የፊደሉ ፣ እጅታ ፣ ጣቶች ፣ የሚያርፉበት ፣ ክስግው ና ፣ አውታሩ ፣ ፵፪ና ፣ ፵፫ ፣ ሲኾን ፤ ፊደሎ ፣ ከናኃዙና ፣ ከነጓዙ ፣ ከነይዘቱ ፣ ከነምልክቱ ፣ ፹፬ ፣ ወይም ፣ ፹፯ ፣ ነውና ፤ የኛም ፣ አኃዝ ፣ ካንድ ፣ እስክ ፣ አልፍ ፣ (፩—፼) ያለው ፣ ኻያው ፣ ቅን ጣት ፣ ፊደል ፣ በዚያ ፣ ባሥሩ ፣ በህንዳዊው ፣ ላይ ፣ ቢጨመር ፣ ዐታው ፣ ይቱርፋል ፣ እንጂ ፣ አይ ጠበውም ። ይኽም ፣ ኹሉ ፣ ኹኖ ፣ የግእዝና ፣ ያማርኛ ፣ ፊደል ፣ ከነጓዙና ፣ ከነጭፍራው ፣ ከነ ምልክቱ ፣ ኹሉን ፣ ባንዳይቅር ፣ ስብስቦ ፣ ሲቈጥሩት ፣ ገና ፣ ፹፱ ፣ ነውና ፤ ፹፱ና ፣ ፹፯ ፣ ለማድ ረግ ፤ አስቀድመን ፣ በንጥብ ፣ አገባብ ፣ እንደ ጐተናገርን ፤ ከፈረንጆቹ ፣ ምልክት ፣ አሻሽሎ ፣ መር ጠ ፣ ፩ ፣ ወይም ፣ ፯ ፣ ያኽል ፣ ተውሳክ ፣ መጨመርና ፣ ማግባት ፣ ያስፈልጋል ። የዚኽ ፣ መ

ሊኽን ፣ ግን ፤ በትንቢት ፣ በዘንድ ፣ ራሱን ፣ እንደ ፣ ወና ፣ እንደ ፣ የ ፣ ይጐርዳል ። (ማስረሻ) **አ ቅተለ** ፣ ብሎ ፤ **የአ** ፣ በማለት ፣ ፈንታ ፣ **ያቀትል ፣ ያቅትል** ። **አቅተልከ** ፣ ብሎ ፤ **ተ አ** ፣ በማለት ፣ ፈንታ ፣ **ታቀትል ፤ ታቅትል** ፣ የመስለው ፣ ኹሉ ። «ባማርኛውም ፣ እንደዚ ኽ ፣ ነው ፤ ዐዲሳበባ ፤ ባዲ ፤ ክዲ ፤ ላዲ ፤ ስላዲ ፤ ወዳዲ ፤ ዐዲሳበባን ። አባት ፤ ባባት ፤ ክባት ፤ ላባት ፤ ስላባት ፤ ወዳባት ፣ እያለ ፣ ዐመልኔቱን ፣ መደብ ፣ አድርጎ ፣ ጐራጅነቱን ፣ ያሳያል ። ፪ኛም ፣ ሳድስ ፣ ኹኖ ፣ አገባብ ፣ ሲጣነው ፣ ተበገብበዘ ፣ ሳይጣፍና ፣ ሳይነገር ፣ ተውጦ ፣ ተጐርዶ ፣ ይቀራ ል ። እናት ፤ በናት ፤ ክናት ፤ ለናት ፤ ወደናት ። እግዜር ፤ በግዜር ፤ ከ ፣ ለ ፣ ስለ ፣ ወደግዜር ። እጅ ፤ በጅ ፤ ከ ፣ ለ ፣ ስለ ፣ ወደጅ ፤ የመስለው ፣ ኹሉ» ።(፩) ፊደል ፣ ኹሉ ፣ እና ፣ ሀ ፣ በፊቱ ፣ ክሌሉ ፣ ብቻው ን ፣ ሳድስና ፣ ራብዕ ፣ አይኾንም ። የግእዝና ፣ ያማርኛ ፣ አካሄድ ፣ ዐዋጁና ፣ ሕጉ ፣ እንዲኽ ፣ ባ ራት ፣ ዐመል ፣ የቆመና ፣ የተወሰነ ፣ ስለ ፣ ኽነ ፤ የወ ፣ ካዕብና ፣ ሳብዕ ፣ **ዉ ፣ ዎ** ፤ የየ ፣ ግል ስና ፣ ኃምስ ፣ **ዬ ፣ ዬ** ፤ የአ ፣ ራብዕ ፣ **አ** ፤ የሀ ፣ ሳድስ ፣ **ህ** ፤ እነዚኽ ፣ ፮ቱ ፣ ለየራሳቸው ፣ በመነሻና ፣ በመድረሻ ፣ በቁም ፣ ቀሪዎች ፣ እየኾኑ ፣ ራሳቸውን ፣ ችለው ፣ ግእዝን ፣ ፊደል ፣ ኹ ሉ ፣ በጅ ፣ መኪና ፣ እንደደሳቸው ፣ ድምጥ ፣ ማስኬድ ፣ ይችላሉ ። ድምጣቸውና ፣ ድምጥንታቸ ውም ፣ ክሮማይስጥ ፣ ዋየል ፣ ከ፮ቱ ፣ ኹሉ ፣ ይስማማል ። ዋየል ፣ የላቲን ፣ ቃል ፣ ነው ፤ የ ግእዝም ፣ ሊኾን ፣ ይቻላል ። መላው ፣ የአ ፣ ቤት ፣ ፊደል ፣ ፮ቱ ፣ ዐይነት ፣ ኹሉ ፣ በሮማይስጥ ፣ ዋየል ፣ ይባላል ። (ኹለቱ ፣ የና ፣ ሄ ፣ ናቸው) ። ፍችውንም ፤ ድምዕ ፣ ወሃቤ ፣ ድምዕ ፣ ይሉታ ል ፤ ድምዕ ፣ ለራሱ ፣ ወሃቢ ፣ ለሌላው ። እኛ ፣ ባገባብ ፣ ትምርት ፣ ግእዝ ፣ ዐመል ፣ ደጊመ ፣ ቃ ል ፣ የምንላቸውን ፣ እሊኽን ፣ ፫ቱን ፣ ያፈታውያን ፤ ኮንሶን ፣ ዋየል ፣ ዱብል ፣ ይሏቸዋል ። እሊ ኹም ፣ **ከነሰ ፤ ዋይ ፣ ወይል ፣ ወይለየ ፤ ደበለ** ፣ ከማለት ፣ ጋራ ፣ አንድ ፣ ናቸው ፤ በን ባብ ፣ በምስጢር ፣ ይገጥማሉ ፤ እንዲያውም ፣ በጭራሽ ፣ ከነዚኽ ፣ የወጡ ፣ ይመስላሉ ።

ዳግመኛም ፤ ያራቱ ፣ ዲቃሎች ፣ የንጐሳኰቄ ፣ ቅጥል ፣ ኹሉም ፣ መንታ ፣ መንታ ፣ ዐይነት ፣ መኾኑ ፤ ዋየሎቻቸው ፣ ፪፪ ፣ ስለ ፣ ኽነ ፣ ነው ። የግእዛቸውም ፣ ቅጥል ፣ ቀለበቱ ፣ እንደ ፣ ሎ ፣ መኾኑ ፣ ፪ ወ ፣ ያሳያል ፤ ህየንተ ፣ ዉወ ፣ ነው ። ይኽም ፤ **ገዉወ—ገ** ፤ **ጎዉወ—ጎ** ፤ **ከዉወ—ኩ** ፤ **ቀዉወ—ቈ** ፤ ማለቱን ፣ ያሳያል ። የሎም ፣ አጣጣፍ ፣ እንደ ፣ ኦቦደና ፣ እን ደ ፣ ዘሐጠ ፣ እንደ ፣ ከጸጸሶ ፣ ወንካሳ ፣ ቈራጣ ፣ ሊኽን ፣ እንጂ ፤ እንደ ፣ ጐጐኰቄ ፣ ቅጥላምና ፣ ቀለበታም ፣ ሊኽን ፣ ባልተገባውም ፤ ድምጡና ፣ ቅጥሉ ፣ አልተስማማም ፤ ከሳብዖች ፣ ሕግ ፣ ወጥ ቶ ፣ እንደነኮ ፣ ዲቃል ፣ ባለ፪ ፣ ዋየል ፣ ኹሉዋል ፤ ስለዚኽ ፣ በገርዝገር ፣ ሲጣፍ ፣ **ሉወ ፣ ለዉ ወ** ፣ ያሰኛል ። መንታ ፣ ዐይነት ፣ ያልነውም ፤ **ገወዬ—ጊ** ፤ **ገዉአ—ጓ** ፤ **ገወዬ—ጌ** ፤ **ገ ወህ—ጊ** ፤ እያለ ፣ መንታውን ፣ ዋየል ፣ በመንታ ፣ ቅጥል ፣ ያሳያል ። ምንም ፣ የቅጥይን ፣ ጠባ ይ ፣ ለማስረዳት ፣ መንታ ፣ ዋየል ፣ ብንል ፤ በዚኽ ፣ ፊደል ፣ ውስጥ ፣ ካንዳንድ ፣ በቀር ፣ ኹሉት ፣ ዋየል ፣ የለም ፤ ወ ፣ በየቅጥላቸው ፣ ስላለ ፣ ተውጦና ፣ ተጐርዶ ፣ ይቀራል ። ድምጣቸው ፣ ግን ፣ ከታች ፣ አስቀድመን ፣ እንደ ፣ ተናገርን ፣ (ክፍ ፣ ፯) በቅጥሉና ፣ በዋየሉ ፣ መጠን ፣ ዕጥፍ ፣ ድር ብ ፣ ነው ፤ በግእዛቸው ፣ ላይ ፣ ካዕብና ፣ ሳብዕ ፣ እንደ ፣ ተደረቡ ፤ በቀሩትም ፣ ባራት ፣ ባራቱ ፣ ላ

(፩) የ ፣ ደግሞ ፣ በደፊንቱ ፣ አገባብ ፣ ሲጣነው ፣ እንደዚኽ ፣ ነው ። የኢትዮጵያ ፣ መንግሥት ፤ በ ኢት ፣ ከኢት ፣ ለኢት ፣ ስለኢት ፣ ወደኢት ፣ እስከኢት ፣ ይላል ፣ እንጂ ፤ በየኢት ፣ ከየኢት ፣ ስለ ፣ የኢት ፣ ወደ ፣ የኢት ፣ እስክ ፣ የኢትዮጵያ ፣ መንግሥት፣ አይልም ፤ ቢልም ፣ ጸያፍ ፣ ነው ።

ቅድም ፡ ሐሳብ ፡ ምኞቱና ፡ ጣሩ ፡ ፍሬ ፡ ንገሩ ፤ ክፈደላት ፡ በቀር ፡ የመኪናው ፡ ሕግ ፡ ሥርዐቱ ና ፡ ደንቡ ፡ ሳይለወጥ ፡ በዚያው ፡ በነፍጅ ፡ መኪና ፡ የኛን ፡ ፊደሎች ፡ ጀዘቱን ፡ በያንዳንዱ ፡ ካ ስማ ፡ እያገቡ ፡ ለመጣፍና ፡ ለማተም ፡ ነው ። ይኸን ፡ ጥሩ ፡ ሐሳብ ፡ ክባለመኪናች ፡ ተሰማም ቶ ፡ በጥሩ ፡ ሥራ ፡ ቢከተሉት ፡ ከዚያው ፡ ከተቁረጠው ፡ ከመኪናው ፡ ዋጋ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ክሳራ ፡ የድክም ፡ ሥራ ፡ የለበትም ። የፊደሉም ፡ ትምርት ፡ የኤውሮፓን ፡ ፊደል ፡ ላዩ ፡ ልጆች ፡ ፊደሉ ን ፡ ብቻ ፡ መላልሶ ፡ በማየት ፡ ይፈጸማል ፤ ርሱው ፡ ራሱ ፡ ፊደሉ ፡ ቅናት ፡ ምቀኝነት ፡ የሌለው ፡ መምርና ፡ መጣፍ ፡ ስለ ፡ ኸነ ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ አያሻም ።

(፴፩)

ፊደል ፡ ማልስ ፡ ጸያሔ ፡ ፍኖት ፡ መብእስ ።

ደኛ ፡ ፊደል ፤ ሐዲስ ፡ መንገድ ፡ በጥፊትና ፡ በጅ ፡ መኪና ፡ ግእዝ ፡ ክማርኛ ፡ የሚያስኬድ ።

ዐመሎች ፡ ወይም ፫ ዋየሎች ።

(ግእዝ)	(ካዕብ) ዉ	(ማልስ) ዩ	(ራብዕ) ኣ ፤ ዋ	(ኃምስ) ዬ	(ሳድስ) ህ	(ሳብዕ) ዎ
አ	አዉ–አ·	አዩ–አ፡	አ(ዋ)	አዬ–አ	አህ–እ	አዎ–አ
ⳓ	በዉ–በ·	በዩ–ቢ፡	በአ–ባ በዋ-ቧ	በዬ–ቤ	በህ–·ብ	በዎ–ቦ
ገ	ገዉ–ጉ·	ገዩ–ጊ፡	ገአ–ጋ	ገዬ–ጌ	ገህ–ግ	ገዎ–ጎ
ጐ	—	ጐዩ–ጒ፡	ጐዋ–ጓ	ጐዬ–ጔ	ጐህ–ጒ·	—
ደ	ደዉ–ዱ·	ደዩ–ዲ፡	ደአ–ዳ ደዋ-ዷ	ደዬ–ዴ	ደህ–ድ·	ደዎ–ዶ
ጀ	ጀዉ–ጁ·	ጀዩ–ጂ፡	ጀአ–ጃ ጀዋ-ጇ	ጀዬ–ጄ	ጀህ–ጅ·	ጀዎ–ጆ
ሀ	ሀዉ–ሁ·	ሀዩ–ሂ፡	ሀአ–ሃ	ሀዬ–ሄ	ሀ	ሀዎ–ሆ
ወ	ዉ	ወዩ–ዊ፡	ወአ–ዋ	ወዬ–ዌ	ወህ–ው·	ዎ
ዘ	ዘዉ–ዙ·	ዘዩ–ዚ፡	ዘአ–ዛ ዘዋ-ዟ	ዘዬ–ዜ	ዘህ–ዝ	ዘዎ–ዞ
ገ	ገፐዉ–ገፑ	ገፐዩ–ገፒ፡	ገፐአ–ገፓ ገፐዋ-ገፗ	ገፐዬ–ገፔ	ገፐህ–ገፕ	ገፐዎ–ገፖ

ሐ	ሐዉ–ሑ·	ሐዩ–ሒ፡	ሐአ–ሓ	ሐዬ–ሔ	ሐህ–ሕ	ሐዎ–ሖ
ኀ	ኀዉ–ኁ·	ኀዩ–ኂ፡	ኀአ–ኃ	ኀዬ–ኄ	ኀህ–ኅ	ኀዎ–ኆ
ኀሠ	—	ኀሠዩ–ኀሢ፡	ኀሠዋ–ኀሣ	ኀሠዬ–ኀሤ	ኀሠህ–ኀሥ·	—
ጠ	ጠዉ–ጡ·	ጠዩ–ጢ፡	ጠአ–ጣ ጠዋ-ጧ	ጠዬ–ጤ	ጠህ–ጥ	ጠዎ–ጦ
ጨ	ጨ ዉ–ጩ·	ጨ ዩ–ጪ፡	ጨ አ–ጫ ጨ ዋ-ጯ	ጨ ዬ–ጬ	ጨ ህ–ጭ	ጨ ዎ–ጮ
የ	የዉ–ዩ	ዩ	የአ–ያ	ዬ	የህ–ይ	የዎ–ዮ·
ከ	ከዉ–ኩ·	ከዩ–ኪ፡	ከአ–ካ	ከዬ–ኬ	ከህ–ክ	ከዎ–ኮ
ኸ	ኸዉ–ኹ·	ኸዩ–ኺ፡	ኸአ–ኻ ኸዋ-኿	ኸዬ–ኼ	ኸህ–ኽ	ኸዎ–ኾ
ኰ	—	ኰዩ–ኰ፡	ኰዋ–ኳ	ኰዬ–ኲ	ኰህ–ኵ·	—
ለ	ለዉ–ሉ·	ለዩ–ሊ፡	ለአ–ላ ለዋ-ሏ	ለዬ–ሌ	ለህ–ል	ለዎ–ሎ
መ	መዉ–መ·	መዩ–ሚ፡	መአ–ማ መዋ-ሟ	መዬ–ሜ	መህ–ም	መዎ–ሞ
ነ	ነዉ–ኑ·	ነዩ–ኒ፡	ነአ–ና ነዋ-ኗ	ነዬ–ኔ	ነህ–ን	ነዎ–ኖ
ኘ	ኘዉ–ኙ·	ኘዩ–ኚ፡	ኘአ–ኛ ኘዋ-ኟ	ኘዬ–ኜ	ኘህ–ኝ	ኘዎ–ኞ
ሠ	ሠዉ–ሡ·	ሠዩ–ሢ፡	ሠአ–ሣ	ሠዬ–ሤ	ሠህ–ሥ	ሠዎ–ሦ
ዐ	ዐዉ–ዑ·	ዐዩ–ዒ፡	ዐአ–ዓ	ዐዬ–ዔ	ዐህ–ዕ	ዐዎ–ዖ
ፈ	ፈዉ–ፉ·	ፈዩ–ፊ፡	ፈአ–ፋ ፈዋ-ፏ	ፈዬ–ፌ	ፈህ–ፍ	ፈዎ –ፎ
ጸ	ጸዉ–ጹ·	ጸዩ–ጺ፡	ጸአ–ጻ ጸዋ-ጿ	ጸዬ–ጼ	ጸህ–ጽ·	ጸዎ–ጾ
ፀ	ፀዉ–ፁ·	ፀዩ–ፂ፡	ፀአ–ፃ	ፀዬ–ፄ	ፀህ–ፅ	ፀዎ–ፆ
ቀ	ቀዉ–ቁ·	ቀዩ–ቂ፡	ቀአ–ቃ	ቀዬ–ቄ	ቀህ–ቅ	ቀዎ–ቆ
ቈ	—	ቈዩ–ቈ፡	ቈዋ–ቋ	ቈዬ–ቌ	ቈህ–ቍ·	—

ረ	ረዉ--ሩ	ረዩ--ሪ	ረአ--ራ ረዋ--ሯ	ረዬ--ሬ	ረህ--ር	ረዎ--ሮ
ሰ	ሰዉ--ሱ	ሰዩ--ሲ	ሰአ--ሳ ሰዋ--ሷ	ሰዬ--ሴ	ሰህ--ስ	ሰዎ--ሶ
ሸ	ሸዉ--ሹ	ሸዩ--ሺ	ሸአ--ሻ ሸዋ--ሿ	ሸዬ--ሼ	ሸህ--ሽ	ሸዎ--ሾ
ተ	ተዉ--ቱ	ተዩ--ቲ	ተአ--ታ ተዋ--ቷ	ተዬ--ቴ	ተህ--ት	ተዎ--ቶ
ቸ	ቸዉ--ቹ	ቸዩ--ቺ	ቸአ--ቻ ቸዋ--ቿ	ቸዬ--ቼ	ቸህ--ች	ቸዎ--ቾ
ጸ	ጸዉ--ጹ	ጸዩ--ጺ	ጸአ--ጻ	ጸዬ--ጼ	ጸህ--ጽ	ጸዎ--ጾ
ፐ	ፐዉ--ፑ	ፐዩ--ፒ	ፐአ--ፓ	ፐዬ--ፔ	ፐህ--ፕ	ፐዎ--ፖ

(፴፪)

የመኪና ፣ ፊደል ፣ ከንጓዙ ።

አ ለ ገ ደ ሀ ወ ዘ ሐ ኀ ጠ የ ከ ለ መ ነ ሠ ዐ ፈ ጸ ፀ ቀ ረ ሰ ተ ጸ ፐ ።

ዲ ቃ ሎ ች ።

ጐ ጀ ገሯ ጎ ጨ ኰ ኸ ኘ ቈ ኸ ቸ ።

ዋ የ ሎ ች ።

ዉ ዩ አ—ዋ ዬ ህ ዎ ።

ም ል ክ ቶ ች ።

፡ ። ፣ ፤ ፥ ? ! ( ) - « » — ' ።

አ ኃ ዘ ች ።

1	2	3	4	5	6	7	8	9	0
፩	፪	፫	፬	፭	፮	፯	፰	፱	፲
፳	፴	፵	፶	፷	፸	፹	፺	፻	፼

(፴፫)

የዋየል ፣ አገባብ ፣ ማሳያ ፣ ከመጽሐፈ ምሳሌ ፣ የመጡ ፣ ቃሎች ።

ገህ አህ ዘህ = ላ እ ዝ ።

(ም፩ ፣ ፩ ፣ ፪) መህሰአለህየአተ ፣ ሰለዎመዎነህ ፣ ወለህደ ፣ ደአወዱ-ተህ ፣ ነህገዉሠ ፣ አህሰህረአአዬለህ ። ለአአህመህረዎ ፣ ጠህበበህ ፣ ወተ-ገህሠአጸህ = ምሳልያተ ፣ ሰሎሞን ፣ ወልደ ፣ ዳዊት ፣ ንጉሠ ፣ እስራኤል ። ለአእምሮ ፣ ጥበ ብ ፣ ወተግሣጽ ።

0 መኣ ረህ ኘኣ = 0 ማ ር ኛ ።

(፬ ፣ ፭) አህለአነህተ ፣ ለህጀዎቸህ ፣ የአበአተህነህ ፣ ተገህሠአጸህ ፣ ሰ-ህመዉ ፤ ዐህወህቀተህነህመህ ፣ ተአሰህተወህለዉ ፣ ዘነህደህ ፣ አደህመህ-ጠዉ = እላንት ፣ ልጆች ፣ ያባትን ፣ ተግሣጽ ፣ ስሙ I ዕውቀትንም ፣ ታስተውሉ ፣ ዘንድ ፣ አ ድምጡ ። (፪) መለህከአመህ ፣ ተህመህረህተህ ፣ አህሰጠአቸህኸዋለኸዉነአ I ተህመህረህተዱነህ ፣ አተህተወዉ = መልካም ፣ ትምርት ፣ እሰጣችኹዋለኹና I ትም ርቴን ፣ አትተዉ ። (፲፯ ፣ ፷፩) ለህበዉ ፣ በህለህጎተኘአ ፣ የኸዎነ ፣ አሰህተወአ-የህ ፣ ተበህለዎ ፣ የህጠረአለህ ፤ በነገረዉመህ ፣ ጠአፈአጨህ ፣ የኸዎነ ፣ ተህመህረህተህ ፣ የአበዘአለህ = ልቡ ፣ ብልኀተኛ ፣ የኾነ ፣ አስተዋይ ፣ ተብሎ ፣ ይጠራ ል I በነገሩም ፣ ጣፋጭ ፣ የኾነ ፣ ትምርት ፣ ያበዛል ። (፷፪) ለገዘአወህ ፣ ሰወህ ፣ መአ-ሰህተወአለህ ፣ የሐህየህወተህ ፣ መህነህጨህ ፣ ነወህ ፤ የደነአቈህረህተህ ፣ ተህመህረህተህ ፣ ገህነህ ፣ ሰህነህፈህነአ ፣ ነወህ = ለገዛው ፣ ሰው ፣ ማስተዋል ፣ የ ሕይወት ፣ ምንጭ ፣ ነው I የደናቍርት ፣ ትምርት ፣ ግን ፣ ስንፍና ፣ ነው ። (፷፫) የበህለህጎ-ተኘአ ፣ ለህበህ ፣ አፈዉነህ ፣ አሰህተወአየህ ፣ የአደረህገአለህ ፤ ለከነህፈ-ረዉመህ ፣ ተህመህረህተህ ፣ የህጨመህረአለህ = የብልኀተኛ ፣ ልብ ፣ አፉን ፣ አ ስተዋይ ፣ ያደርጋል I ለከንፈሩም ፣ ትምርት ፣ ይጨምራል ። (፲፯ ፣ ፲፯) በሰነፈህ ፣ አህ-ጀህ ፣ የጠህበበህ ፣ መግህዣአ ፣ ገነህዘበህ ፣ በዱነዎረህ ፣ ጠህበበህነህ ፣ የህ-ገዘአ ፣ ዘነህደህ ፣ አአህመህረዎ ፣ የለወህመህነአ ፣ መህነህ ፣ የህጠቀህመ-ወአለህ = በሰነፍ ፣ እጅ ፣ የጥበብ ፣ መግዣ ፣ ገንዘብ ፣ ቢኖር ፣ ጥበብን ፣ ይገዛ ፣ ዘንድ ፣ አእ ምሮ ፣ የለውምና I ምን ፣ ይጠቅመዋል ። (አስተውል) ዋየሎች ፣ ራሳቸውን ፣ መቻላቸው I አስቀድመን ፣ እንደ ፣ ትናገርን ፣ በመነሻና ፣ በመድረሻ I ብቻ ፣ ብቻቸውን ፣ ሲኾኑ ፣ ነው ። (ምሳ ሌ I (ዉ ፣ ዋ ፣ ዎ) ዉለዋለህ I ዉሏል ። ዉጠዋለህ I ዉጧል ። ዋጀ I ዋሸ I ዋኘ I ዋለለ ። ደ-ኣዋ I ዳዋ ። መህጠህዋ I ምጥዋ ። ለህጀህዎ I ልጅዎ ። በቤተህዎ I ቤትዎ ። በዱለኣዎ I ቢሳዎ ። ግእዝ ፣ ሲቀድመው ፣ ግን ፣ ዋየል ፣ እንጂ ፣ (ኮንሶን) ባለቤት ፣ አይኾንም ። (ምሳሌ) ጨዉ ፣ ጩ I ስዉ ፣ ሱ I ጨወዉ I ሰወዉ I ጨዉ ፣ ስዉ ። ሸዋ I ኟ I ዐደዋ I ዐጂ ። ንገዎ I ንጎ ። ንገወዎ I ን ገዎ I የመስለው ፣ ኹሉ ። (ዱ ፣ ዱ) ነዱ I ኂ ። ነየዱ I ነዱ ። ነየህ I ነይ ። አህዱ፣እዱ ። ገዱተኣዱ I

ጊዜ። ▪ አህመዲኔጃድ I አመሰግቱ ▪ ሽመዳ I ሸዋዬ I የመሰለው ▪ ኀሎ ▪ ነ፣ ሀ) ነ፣ ባማርኛ ▪ መ
ሃኖና ▪ መድረሻ ▪ ሲኸን ▪ እኔ ▪ በማልል ▪ ባስያረረ ▪ ትንባኬ ▪ አስመሰለኸ I አስቀመስኸኝ I ይኸ
ን ▪ በመስለ ▪ መድረሻ ▪ ሲኸን ▪ አፈሀኑ I አፍኑ ▪ ሠወሀህ I ሠወሀህ I የሞሀህ I ሂያስ ▪
በሽዚኸ ▪ ብቻ ▪ ይገኛል ▪ ይኸ I ፊደል I የመጠ ▪ በጅ ▪ መኸና ▪ ምኸንያት ▪ ፊደላት ▪ በሙ·
ተብለው ▪ እንዴይከለሉ ▪ ለመኪና ▪ ብቻ ▪ ስለ ▪ ኸን ▪ ሲጅ ▪ ጥፈት ▪ እይቀናም I ሥራው ▪ ዕጥ
ፍ ▪ ድርብ ▪ ነው ▪ « ያማርኛ ▪ ቃል ▪ ገዚር ▪ ሊኸን I ከልሆረዚ ▪ መኸር ▪ ን ▪ አየሰኝም ▪ ማን
ት ▪ አገ ▪ ልጅ ▪ ወለደ I ይሰል ▪ አንጂ ▪ ሚስትን ▪ ሲጅን ▪ አይልም I ሊዘረዝር ▪ ማን ▪ ማስቴ
ን ▪ ፈታ ▪ ሲጅን ▪ መታ ▪ ያስኸል ▪ አንዳንድ ▪ ኸዜ ▪ ብቻ ▪ አንደ ▪ ግእዙ I ሲጅን ▪ መቅጠት I
ማስኸን ▪ መቁጠት ▪ እያለኸ I በማያምርልኸ ▪ በታ ▪ አለዝርዝር ▪ ይገኛል» ።

(በ፬) ▪ ኅብረቁምፊ ▪ ትዕዛዞ ▪ (አርባዕቱ ▪ አዕዋደ ▪ ትዕዛዝ)

ች ▪ በየውስጣቸው ▪ ሂ ▪ መደብ ▪ የመደመርና ▪ የመቀነስ ▪ የማባዛትና ▪ የመካፈል ▪ ርብ ▪ ያሉት
መ) ▪ በዘሮው ▪ ፈንታ ▪ ሂኛ ▪ አጋዥ ▪ ዜሀ ▪ ገበሬዎው ▪ መደበኛው ▪ በመሸጋገሪ ▪ ተግፍ ▪ አ
ደ ▪ ጣት ▪ ታላቅና ▪ ታናሽ ▪ ኀሎት ▪ ሳይንጸፍ I በየመሰሉ ▪ በ
ስ ▪ ሽን ▪ ከሀንዳዊው ▪ ተራ ▪ ልደ ▪ ነው I ምንም ▪ ምክሪናና ▪ ቀጥሩ ▪ ዘር ▪ ተመምጥም ▪
ያው ▪ ቢኸን ▪ አዚፊ ▪ አይገሣም ▪ ። በግእዝ ▪ አንገት ▪ መጠፋፍን ▪ አዳኖት ▪ ቆሎ ▪ በቅርብ ▪
እንዲያንሰራና ▪ እንዲያሰኙት ▪ ነው I ሥራው ▪ ግን ▪ በዚያው ▪ በበቀልኸት ▪ በባዘርው ▪ በሀ
ንዲዊው ▪ አጋገ ▪ ከልኸን ▪ በዚኸ ▪ አይመችም I በዚ ▪ የተመሰውን ▪ ፀጋማይ ▪ መማሪ ▪ ነኝ ▪
ውጊ ▪ ቀኝ ▪ መሃድ ▪ ያለርስትል ▪ ኸታች ▪ በደኸው ▪ ነፍስ ▪ ከ(1ጅ—10ጅ)ንጂ ▪ አስከሥር ▪ የ
ቃጠሎን ▪ ቀጥር ▪ አኸን ▪ በዚኸ ▪ ከአሰቀድ ▪ መቅድም ▪ አድርጎን ▪ አስከ ▪ ምኸል
ፊት ▪ አንጥፋለን ▪ ሀንዳዊው ▪ አጋገ ▪ ከቀኝ ▪ ወደ ▪ ግራ ▪ መሃይን I በዘር ▪ መብዙቱን I ፀ–
9 ▪ ብቻ ▪ ኸሎ ▪ በር ▪ ቤት ▪ መከፈሉን I የዘርዉን ▪ ጠባይ ▪ (0) ▪ ቅርሀን ▪ አቀማመጡ
ን I የአጋዘኑን ▪ ነው ▪ በሀኑ ▪ ምክኒያት ▪ መለዋወጡን I ሰው ▪ ኸሎ ▪ የማይወቀው ▪ ከለ ▪ ኸ
ን ▪ መልካሉና ▪ ግብሩን ▪ ሠርገረን ▪ ሳንሄን ▪ አንዲን ▪ (1) ▪ ብቻ ▪ በዘር ▪ ሳይ ▪ (የሀንዳዊ ▪ አጋገ
እገ ▪ ቀ·ጥር ▪ እናባመልከን I መሰማዕቱ·ም ▪ ባያነው ▪ አይ ▪ (የሀንዳዊ ▪ አጋገ

፩	ኢ	—	፩ I
፲	፨	—	፲ I
፻	ቂ	—	፻ I
፲፡፡፡	ኪ	—	፲፡፡፡ I
፻፡፡፡	ኬ	—	፻፡፡፡ I
፩፡፡፡፡	ክ	—	፩፡፡፡፡ I
፲፡፡፡፡	ኮ	—	፲፡፡፡፡ I
፻፡፡፡፡	ኰ	—	፻፡፡፡፡ I
፩፡፡፡፡፡	ኲ	—	፩፡፡፡፡፡ I
፲፡፡፡፡፡	ኳ	—	፲፡፡፡፡፡ I
፻፡፡፡፡፡	ኴ	—	፻፡፡፡፡፡ I
፩፡፡፡፡፡፡	ኵ	—	፩፡፡፡፡፡፡ I
፲፡፡፡፡፡፡	ኸ	—	፲፡፡፡፡፡፡ I
፻፡፡፡፡፡፡	ኹ	—	፻፡፡፡፡፡፡ I
፩፡፡፡፡፡፡፡	ኺ	—	፩፡፡፡፡፡፡፡ I
፲፡፡፡፡፡፡፡	ኻ	—	፲፡፡፡፡፡፡፡ I
፻፡፡፡፡፡፡፡	ኼ	—	፻፡፡፡፡፡፡፡ I
፩፡፡፡፡፡፡፡፡	ኽ	—	፩፡፡፡፡፡፡፡፡ I
፲፡፡፡፡፡፡፡፡	ኾ	—	፲፡፡፡፡፡፡፡፡ I
፻፡፡፡፡፡፡፡፡	ዀ	—	፻፡፡፡፡፡፡፡፡ I
፩፡፡፡፡፡፡፡፡፡	ዂ	—	፩፡፡፡፡፡፡፡፡፡ I
፲፡፡፡፡፡፡፡፡፡	ዃ	—	፲፡፡፡፡፡፡፡፡፡ I
፻፡፡፡፡፡፡፡፡፡	ዄ	—	፻፡፡፡፡፡፡፡፡፡ I
፩፡፡፡፡፡፡፡፡፡፡	ዅ	—	፩፡፡፡፡፡፡፡፡፡፡ I
፲፡፡፡፡፡፡፡፡፡፡	዆	—	፲፡፡፡፡፡፡፡፡፡፡ I
፻፡፡፡፡፡፡፡፡፡፡	዇	—	፻፡፡፡፡፡፡፡፡፡፡ I
፩፡፡፡፡፡፡፡፡፡፡፡	ወ	—	፩፡፡፡፡፡፡፡፡፡፡፡ I
፲፡፡፡፡፡፡፡፡፡፡፡	ዉ	—	፲፡፡፡፡፡፡፡፡፡፡፡ I
፻፡፡፡፡፡፡፡፡፡፡፡	ዊ	—	፻፡፡፡፡፡፡፡፡፡፡፡ I
፩፡፡፡፡፡፡፡፡፡፡፡፡	ዋ	—	፩፡፡፡፡፡፡፡፡፡፡፡፡ I
፲፡፡፡፡፡፡፡፡፡፡፡፡	ዌ	—	፲፡፡፡፡፡፡፡፡፡፡፡፡ I
፻፡፡፡፡፡፡፡፡፡፡፡፡	ው	—	፻፡፡፡፡፡፡፡፡፡፡፡፡ I
፩፡፡፡፡፡፡፡፡፡፡፡፡፡	ዐ	—	፩፡፡፡፡፡፡፡፡፡፡፡፡፡ I
፲፡፡፡፡፡፡፡፡፡፡፡፡፡	ዑ	—	፲፡፡፡፡፡፡፡፡፡፡፡፡፡ I
፻፡፡፡፡፡፡፡፡፡፡፡፡፡	ዒ	—	፻፡፡፡፡፡፡፡፡፡፡፡፡፡ I
፩፡፡፡፡፡፡፡፡፡፡፡፡፡፡	ዓ	—	፩፡፡፡፡፡፡፡፡፡፡፡፡፡፡ I
፲፡፡፡፡፡፡፡፡፡፡፡፡፡፡	ዔ	—	፲፡፡፡፡፡፡፡፡፡፡፡፡፡፡ I
፻፡፡፡፡፡፡፡፡፡፡፡፡፡፡	ዕ	—	፻፡፡፡፡፡፡፡፡፡፡፡፡፡፡ I
፩፡፡፡፡፡፡፡፡፡፡፡፡፡፡፡	ዖ	—	፩፡፡፡፡፡፡፡፡፡፡፡፡፡፡፡ I

መ ደ መ ር ▪

የመደመር ▪ ሥርዓት ▪ በያንዳንዱ ▪ መደብ ▪ ከተጠራው ▪ ከቁ ▪ ከቁት ▪ ተራ ▪ አኸን ▪ ጀምሬ
ን ▪ በማጠቃሪር ▪ እየደመሩ ▪ ይኸ ▪ ይኸመን ▪ ድመር ▪ ማለት ▪ ነው ▪ ይኸም ▪ ጀን ▪ ፪ ▪ ፪ ▪
ጀን ▪ ፫ ▪ ፫ ▪ እያለኸ ▪ ባሥሩ ▪ አኸን ▪ ኹሉ ▪ እስከሥር ▪ መደብ ▪ መጠመቱን ▪ ያሳያል ▪

፩	፪	፫	፬	፭	፮	፯	፰	፱	፲

٨	٧	٦	٥	٤	٣	٢	١
٨	٧	٦	٥	٤	٣	٢	١
١٦	١٥	١٤	١٣	١٢	١١	١٠	٩
٢٤	٢٣	٢٢	٢١	٢٠	١٩	١٨	١٧
٣٢	٣١	٣٠	٢٩	٢٨	٢٧	٢٦	٢٥
٤٠	٣٩	٣٨	٣٧	٣٦	٣٥	٣٤	٣٣
٤٨	٤٧	٤٦	٤٥	٤٤	٤٣	٤٢	٤١
٥٦	٥٥	٥٤	٥٣	٥٢	٥١	٥٠	٤٩
٦٤	٦٣	٦٢	٦١	٦٠	٥٩	٥٨	٥٧
٧٢	٧١	٧٠	٦٩	٦٨	٦٧	٦٦	٦٥
٨٠	٧٩	٧٨	٧٧	٧٦	٧٥	٧٤	٧٣
٨٨	٨٧	٨٦	٨٥	٨٤	٨٣	٨٢	٨١
٩٦	٩٥	٩٤	٩٣	٩٢	٩١	٩٠	٨٩
١٠٤	١٠٣	١٠٢	١٠١	١٠٠	٩٩	٩٨	٩٧
١١٢	١١١	١١٠	١٠٩	١٠٨	١٠٧	١٠٦	١٠٥
١٢٠	١١٩	١١٨	١١٧	١١٦	١١٥	١١٤	١١٣
١٢٨	١٢٧	١٢٦	١٢٥	١٢٤	١٢٣	١٢٢	١٢١
١٣٦	١٣٥	١٣٤	١٣٣	١٣٢	١٣١	١٣٠	١٢٩
١٤٤	١٤٣	١٤٢	١٤١	١٤٠	١٣٩	١٣٨	١٣٧
١٥٢	١٥١	١٥٠	١٤٩	١٤٨	١٤٧	١٤٦	١٤٥
١٦٠	١٥٩	١٥٨	١٥٧	١٥٦	١٥٥	١٥٤	١٥٣
١٦٨	١٦٧	١٦٦	١٦٥	١٦٤	١٦٣	١٦٢	١٦١
١٧٦	١٧٥	١٧٤	١٧٣	١٧٢	١٧١	١٧٠	١٦٩
١٨٤	١٨٣	١٨٢	١٨١	١٨٠	١٧٩	١٧٨	١٧٧
١٩٢	١٩١	١٩٠	١٨٩	١٨٨	١٨٧	١٨٦	١٨٥
٢٠٠	١٩٩	١٩٨	١٩٧	١٩٦	١٩٥	١٩٤	١٩٣
٢٠٨	٢٠٧	٢٠٦	٢٠٥	٢٠٤	٢٠٣	٢٠٢	٢٠١
٢١٦	٢١٥	٢١٤	٢١٣	٢١٢	٢١١	٢١٠	٢٠٩
٢٢٤	٢٢٣	٢٢٢	٢٢١	٢٢٠	٢١٩	٢١٨	٢١٧
٢٣٢	٢٣١	٢٣٠	٢٢٩	٢٢٨	٢٢٧	٢٢٦	٢٢٥
٢٤٠	٢٣٩	٢٣٨	٢٣٧	٢٣٦	٢٣٥	٢٣٤	٢٣٣
٢٤٨	٢٤٧	٢٤٦	٢٤٥	٢٤٤	٢٤٣	٢٤٢	٢٤١
٢٥٦	٢٥٥	٢٥٤	٢٥٣	٢٥٢	٢٥١	٢٥٠	٢٤٩

٨	٧	٦	٥	٤	٣	٢	١
٨	٧	٦	٥	٤	٣	٢	١
١٦	١٥	١٤	١٣	١٢	١١	١٠	٩
٢٤	٢٣	٢٢	٢١	٢٠	١٩	١٨	١٧
٣٢	٣١	٣٠	٢٩	٢٨	٢٧	٢٦	٢٥
٤٠	٣٩	٣٨	٣٧	٣٦	٣٥	٣٤	٣٣
٤٨	٤٧	٤٦	٤٥	٤٤	٤٣	٤٢	٤١
٥٦	٥٥	٥٤	٥٣	٥٢	٥١	٥٠	٤٩
٦٤	٦٣	٦٢	٦١	٦٠	٥٩	٥٨	٥٧
٧٢	٧١	٧٠	٦٩	٦٨	٦٧	٦٦	٦٥
٨٠	٧٩	٧٨	٧٧	٧٦	٧٥	٧٤	٧٣
٨٨	٨٧	٨٦	٨٥	٨٤	٨٣	٨٢	٨١
٩٦	٩٥	٩٤	٩٣	٩٢	٩١	٩٠	٨٩
١٠٤	١٠٣	١٠٢	١٠١	١٠٠	٩٩	٩٨	٩٧
١١٢	١١١	١١٠	١٠٩	١٠٨	١٠٧	١٠٦	١٠٥
١٢٠	١١٩	١١٨	١١٧	١١٦	١١٥	١١٤	١١٣
١٢٨	١٢٧	١٢٦	١٢٥	١٢٤	١٢٣	١٢٢	١٢١
١٣٦	١٣٥	١٣٤	١٣٣	١٣٢	١٣١	١٣٠	١٢٩
١٤٤	١٤٣	١٤٢	١٤١	١٤٠	١٣٩	١٣٨	١٣٧
١٥٢	١٥١	١٥٠	١٤٩	١٤٨	١٤٧	١٤٦	١٤٥
١٦٠	١٥٩	١٥٨	١٥٧	١٥٦	١٥٥	١٥٤	١٥٣
١٦٨	١٦٧	١٦٦	١٦٥	١٦٤	١٦٣	١٦٢	١٦١
١٧٦	١٧٥	١٧٤	١٧٣	١٧٢	١٧١	١٧٠	١٦٩
١٨٤	١٨٣	١٨٢	١٨١	١٨٠	١٧٩	١٧٨	١٧٧
١٩٢	١٩١	١٩٠	١٨٩	١٨٨	١٨٧	١٨٦	١٨٥
٢٠٠	١٩٩	١٩٨	١٩٧	١٩٦	١٩٥	١٩٤	١٩٣
٢٠٨	٢٠٧	٢٠٦	٢٠٥	٢٠٤	٢٠٣	٢٠٢	٢٠١
٢١٦	٢١٥	٢١٤	٢١٣	٢١٢	٢١١	٢١٠	٢٠٩
٢٢٤	٢٢٣	٢٢٢	٢٢١	٢٢٠	٢١٩	٢١٨	٢١٧
٢٣٢	٢٣١	٢٣٠	٢٢٩	٢٢٨	٢٢٧	٢٢٦	٢٢٥
٢٤٠	٢٣٩	٢٣٨	٢٣٧	٢٣٦	٢٣٥	٢٣٤	٢٣٣
٢٤٨	٢٤٧	٢٤٦	٢٤٥	٢٤٤	٢٤٣	٢٤٢	٢٤١
٢٥٦	٢٥٥	٢٥٤	٢٥٣	٢٥٢	٢٥١	٢٥٠	٢٤٩

መ ክ ፈ ል ።

የመክፈል ፣ ወይም ፣ የማካፈል ፣ ሥርዐት ፤ ከፎቱ ፣ ተራ ፣ አጋዝ ፣ ጀኛው ፣ ተከፋይ ፤ ፪ኛው ፣ ከፋይ ፣ መክፈያ ፣ ወይም ፣ ተቀባይ ፤ ፫ኛው ፣ ክፍል ፣ ይባላል ። ይኸም ፣ ፭ ፣ ባ፭ ፣ ቢከፈል ፣ ፭ ፣ ይኸናል ፤ ወይም ፣ ፭ን ፣ ላ፭ ፣ ቢሰጡት ፣ ፭ ፣ ይደርሰዋል ፣ እያለ ፣ አስካ፲ ፣ መደብ ፣ መገመቱን ፣ ያሳያል ።

፱ኛ ፣ የ ማ ካ ፈ ል ፣ ዐ ው ድ ።

ይ	፭	ቢ	፭	ባ	፭
»	፭	»	፭	»	፭
»	፫	»	፭	»	፭
»	፬	»	፭	»	፭
»	፭	»	፭	»	፭
»	፮	»	፭	»	፭
»	፯	»	፭	»	፭
»	፰	»	፭	»	፭
»	፱	»	፭	»	፭

ይ	፪	ቢ	፪	ባ	፪
»	፪	»	፪	»	፪
»	፫	»	፪	»	፪
»	፬	»	፪	»	፪
»	፭	»	፪	»	፪
»	፮	»	፪	»	፪
»	፯	»	፪	»	፪
»	፰	»	፪	»	፪
»	፱	»	፪	»	፪

ይ	፫	ቢ	፫	ባ	፫
»	፫	»	፫	»	፫
»	፬	»	፫	»	፫
»	፭	»	፫	»	፫
»	፮	»	፫	»	፫
»	፯	»	፫	»	፫
»	፰	»	፫	»	፫
»	፱	»	፫	»	፫

ይ	፬	ቢ	፬	ባ	፬
»	፬	»	፬	»	፬
»	፭	»	፬	»	፬
»	፮	»	፬	»	፬
»	፯	»	፬	»	፬
»	፰	»	፬	»	፬
»	፱	»	፬	»	፬

ይ	፭	ቢ	፭	ባ	፭
»	፭	»	፭	»	፭
»	፮	»	፭	»	፭
»	፯	»	፭	»	፭
»	፰	»	፭	»	፭
»	፱	»	፭	»	፭

ይ	፮	ቢ	፮	ባ	፮
»	፮	»	፮	»	፮
»	፯	»	፮	»	፮
»	፰	»	፮	»	፮
»	፱	»	፮	»	፮

ይ	፯	ቢ	፯	ባ	፯
»	፯	»	፯	»	፯
»	፰	»	፯	»	፯
»	፱	»	፯	»	፯

ይ	፰	ቢ	፰	ባ	፰
»	፰	»	፰	»	፰
»	፱	»	፰	»	፰

ይ	፱	ቢ	፱	ባ	፱
»	፱	»	፱	»	፱

(፴፭)

ታ ሪ ክ ፤ – በእንተ ፡ ፍልጠተ ፡ ጕልቈ ፡ ዘመን ፡ ቀዳማዊ ፡ ወደኃራዊ ።

ስለ ፡ ዘመን ፡ ቍጥር ፣ መለያየት ፡ የሚናገር ፡ ታሪክ ።

የብሉይና ፡ የቍጥር ፡ መምራን ፡ ዘመን ፡ አበውን ፡ እያሻሉና ፡ እየነሡ ፡ እያፋሰሱ ፡ ተርት ረው ፡ ደምረው ፡ ሲቈጥሩ ፡ እንዳራቱ ፡ መደብ ፡ ባራት ፡ ዐቢይ ፡ ክፍል ፡ ይከፍሉና ፡ ድምሩን ፡ ፭ሺሕ ፡ ካ፭፻ ፡ ዓመት ፡ ይሉታል ። ቍጥሩና ፡ ክፍሉም ፡ አከፋፈሉም ፡ እንደዚኽ ፡ ነው ። ከአዳም ፡ እስከ ፡ ኖህ ፡ ፳፱፻፶፯ ። — ከኖህ ፡ እስከ ፡ ሙሴ ፡ ፲፭፻፶፫ ። — ከሙሴ ፡ እስከ ፡ ሰሎሞን ፡ ፭፻፶፫ ። — ከሰሎሞን ፡ እስከ ፡ ክርስቶስ ፡ ፲፻፵፫ ። ድሙር ፡ ፶፭፻ ። የክፍሉም ፡ ምስጢራት ፡ መርከብና ፡ ድንኳን ፡ መቅደስና ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ናቸው ።



ዘከመ ፡ አውፅአሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለአዳም ፡ ወሔዋን ፡ እምገነት ፡ ት ፍሥሕት ፡ ወአሰፈዎሙ ፡ ፤ ካዕበ ፡ ተስፋ ፡ መድኀኒት ፡ (ዘፍ፫ ፡ ፲፭ ፡ ፲፭ ፡ ፳፪–፳፬) ። ወአመ ፡ በጽሐ ፡ ዕድሜሁ ፡ ፈነወ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወልዶ ፡ ወ ተወልደ ፡ እምብእሲት ፡ ወግብረ ፡ ቢሕገ ፡ አሪት ፡ ከመ ፡ ይሣየጦሙ ፡ ለ እለ ፡ ውስተ ፡ አሪት ፤ ከመ ፡ ንርከብ ፡ ትርሲተ ፡ ውሉድ ፡ (ገላ፬ ፡ ፬ ፡ ፭) ። እስመ ፡ ከመዝ ፡ አፍቀሮ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለዓለም ፡ እስከ ፡ ወልዶ ፡ ዋ ሕዶ ፡ መጠወ ፡ ወወሀበ ፡ ቤዛ ፡ (ዮሐ፫ ፡ ፲፮—፲፱ ። ሮሜ፭ ፡ ፰ ። ፰ ፡ ፴፪) ።

ክክርስቶስና ፣ ክቤተ ፣ ክርስቲያኑ ፣ ለማራቅ ፣ በኦሪትና ፣ በነቢያት ፣ መጽሐፍ ፣ የንባብ ፣ ግልፎ ፣ የትርጓሜ ፣ ጣያት ፣ አቁመዋል ፤ የትርጓሜውን ፣ ኹዋላ ፣ በበታው ፣ እናመጣዋለን ፣ (ገጽ ፣ ፷፪) ። አለመስታዮት ፣ ዐይንን ፣ ባይን ፣ ማየት ፣ እንዳይቻል ፤ አለመሲሕም ፣ መመርነት ፣ የብሉይ ፣ ኪዳንን ፣ ትርጓሜ ፣ አካቶ ፣ ፈጽሞ ፣ ማወቅ ፣ መረዳት ፣ ርግጡን ፣ ግግኘት ፣ ለማንም ፣ ለማን ፣ አይቻልምና ፤ ክዚኽ ፣ የተንማ ፣ የክርስቶስ ፣ ደቀ ፣ መዛሙርት ፣ ሐዋርያት ፣ አርድእት ፤ ይልቁንም ፣ የኦሪት ፣ ትምርት ፣ አበጋዞች ፣ የብሉይ ፣ የሐዲስ ፣ መሐንድዞች ፣ እንጻውሎስ ፣ እንእስጢፋናስ ፣ እንዚኽን ፣ የመሰሉ ፣ ኹሉ ፣ ሱባዔ ፣ ትውልድ ፣ ክሔኖክ ፤ ሱባዔ ፣ ዘመን ፣ ክዳንኤል ፤ ሱባዔ ፣ ዕለት ፣ ክኤርምያስ ፣ በስፍር ፣ በቊጥር ፣ እያመጡ ፤ ክኦሪትና ፣ ክነቢያት ፣ ብዙ ፣ ምስክር ፣ እየሰጡ ፤ ትውልዱን ፣ ክዘመን ፣ ትንቢቱን ፣ ከመድኀን ፣ እያስማሙና ፣ እየተረጐሙ ፤ ኦሪትን ፣ በፋና ፣ በአጋር ፣ በአመት ፤ ወንጌልን ፣ በፀሓይ ፣ በሳራ ፣ በመቤት ፤ የሱስን ፣ በይስሐቅ ፣ በአብርሃም ፣ መሥዋዕት ፣ እየመሰሉ ፤ ወግኅሳስቅቱስ ፣ ለጽድቀ ፣ ኦሪት ፣ አሚን ፣ በክርስቶስ ። እስመ ፣ ጽላሎታ ፣ ይእቲ ፣ ኦሪት ፣ ለእንተ ፣ ትመጽእ ፣ ውናይት ። ኦሪትሰኬ ፣ መርሐ ፣ ኮነተን ፣ ለንበ ፣ ክርስቶስ ፤ እንክሰ ፣ ኢንፈቅድ ፣ መርሐ ፣ እያሉ ፤ በክርክርና ፣ በሙግት ፤ ወዲኽም ፣ በአምላካዊ ፣ ኀይል ፣ በታምራት ፣ በ፪ ፣ ወገን ፣ የማይገፋ ፣ የማይሸነፋ ፣ የብሉይ ፣ ገግኖች ፣ የሐዲስ ፣ ወርበኞች ፣ ስለ ፣ ኽኑባቸው ፤ ካርባ ፣ የሚበዙ ፣ ይሁዶች ፣ እስጢፋኖስና ፣ ያዕቆብን ፣ ደብድበን ፣ እንደ ፣ ገደልን ፣ ጳውሎስን ፣ ሳኀንድል ፣ እኽል ፣ ውሀ ፣ እንዳንቀምስ ፣ ብለው ፣ ከተማማሉ ፣ በኹዋላ ፣ ርሱን ፣ ለብቻው ፣ ማግኘትና ፣ መግደል ፣ ቢሳናቸው ፣ ሥጋዊ ፣ ጦራቸው ፣ ጦርነታቸው ፤ የቊጣቸው ፣ አፍሬ ፣ የመሐላቸው ፣ ሰይፍ ፣ በስለቱና ፣ ባንደበቱ ፣ ወደ ፣ መጻሕፍት ፣ ተመልሷል ። በሽንን ፣ ቢረታ ፣ ከቤት ፣ ሚስቱን ፣ መታ ፣ እንደሚሉት ፣ ኹሉ ፤ ክኅፍረትና ፣ ክብስዊት ፣ ክቊጣ ፣ ብዛት ፣ የተንማ ፣ ወንጌልን ፣ ያወኩ ፣ ኦሪትን ፣ ያሰፉ ፣ መስሏቸው ፤ ሐዋርያት ፣ የሚጠቅሏቸውን ፣ ደረቅ ፣ ትንቢትና ፣ ሱባዔ ፣ ራእይ ፣ ያሳቸውን ፤ የክርስቶስን ፣ አምላክነትና ፣ ሰውነት ፤ ድካሙን ፣ ኀይሉን ፣ መከራ ፣ መስቀሉን ፤ በሕማሙና ፣ በሞቱ ፣ የኅሊም ፣ መድኀኒት ፣ መኾኑን ፣ እንደ ፣ ቅዱስ ፣ ወንጌል ፣ ገልጠው ፣ አፍርጠው ፣ የሚናገሩትን ፤ ቃላቸው ፣ ክብሉይ ፣ ንባብ ፣ የተለየ ፣ ፍጹም ፣ ደረቅ ፣ ሐዲስ ፣ ስለ ፣ ኽነ ፣ ክቊጥር ፣ ክቀመር ፣ ሳይገቡ ፣ ለምስክርነት ፣ እንዳይን ፣ ብሌን ፣ እንዳደራ ፣ ምናን ፣ በፍጹም ፣ ጥንቃቄ ፣ ተጠብቀው ፣ በቤተ ፣ መቅደስ ፣ ይኖሩ ፣ የነበሩትን ፣ የብሉይን ፣ አዋልድ ፣ ኹሉ ፣ በሕዝቅኤል ፣ መቅድም ፣ እንደ ፣ ጣፍነው ፤ ሞ ፌሽ ፣ ክዕብራይስጥ ፣ ዕልም ፣ ድርግም ፣ አርገው ፣ አጠኞቸው ፤ ይኽውም ፣ በሐዋርያት ፣ ጥቅስ ፣ ይታወቃል ፣ (ማቴ፳፫ ፣ ፱ ፣ ፲ ። ይሁ ፣ ፲፱ ፣ ፲፳) ። ያገራችን ፣ ሰዎች ፣ ዕብራይስጥ ፣ ጠፍቷል ፣ የሚሉት ፣ ይኽን ፣ ምክንያት ፣ ይዘው ፣ ነው ፤ ወርቁ ፣ ደረቅ ፣ ትንቢት ፣ ጠፋ ፣ እንጂ ፣ ሚዛኑስ ፣ ቋንቋው ፣ አልጠፋም ፤ የሰነፍ ፣ ወፌ ፣ ነው ። (ኹዋላ ፣ ግን ፣ በጽርኡ ፣ ምላሽ ፣ ተገኝተው ፣ ወደ ፣ ግእዝ ፣ ከተተረጐሙት ፣ አዋልድ ፣ ኩፋሌና ፣ ሔኖክ ፣ ተረፈ ፣ ኤርምያስ ፣ ዕርገተ ፣ ኢሳይያስ ፣ እሊኽ ፣ አራቱ ፣ ከግእዝ ፣ በቀር ፣ በኹሉ ፣ ስላልተገኙ ፤ ሔኖክን ፣ ብቻ ፣ ከግእዝ ፣ ተርጕመው ፣ አይሁድ ፣ ሳይቀሩ ፣ ክርስቲያኖች ፣ ኹሉ ፣ ይዘውታል ። ከግእዝ ፣ ጋራ ፣ በዕብራይስጥ ፣ የታተመውን ፣ መጽሐፈ ፣ ሔኖክ ፣ ኢየሩሳሌም ፣ ላይ ፣ ደብረ ፣ ገነት ፣ ባለው ፣ በአይሁድ ፣ ዕቃ ፣ ቤት ፣ እኛ ፣ ባይናችን ፣ አይተናል) ። ከኦሪቱም ፣ ኹለቱን ፣ ምዕራፍ ፣ (ዘፍ፭ ፣ ፫-፴፩ ። ፲፩ ፣ ፲-፳፯) ፣ ለዋውጠው ፣ ገላብጠው ፣ ዘመን ፣ አበውን ፣ አፈሰሱት ፤ አዳም ፣ ሴትን ፣ በ፱፻፴ ፣ ወለደ ፣ ያለውን ፣ በ፻፴ ፣ አሉት ። ሴት ፣ ሄኖስን ፣ በ፹፻፭ ፣ ያለውን ፣ በ፻፭ ፣ አሉት ። ሄኖስ ፣ ቃይናንን ፣ በ፻፺ ፣ ያለውን ፣ በ፺ ፣ አሉት ። እንዲኽ ፣ እያሉ ፣ ፻፻ዉን ፣ ስርቀው ፣ ከፊት ፣ ወደ ፣ ኹዋላ ፣ እያዞሩ ፣ ከድጎሩና ፣ ከድምሩ ፣ ጋራ ፣ ጥፈውታል ፤ የፋቁትም ፣ ፫፻ ፣ ዓመት ፣ አለ ። ክትውልዱም ፣ አንዱ

ክክርስቶስ ፣ በፊት ፣ የንበረው ፣ ዘመን ፤ ዓመተ ፣ ፍዳ ፤ ዓመተ ፣ ዅንኔ ፤ ዘመን ፣ ብሉይ ፣ ይባላል ። ክክርስቶስ ፣ ወዲኽ ፣ ያለው ፣ ዘመን ፤ ዓመተ ፣ ምሕረት ፤ ዓመተ ፣ ሥጋዌ ፤ ዘመነ ፣ ሐዲስ ፣ ይባላል ፤ ይኽውም ፣ ዘመነ ፣ መሲሕ ፣ ማለት ፣ ነው ። መላው ፣ ባንድነት ፣ ሲደመርና ፣ ሲጠቀለል ፤ ዓመተ ፣ ዓለም ፤ መዋዕለ ፣ ዓለም ፣ ይባላል ። ኢትዮጵያ ፣ ዘመነ ፣ ብሉይን ፣ ፭ሺሕ ፣ ካ፭፻ ፣ ወይም ፣ ፱፭፻ ፣ ማለቷ ፤ ክጥንታዊው ፣ ጽርኣ ፣ የተቀዳ ፣ ክየናኒ ፣ የተመለሰ ፣ መጽሐፈ ፣ ኦሪቷን ፣ ተክትላ ፣ ነው ። ኦሪት ፣ በዘመነ ፣ ብሉይ ፣ ይኺዜ ፣ ተካክሎ ፣ ተጥፎ ፣ በ፫ ፣ ስሞች ፣ ተጠርቷል ፤ መገሥፅያ ፣ ሙሴ ፣ የጣፈው ፣ ኦሪተ ፣ ሌዋውያን ፣ ተብሏል ። ፱ኛ ፣ በስልምናሶር ፣ ዘመን ፣ ምናሴ ፣ ክህነ ፣ ቤቴል ፣ ለስግርያ ፣ ሕዝብ ፣ የጣፈው ፣ ኦሪተ ፣ ሳምራውያን ፣ ተብሏል ፤ እሊኹም ፣ አሕዛብ ፣ ናቸው ፣ (ይንገ ፣ ፲፯ ፣ ፳፬—፴) ። ይኛ ፣ በበጥሊሞስ ፣ ዘመን ፣ ስብዓ ፣ ሊቃናት ፣ ክዕብራኒ ፣ ወደ ፣ ዮናኒ ፣ የመለሱት ፤ በስግቸው ፣ ኦሪተ ፣ ሊቃናት ፣ ተብሏል ፣ (ስንክ ፣ የካ፳) ። ክዚኽ ፣ በኹዋላ ፣ አይሁድ ፣ በዘመን ፣ ሐዲስ ፤ ኦሪት ፣ ነቢያትን ፣ ለመቃወም ፤ በግዜርና ፣ በመሲሑ ፣ ላይ ፣ በጠላትነት ፣ ተነሥተዋል ። ኦሪት ፣ ነቢያት ፣ የሰበኩት ፣ ርግጡ ፣ የመሲሕ ፣ አመጣጥ ፣ ለማዳንና ፣ ለመፍረድ ፣ በትሕትናና ፣ በልዕልና ፣ ክዕዋልና ፣ በደመና ፣ ፪ጊዜ ፣ ሲኾን ፤ የትሕትናዉን ፣ አመጣጥ ፣ ፊተኛውን ፣ ክደው ፣ ኹዋለኛውን ፣ ብቻ ፣ የልዕልናውን ፣ ስላመኑ ፤ ኹዋላም ፣ እንደዚኹ ፣ ስተው ፣ ተሳስተው ፣ ከመሲሕ ፣ በፊት ፣ በሚመጣው ፣ በሐሳዊ ፣ መሲሕ ፣ የሚያምኑ ፣ ሐሳውያን ፣ ነቢያተ ፣ ሐሰት ፣ ስለ ፣ ኽኑ ፣ የመሲሕን ፣ መንግሥት ፣ ሥጋዊ ፣ ምድራዊ ፣ አስመስለው ፤ መሲሑንም ፣ ሥግው ፣ ቃል ፣ ያይደለ ፣ ዕሩቅ ፣ ብእሲ ፣ ብለው ፣ ከውነተኛ ፣ አምልኮ ፣ ክግዜር ፣ መንግሥት ፣ ክብርሃም ፣ በረከት ፣ ወጥተው ፣ በኦሪት ፣ መርገም ፣ ተጨለጠውና ፣ ተገርኝተው ፣ ወደ ፣ ሰይጣን ፣ መንግሥት ፣ ሂደዋል ፣ (ዮሐ፰ ፣ ፵፬ ። ራእ፪ ፣ ፱) ። የአዳም ፣ ኀጢአት ፣ እንደ ፣ ኰብኵና ፣ እንደ ፣ ቂጥኝ ፣ ወርሶት ፣ በሔዋን ፣ እባብ ፣ መርዝ ፣ ተወግዶ ፤ ሹለንተናው ፣ ቄስሎ ፣ ተበላሽቶ ፣ ውሾች ፣ አጋንንት ፣ የሚልሱት ፣ ይኽ ፣ በሽተኛ ፣ ዓለም ፣ ከጥንቱና ፣ ከመሠረቱ ፣ ክባቱ ፣ ከአዳም ፣ ከናቱ ፣ ከሔዋን ፣ ገምሮ ፣ ፈጣሪው ፣ የሰጠው ፣ የመድኀኒት ፣ ተስፋ ፣ ስላለው ፤ ስሙ ፣ ከግብሩ ፣ ተባብሮለት ፣ የሱስ ፣ ዐማኑኤል ፣ ተብሎ ፣ በሙሴ ፣ እባብ ፣ አምላል ፣ ተሰቅሎ ፣ ክሰማይ ፣ እባብ ፣ ክዲያብሎስ ፣ ሕምዝ ፣ ክሰራዊቱ ፣ መርዝ ፣ የሚያድን ፣ ስማያዊ ፣ ኀጉሥ ፣ ሐኪምና ፣ ፈውስ ፣ የማይሻ ፣ መስሏቸው ፤ የንቅፋትና ፣ የማእዝን ፣ ደንጊያ ፣ ብተባለው ፣ በክርስቶስ ፣ ትሕትና ፣ በፍጹም ፣ ውርደቱ ፤ ጨርቅ ፣ አጠርቅሞ ፣ ግንድ ፣ ተሸክሞ ፣ በመታየቱ ፣ በመስቀሉ ፣ በመስቀሉ ፣ ተሰናክለው ፣ ትንግኤውንም ፣ አስተባብለው ፣ እውነተኛውን ፣ መሲሕና ፣ መድኀን ፣ የመሲሕን ፣ ዘመን ፣ ክዘመናቸው ፣ ለማራቅ ፤ መሲሑም ፣ ዘመኑም ፣ ሌላ ፣ ነው ፤ ገና ፣ ወደ ፣ ፊት ፣ ነው ፤ ይኽ ፣ ዛፊ ፣ በኛ ፣ ዘመን ፣ ንጉሠ ፣ አይሁድ ፣ ተብሎ ፣ ሌላ ፣ ነው ፤ ገና ፣ ወደ ፣ ፊት ፣ ነው ፤ ይኽ ፣ ዛፊ ፣ በኛ ፣ ዘመን ፣ ንጉሠ ፣ አይሁድ ፣ ተብሎ ፣ ዓለም ፣ ኹሉ ፣ የተከተለው ፣ እኛ ፣ ግን ፣ ሰቅለን ፣ የገደልነው ፣ የናዝሬቱ ፣ የሱስ ፤ ምንም ፣ ክዳዊት ፣ ዘር ፣ ቢወለድ ፣ ለኛ ፣ ተገዛ ፣ እንጂ ፣ በኛ ፣ ላይ ፣ አልንገሠምና ፣ መሲሕ ፣ አይደለም ፣ ለማለት ፣ እግዜር ፣ በሙሴ ፣ እጅ ፣ ላባቶቻቸው ፣ ለሌዋውያን ፣ የሰጠውን ፣ ኦሪት ፣ በዘመን ፣ አበው ፣ ምክንያት ፣ ክኦሪት ፣ ዘፍጥረት ፣ ኹለቱን ፣ ምዕራፍ ፣ (፭ና ፣ ፲፩) ስላባጠሉት ፤ ስሙ ፣ ተለውጠ ፣ ኦሪተ ፣ አይሁድ ፣ ብጡል ፣ ተብሏል ። ይኽውም ፤ ብጡሰ ፣ ፍቅድ ፤ መብጠሌ ፣ ትውልድ ፣ ዘአብጠልም ፣ አይሁድ ፣ ለአስሕቶ ፣ ደኀርት ፣ ውስድ ፣ ማለት ፣ ነው ፤ ብጡልነቱም ፣ በነዚኽ ፣ በ ኹለቱ ፣ ምዕራፍ ፣ ብቻ ፣ እንጂ ፤ የብሉይ ፣ መምራን ፣ እንደሚሉት ፣ መላው ፣ ፭ቱ ፣ ብሔር ፤ ወይም ፣ ፭ቱ ፣ የሙሴ ፣ መጽሐፍ ፣ ከሥር ፣ እስከ ፣ ጫፍ ፣ አይደለም ። ኢዮርብዓም ፣ ዐሥሩን ፣ ነገድ ፣ ክግዜርና ፣ ክኢየሩሳሌም ፣ ለማራቅ ፣ በዳንና ፣ በቤቴል ፣ ተራራ ፣ ፪ የወርቅ ፣ እንቦሶች ፣ አማልክት ፣ ብሎ ፣ እንዳቆመ ፤ አይሁድም ፣ ግብዝ ፣ ሕዝባቸውን ፣ ከውነተኛው ፣ መቅደስ ፣

ጽርኡ ፡ ግን ፡ ሺ ፡ ፲፱፻፸፭ ፡ (1775) ነው ። አግዜር ፡ አስቀድሞ ፡ መጻሕፍቱን ፡ ወደ ፡ ጽር
እ ፡ ቋንቋ ፡ ባያሸሽ ፡ የአይሁድ ፡ ክፋት ፡ የኦሪታቸው ፡ ብሙልነት ፡ እንዲኸ ፡ ፈጽሞ ፡ ባልታወ
ቀም ፡ ነበር ። (ተረት ፤ ስለ ፡ በቅሎ ፡ ክፋት) እግዜር ፡ ባወቀ ፡ ሰማዩን ፡ አራቀ ። አይሁድ ፡ ግን ፡
በሕይወታቸው ፡ አበጋዝ ፡ በክርስቶስ ፡ ትንግኢ ፡ ለመታብሩ ፡ ጠባቆች ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ ደፍተ
ው ፡ ሐዋርያት ፡ ኦሮድእት ፡ የተባሉትን ፡ ፲፪ቱን ፡ አንቅዕተ ፡ ሕግና ፡ ፍዉን ፡ የወንጌል ፡ በቀል
ት ፡ እንዳስተባበሉ ፤ በዚኽ ፡ ደግሞ ፡ ፍሊቃናትን ፡ ያስተባብላሉ ። (ማቴ፳፰ ፡ ፲፭-፲፰) ። የሳም
ራውያንም ፡ ኦሪት ፡ በዘመነ ፡ አበው ፡ ቍጥር ፡ ከሰብዓ ፡ ሊቃናት ፡ ትርጓሜ ፡ ከኦሪተ ፡ ጽርእ ፡
እንጂ ፤ ብሙል ፡ ከተባለው ፡ ከኦሪተ ፡ አይሁድ ፡ አይገጥምም ። ይኽም ፡ ሐተታና ፡ ቍጥር ፡ ኦሪ
ተ ፡ አይሁድን ፡ ብሙል ፡ ማለት ፡ የሊቁ ፡ የባለታሪኩ ፡ ያቡሻህር ፡ ቃል ፡ ነው ፤ ርሱ ፡ ዘመነ ፡ አ
በውን ፡ ሲጥፍ ፤ ይቤ ፡ መጽሐፈ ፡ ኦሪቶሙ ፡ ለሰብዓ ፡ መተርጕማን ፡ ብሎ ፡ ይገሥምናና ፡ በመ
ጨረሻው ፡ ይኽን ፡ አይሁድ ፡ የፋቁትን ፡ ይናገራል ። ዜና ፡ አይሁድን ፡ የጣፈ ፡ እውነተኛው ፡
ካህን ፡ ዮሴፍ ፡ ወልደ ፡ ኮርዮንም ፡ ዘመነ ፡ አበውን ፡ እንዳቡሻህር ፡ እንደ ፡ ኦሪተ ፡ ጽርእ ፡ ጥ
ኖል ፤ ይኸውም ፡ ሊታወቅ ፡ አይሁድ ፡ ከአዳም ፡ እስከ ፡ ጥጦስ ፡ ፫ሺሕ ፡ ከ፮፻፸፮ ፡ የሚሉትን ፡
ዓመተ ፡ ፀሓይ ፡ ርሱ ፡ በጨረቃ ፡ ፭ሺሕ ፡ ከ፯፻፸፭ ፡ ይላል ። «አይሁድም ፡ ከዚኽ ፡ የተንሣ
ሌላም ፡ ርሳቸውን ፡ የሚያሳፍርና ፡ አባቶቻቸውን ፡ የሚያስንውር ፡ ብዙ ፡ ድንቅ ፡ ታሪክ ፡ አምላ
ካዊ ፡ ሥራ ፡ ስላለበት ፡ የዮሴፍን ፡ መጣፍ ፡ አይወዱትም ፤ ይልቁንም ፡ ክርስቲያኖች ፡ ስለ ፡ ተ
ቀበሉት ፡ ታሪኩንም ፡ ታምራቱንም ፡ ተረት ፡ ነው ፡ እያሉ ፡ እንደ ፡ ወንጌል ፡ እንደ ፡ ሐዲሳት ፡
ይንቅፉታል» ። በጥንተዮን ፡ ቍጥር ፡ ፭ቱ ፡ ሺሕ ፡ ከ፭፻ ፡ ዓመተ ፡ ወርኃ ፡ ከ፲፬ ፡ ጨረቃ ፡ እስ
ከ ፡ ጌታ ፡ ስቅለት ፡ ልክ ፡ ይኾናል ፤ ፵፮ቱም ፡ ከስቅለት ፡ እስከየሩሳሌም ፡ ጥፋት ፡ ነው ። የጨ
ረቃ ፡ ቍጥር ፡ ከፀሓይ ፡ ቁጥር ፡ መብዛቱ ፡ ግን ፡ ዐውደ ፡ ዓመታ ፡ ፫፻፶፬ ፡ ዕለት ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ነ
ው ። በኹዋላ ፡ ዘመንም ፤ የተነሡ ፡ ፯ቱ ፡ ባለታሪኮች ፡ ኦሪተ ፡ አይሁድን ፡ ነቅፈው ፡ አጸይፈው ፡
ዘመነ ፡ አበውን ፡ እንደ ፡ ጽርእና ፡ እንደ ፡ ሳምር ፡ ኦሪት ፡ ጥፈዋል ፤ እሊኹም ፡ ስሚድ ፡ ወል
ደ ፡ በጥሪቅ ፤ መሕቡብ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ዘመንበጣ ፤ ዮሐንስ ፡ አፈ ፡ ወርቅ ፤ ኤጲፋንዮስ ፡ ዘቆጵሮ
ስ ፤ ጽሚዳውያን ፡ ናቸው ። (ኤጲፋንዮስ ፡ እንደነጓውሎስ ፡ ምሁረ ፡ ኦሪት ፡ የነበረ ፡ አይሁዳዊ ፡
ሊቅ ፡ ነው ፤ ጌታ ፡ በታምራት ፡ ማርኮታል) ። አቡሻህር ፡ ባ፵፯ኛው ፡ አንቀጽ ፡ ምስክር ፡ አድር
ጎ ፡ ኹሉንም ፡ ባንድነት ፡ ጠቅሏቸዋል ፤ ቍጥራቸውንም ፡ ከሠንጠረዙ ፡ ውስጥ ፡ አግብቶታል ፤
፯ተኛው ፡ ባለታሪክ ፡ ግን ፡ ርሱው ፡ ራሱ ፡ ነው ። ፯ኛም ፡ ሉቃስ ፡ ወንጌላዊ ፡ በርኖው ፡ ምዕራ
ፍ ፡ (ቍ፴፭ ፡ ፴፯) የክርስቶስን ፡ ትውልድ ፡ አሻቅቦ ፡ ከርሱ ፡ ከዳግማይ ፡ አዳም ፡ ተነሥቶ ፡ እስ
ከርሷው ፡ አዳም ፡ ሲቈጥር ፤ ዔቦርን ፡ ወልደ ፡ ሳላሕ ፤ ሳላሕን ፡ ወልደ ፡ ቃይናን ፤ ቃይናንን ፡
ወልደ ፡ አርፋክስድ ፡ ብሎ ፡ ኦሪተ ፡ አይሁድን ፡ አበጥልሎ ፡ እንደ ፡ ኩፋሌና ፡ እንደ ፡ ኦሪተ ፡
ጽርእ ፡ ፪ቃይናን ፡ ይጥፋል ። ኢትዮጵያ ፡ ዘመነ ፡ ብሉይን ፡ እንዲኸ ፡ አስተካክላ ፡ ፭ሺሕ ፡
ካ፭፻ ፡ ብላ ፡ ስትቈጥር ፤ ዘመነ ፡ ሐዲሳ ፡ ልዩ ፡ ኹኖ ፡ ከግብጽ ፡ በቀር ፡ ከማንም ፡ ቍጥር ፡ አይ
ገጥምም ፤ ከሌሎች ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ከምሥራቆችም ፡ ከምዕራቦችም ፡ ወትሮ ፡ ፯ዓመ
ት ፡ ታጉድላለች ። ምክንያቱም ፡ ባለታሪኮችን ፡ ትታ ፡ ወንጌል ፡ ተርጓሚችን ፡ ስለ ፡ ተከተለች ፡
ይመስላል ። በምሥራቅም ፡ በምዕራብም ፡ ያሉ ፡ መተርጕማን ፡ (ማቴ፳፬ ፡ ፪) ኢይትንደግ ፡ ዝ
የ ፡ እብን ፡ ዲበ ፡ እብን ፡ ያለውን ፡ ሲተረጕሙ ፡ በዘመን ፡ ቍጥር ፡ አልተስማሙም ፤ እኩሌቶ
ች ፡ ከዕርገት ፡ በኹዋላ ፡ በ፴ኛ ፤ ከልደት ፡ በኹዋላ ፡ በ፫ ፡ ይላሉ ፤ እኩሌቶች ፡ በ፷ኛ ፡ ይላሉ ፤
ኢትዮጵያም ፡ ሕጹጽ ፡ ትታ ፡ ከልደት ፡ በኹዋላ ፡ በ፫ ፤ ከዕርገት ፡ በኹዋላ ፡ ባ፵ ፡ ትላለች ። ባ
ለታሪኮች ፡ ግን ፡ እንዳንድ ፡ ልብ ፡ መክሪ ፡ እንዳንድ ፡ ቃል ፡ ተናጋሪ ፡ ኹነው ፡ ስዓት ፡ ደቂቃ ፡

ኻ ፡ ኹለተኛውን ፡ ቃይናን ፡ በሞራሽ ፡ ፍቀው ፡ ከአዳም ፡ እስከ ፡ አብርሃም ፡ ፲፯፻፵፱ ፡ ዓመ
ት ፡ አጕድለዋል ፤ በግእዙና ፡ ባማርኛው ፡ ኦሪት ፡ ተመልክት ። ኦሪተ ፡ አይሁድን ፡ የተቀበሉ ፡ ክ
አዳም ፡ እስከ ፡ ክርስቶስ ፡ ፬ሺሕ ፡ ያኽል ፡ የሚሉበት ፡ ምክንያቱ ፡ ይኽ ፡ ነው ። ኦሪታችን ፡
ከሰብዓ ፡ ሊቃናት ፡ ትርጓሜ ፡ ከጥንታዊው ፡ ጽርእ ፡ መቀዳቱን ፡ አስቀድመን ፡ ተናግረናልና ፤ ስ
ለዚኽ ፡ እናትና ፡ ልጁን ፡ ፭ወገን ፤ ኦሪተ ፡ አይሁድን ፡ ፭ወገን ፡ አድርገን ፡ ልዩንታቸውን ፡ እስ
ክ ፡ ጣፍ ፡ እስከ ፡ መጨረሻ ፡ ዘርዝረን ፡ ደምረን ፡ እናሳያለን ። ፭ወገን ፡ ለኾኑት ፡ ለናትና ፡ ል
ጁም ፡ ለጽርኡና ፡ ለግእዙ ፡ ኦሪት ፡ ካራት ፡ ላይ ፡ ጥቂት ፡ ልዩነት ፡ አሳቸው ፤ ጽርኡ ፡ ከግእዙ ፡
፷፭(26) ዓመት ፡ ያተርፋል ። የኹዋላ ፡ ፀራሚዎች ፡ ወይም ፡ የግእዝ ፡ ጣሮች ፡ በአኃዝ ፡ ሞክሼ
ና ፡ በግድፈት ፡ የተሳሳቱበት ፡ ይመስላል ፤ ጽርኡ ፡ እንዳይታማ ፡ በንባብ ፡ ውስጥ ፡ ያለን ፡ ቍጥ
ር ፡ ኹሉ ፡ እንደ ፡ ዕብራይስጥ ፡ በፊደላት ፡ እንጂ ፤ እንደ ፡ ግእዝ ፡ በአኃዝ ፡ አይጥፍም ። የግእ
ዝ ፡ ጣፊ ፡ ግን ፡ ስንኳን ፡ ቍጥሩንና ፡ ቍጥር ፡ የሌለውን ፡ በፊደል ፡ ሊጣፍ ፡ የሚገባውን ፡ ስ
ም ፤ የአምላክ ፡ ኻያ ፡ እንደ ፡ ግለት ፡ ፰ኤል ፡ እያለ ፡ ይጥፋልና ፤ ሊገድፍና ፡ ሊስት ፡ ይችላል ፤
ጠባቂና ፡ ክልካይ ፡ የለውም ። ከዚኽ ፡ ይልቅ ፡ ደግሞ ፡ ባገራችን ፡ ጥፈትና ፡ ትምርት ፡ ተባብረ
ው ፡ ተጣፍረው ፡ ባንድ ፡ ሰው ፡ እጅ ፡ አይገኙምና ፤ ሳይማሩና ፡ ሊቅ ፡ ሳይኾኑ ፡ ጥፈት ፡ ብቻ ፡
ማወቅ ፡ ክስሕተት ፡ ክግድፈት ፡ አያድንም ። ተምሮም ፡ ጥፈት ፡ አለማወቅ ፡ እንደ ፡ ኽባ ፡ እን
ዳይን ፡ ስዉር ፡ መኾን ፡ ነውና ፤ በትምርት ፡ ብቻ ፡ እንዲኽም ፡ የሚል ፡ አብነት ፡ ይገኛል ፡ እያ
ሉ ፡ ያኑ ፡ የተጣፈውን ፡ ከመተርጕም ፡ በቀር ፤ መጻሕፍትን ፡ ማረም ፡ መጠንቀቅ ፡ አይቻልም ።
መጻሕፍትንም ፡ ፈጽሞ ፡ ለማረም ፡ ለመጠንቀቅ ፤ ሐሳባቸውን ፡ ለማወቅ ፡ ከባሕረ ፡ ምስጢሩ ፡
ለመጥለቅ ፡ የተቀዱበትን ፡ ምንጫቸውን ፡ ማየት ፡ ያስፈልጋል ፤ ምንጫቸውና ፡ የምንጫቸው
ም ፡ ስም ፡ ይኽ ፡ ነው ፤ የብሉይ ፡ ኪዳን ፡ ምንጭ ፡ ዕብራኒ ፤ የሐዲስ ፡ ኪዳን ፡ ምንጭ ፡ የኖኒ ።

ኦሪት ፡ ዘፍጥረት ፡ ምዕራፍ ፡ ፭ ።

(ኦሪተ ፡ ሊቃናት)	(ኦሪተ ፡ አይ)	(ኦሪተ ፡ ሊቃ)	(ኦሪተ ፡ አይ)
ቍ፪ -አዳም ፡ ሴትን ፡ በ፪፻፴ ።	በ፪፴ ።	»፲፪-አርፋክ ፡ ቃይናንን ፡ በ፪፴፭ ።	(ፍሑቅ)
»፮ -ሴት ፡ ሄኖስን ፡ በ፪፻፭ ።	በ፪፭ ።	»፲፫-ቃይና (አርፋ) ሳላሕን ፡ በ፪፴ ።	በ፴፭ ።
»፱ -ሄኖስ ፡ ቃይናንን ፡ በ፲፻ ።	በ፺ ።	»፲፬-ሳላሕ ፡ ዔቦርን ፡ በ፪፴ ።	በ፴ ።
»፲፪-ቃይና ፡ መላልኤልን ፡ በ፪፫ ።	በ፷ ።	»፲፯-ዔቦር ፡ ፋሌግን ፡ በ፪፴፬ ።	በ፴፬ ።
»፲፭-መላል ፡ ያሬድን ፡ በ፪፷፭ ።	በ፷፭ ።	»፲፰-ፋሌግ ፡ ራግውን ፡ በ፪፴ ።	በ፴ ።
»፲፰-ያሬድ ፡ ሔኖክን ፡ በ፪፷፪ =	በ፪፷፪ ።	»፳ -ራግው ፡ ሴሩግን ፡ በ፪፴፪ ።	በ፴፪ ።
»፳፭-ሔኖክ ፡ ማቱሳላን ፡ በ፪፷፭ ።	በ፷፭ ።	»፳፪-ሴሩግ ፡ ናኮርን ፡ በ፪፴ ።	በ፴ ።
»፷፭-ማቱሳላ ፡ ላሜኽን ፡ በ፪፻፸፯ =	በ፪፻፸፯ ።	»፷፱-ናኮር ፡ ታራን ፡ በ፪፻ (በ፫፻)።	በ፷፻ ።
(ጽርኡ ፡ ግን ፡ በ፪፷፯ ፡ ይላል)		(ጽርኡ ፡ ግን ፡ ፻፫፻ ፡ ይላል)	
»፷፯-ላሜኽ ፡ ኖህን ፡ በ፪፻፹ =	በ፪፻፹ ።	»፸፭-ታራ ፡ አብርሃምን ፡ በ፪ ፡ ዓ ።	በ፫ ፡ ዓ ።
(ጽርኡ ፡ ግን ፡ በ፪፻፷፰ ፡ ይላል)		(ጽርኡ ፡ ግን ፡ በ፫ ፡ ይላል)	
»፭፪-ኖህ ፡ ሴምን ፡ ባ፭፻ ፡ ዓ ፡ ወ = ባ፭፻ ።		ድሙር ፡ ከአዳም ፡ እስከ ፡ አብ ድ ፡ ፲፯፻፴፯ ፡	
(ምዕራፍ ፡ ፲፩)		ርሃም ፡ ፪ሺ ፡ ከ፪፻፹፯ ፡ (3386)	(1637)
ቍ፲ -ሴም ፡ አርፋክስድን ፡ በ፪ = በ፪ ።			

ጽርኡ ፡ ከግእዙ ፡ ፭፭ ፡ ዓመት ፡ ያተርፋልና ፤ ፭፭ን ፡ ክ፹፭ ፡ ቢጨምሩ ፡ ፪ሺ ፡ ካ፹፻፸፱ ፡ ዓ
መት ፡ ይኾናል ። አዶተ ፡ አይሁድ ፡ ያጐደለው ፡ እንደ ፡ ግእዙ ፡ ሺ ፡ ፲፯፻፵፱ ፡ (1749) ። እንደ ፡

ሳይተዉ ፤ የነገሥታቱን ፣ ዘመን ፣ በወርኃ ፣ በዕለት ፣ ዘርዝረው ፣ ደምረው ፣ ከዕርገት ፣ በኹዋላ ፣ ባ፸፱ ፣ ከልደት ፣ በኹዋላ ፣ በ፼፯ ፣ ጠፋች ፣ ብለው ፣ ጥፈዋል ። የባለታሪክ ፣ አባት ፣ (ዩሲፉስ) ዮሴፍ ፣ ነው ፤ ርሱ ፣ አስቀድመን ፣ እንደ ፣ ተናገርን ፣ ከፍጥረተ ፣ ዓለም ፣ እስከ ፣ ጥጦስ ፣ ፭ሺሕ ፣ ከ፯፻፸፭ ፭ ዓመተ ፣ ወርኃ ፣ ብሏል ። አቡሻህርም ፣ ባ፲፱ኛው ፣ አንቀጽ ፣ ከዮሴፍ ፣ መጽሐፍ ፣ ከ፹ኛው ፣ ክፍል ፣ ጠቅሶ ፤ ወክን ፣ ውዕየታ ፣ ለቀሥጦስ ፣ በጎምሳ ፣ ውጎምስቱ ፣ ምእት ፣ ሰብዓ ፣ ወሰ ብዐቱ ፣ (፶፭፱፹፯) ዓመት ፣ ወሓያዊት ፣ እምፍጥረተ ፣ ዓለም ፣ አመ ፣ ፀሡሩ ፣ ለጎምስ ፣ ወርኃ ፤ ወ አመ ፣ ተሱው ፣ ለሠርቀ ፣ ረገጠ ፣ በጎምሳ ፣ ወሰብዐቱ ፣ ምእት ፣ አርብዓ ፣ ወሰመንቱ ፣ (፶፭፱፸፯) ዓመት ፣ ወርኃዊት ፣ ይላል ፤ ጎምስ ፣ ወርኃ ፣ ረገጠ ፣ ያለውም ፣ ነሐሴን ፣ ነው ። ፫ኛም ፣ ሮብ ራክ ፣ የሚባል ፣ ባለታሪክ ፣ በክርስቲያን ፣ ቍጥር ፣ ክልደት ፣ በኹዋላ ፣ በ፼፯ ፣ ጠፋች ፣ ይላል ። ፬ኛም ፣ በኹዋላ ፣ ዘመን ፣ የተነሣ ፣ ግሬጽ ፣ የሚባል ፣ አይሁዳዊ ፣ በታሪኩ ፣ እንደዚኹ ፣ ይላል ። ከአይሁድና ፣ ካገራቸው ፣ ጥፋት ፣ በኹዋላ ፣ ወይም ፣ ከዚያ ፣ በፊት ፣ ሌላ ፣ ፪ኛ ፣ የሚያሳስት ፣ ቍጥር ፣ ስለሌለ ፤ ኢትዮጵያ ፣ ከዘመን ፣ ሐዲስ ፣ የምታጐድለው ፣ ያ ፣ ፯ዓመት ፣ ይኸ ፣ እንደ ፣ ኾነ ፣ በግልጥ ፣ ይታወቃል ። ከዕርገት ፣ በኹዋላ ፣ ያለዉን ፣ ፵፱ቱን ፣ ዓመት ፣ ፱ቱን ፣ ትታ ፣ ፵ ፣ እንዳለ ችው ፤ ፼፯ቱንም ፣ ፯ቱን ፣ ትታ ፣ ፼ ፣ ብላዋለች ። ይኸም ፣ ልማድ ፣ ዓመቱን ፣ በወር ፣ ስንቈጥር ፣ ጳግሜን ፣ ስለ ፣ ሕጸጿ ፣ በናሱ ፣ ላይ ፣ ትተን ፣ ፲፱ወር ፣ እንደምንለው ፣ ነው ፤ ሊቃውንትም ፣ እ ነቅዱስ ፣ ኤፍሬም ፣ ፭ቱን ፣ ቀን ፣ ትተው ፤ ተጸውረ ፣ በክርሣ ፣ ተስፀተ ፣ አውራን ፣ የሚሉት ፣ ይ ኽነን ፣ ይመስላል ። ሕጹጽ ፣ ትዩና ፣ ሕጹጽ ፣ መልዶ ፣ መቀሥጠር ፣ ከሰውና ፣ ከግዜር ፣ የተገኘ ፣ የመጽሐፍ ፣ ልማድ ፣ ነው ፣ (ዘፍ፲፭ ፣ ፲፫ ። ዘፀ፲፪ ፣ ፵ ። ጥበ፯ ፣ ፪) ። አንዳንድ ፣ የኤውሮፓ ፣ ሰዎች ፤ ድሜጥሮስ ፣ ዓመተ ፣ ዓለምን ፣ ባ፭፻ ፣ ቀሩና ፣ ሲሰፍር ፣ ሲቈጥር ፣ ዘመነ ፣ ብሉይ ፣ ፭ሺ ፣ ካ፬፻፸፪ ፣ ቢኾንበት ፣ ፭፻ ፣ እንዲመላለት ፣ ፰ቱን ፣ ዓመት ፣ ከላይ ፣ ከዘመነ ፣ ሐዲስ ፣ አውርደ ፣ ለታችኛው ፣ ተውሳክ ፣ አድርጎታል ፣ ብለው ፣ ያወራሉ ፤ የመላ ፣ የግምት ፣ አንጋገር ፣ ነው ፤ የተሣ ልቆም ፣ ይመስላል ፤ እውነትስ ፣ ቢኾን ፣ ባቡሽሀር ፣ በመርሐ ፣ ዕዉር ፣ ይጣፍ ፣ ነበር ። ካገራችን ም ፣ ሰዎች ፤ የምሥራቅ ፣ አብያተ ፣ ክርስቲያናት ፣ ኦርቶዶክሳውያን ፤ ዮርያና ፣ አርመን ፣ ግፊክ ፣ ሌሎ ቹም ፣ ኹሉ ፣ እንደኛና ፣ እንደ ፣ ግብጥ ፣ ፯ዓመት ፣ ያጉድላሉ ፣ ብለው ፣ የሚተርኩ ፣ አሉ ፤ ምሥ ራቃውያን ፣ ግን ፣ ስንኳን ፣ ፯ዓመት ፤ ፯ወር ፣ ፯ቀን ፣ አያጐድሉም ፤ ከበዓላትም ፣ በቀር ፣ በዘመ ን ፣ ቍጥር ፣ ከምዕራብ ፣ እንጂ ፣ ከኛ ፣ ጋራ ፣ አይገጥሙም ። ምሥራቆች ፣ ከምዕራቦች ፣ የሚለ ዩ ፣ በ፪ ፣ ነገር ፣ ነው ፤ በወር ፣ ብተትና ፣ በበዓላት ፣ ብቻ ፤ ይኸነኑም ፣ ባለቤታቸው ፣ በቃል ፣ በስ ንክሳር ፣ ይመሰክራሉ ። ዛሬም ፣ በጥራሽ ፣ በብተትና ፣ በበዓላት ፣ ከምዕራቦች ፣ ተሰማምተው ፣ አንድ ፣ ወገን ፣ ኹነዋል ፤ መቹም ፣ መች ፣ ቢኾን ፣ ከኛ ፣ ጋራ ፣ የብተትና ፣ የቍር ፣ አንድነት ፣ የላቸውም ። የግብጦችም ፣ ታሪክ ፣ ፪ ፣ ነው ፤ ዓመተ ፣ ሥጋዌና ፣ ዓመተ ፣ ሰማዕታት ፤ ከሥጋ ዌም ፣ ይልቅ ፣ የሚጥፉና ፣ የሚቈጥሩ ፣ በሰማዕታት ፣ ነው ፤ ምክንያቱም ፣ ፯ቱን ፣ ዓመቶች ፣ ማ ጕደልንና ፣ መጨመርን ፣ ኹለቱንም ፣ ስለ ፣ ነቀፉ ፣ ነው ፣ ይባላል ፤ ይኸ ፣ ባይኾን ፣ ግን ፣ ጕን ዱን ፣ ትተው ፣ ወዳጽቁ ፣ ባልሄዱም ። ከክርስቶስ ፣ እስከ ፣ ዲዮቅልጥያኖስ ፣ እንደኛና ፣ እንደ ፣ ግብጦች ፣ ቍጥር ፣ ፪፻፸፯ ፣ ነው ፤ እንደሌሎቹ ፣ ግን ፣ ፯ዓመት ፣ ሲጨመርበት ፣ ፪፻፹፫ ፣ ወይ ም ፣ ፹፬ ፣ ይኾናል ። **በዘንዜክር ፣ ሐሳበ ፣ ጸሐፍት ፣ ወፈሪሳውያን ፣ ይቤሉ ፣ አኀው ፣ አይሁድ ፣ ወፈላስያን ፤ እምፍጥረተ ፣ ዓለም ፣ እስከ ፣ ዮም ፤ ኀምሳ ፣ ወስድስቱ ፣ ምእት ፣ ተስዓ ፣ ወአርባእቱ ፣ (፶፭፻፺፭) ዓመት ። ይኸውም ፣** ፭ሺሕ ፣ ከ፭፻፹፬ ፣ ማለት ፣ ነው ፤ አኹን ፣ ዛሬ ፣ ይኸ ፣ መጣፍ ፣ በታተመበት ፣ **በዘመነ ፣ ማ**

ርቆስ ፣ ወንጌላዊ ፤ አመ ፣ ሳድስ ፣ ዓመተ ፣ መንግሥቱ ፣ ለኀይለ ፣ ሥላሴ ፣ ኬንያ ፣ ንጉሠ ፣ ነገሥት ፣ ዘኢትዮጵያ ። ዳግመኛም ፣ ይኸ ፣ ፲፱ቱ ፣ ፮ዓመት ፣ ተጨ ምሮበት ፣ ፯፻ ፣ ከመላ ፣ በኹዋላ ፣ እስከ ፣ ፯ሺ ፣ ያለው ፣ ፲፻፱ው ፣ ዘመን ፣ መሲሕ ፣ ነው ፣ ይላሉ ፤ ይ ኸውም ፣ በዕዐ ፣ በለስ ፣ የተመለሱ ፣ አይሁድ ፣ ከአሕዛብ ፣ እጅ ፣ ወጥተው ፣ አገራቸው ፣ ገብተው ፣ እንደ ፣ ቀድሞቸው ፣ ንጉሥ ፣ ቀብተው ፣ የሚያነግሡበት ፣ ባለቃቸው ፣ የሚታዘዙበት ፣ የነጻነት ፣ ወሬት ፣ ማለት ፣ ነው ፤ ጌታችንና ፣ ጳውሎስ ፣ ዮሐንስ ፣ ሌሎችም ፣ ነቢያት ፣ የተናገሩት ፣ (፱ተሰ ፱ ፣ ፭-፲፱ ። ራእ፲፱ ፣ ፲፭ ፣ ፳) ፣ ሥጋዊውና ፣ ምድራዊው ፣ ሐሳዊው ፣ መሲሓቸው ፣ ግን ፣ የሚ ገለጥና ፣ የሚሰወር ፣ ባ፵ ፣ ዘመን ፣ ነው ፣ ይባላል ። ፪ኛ ፣ ደግሞ ፣ ሺሕ ፣ ዓመት ፣ ሊነግሥ ፣ በጭ ራሽ ፣ ይመጣል ፣ ይላሉ ። የነግ ፣ ማነግም ፣ ጦርነት ፤ ወትከውን ፣ ሀገር ፣ ወባይ ፣ ሠለስተ ፣ መክፈልተ ፣ እንደ ፣ ተባለ ፣ (ራእ፲፮ ፣ ፲፱) ፤ በቮቱ ፣ ነገድ ፣ ስም ፣ በሴምና ፣ በክም ፣ በያፈት ፤ ወ ይም ፣ ነቢዩ ፣ ስማቸውን ፣ ጠርቶ ፣ በተናገራቸው ፣ በቮቱ ፣ ደቂቀ ፣ ያፈት ፣ በማኅግ ፣ በቱባል ፣ በ ሞሳኽ ፣ (ዘፍ፲ ፣ ፮ ፣ ፱ ። ሕዝ፴፰ ፣ ፱) ከሦት ፣ ተከፍሎ ፣ በቀርስ ፣ በምሳ ፣ በራት ፣ ተመስሎ ፣ የ ቍርሱ ፣ ምሳሌ ፣ ተፈጽሟል ፤ (ማቴ፳፬ ፣ ፮-፳) ። የምላውና ፣ የራቱም ፣ ተራና ፣ ጊዜ ፣ ይጠብቃ ል ። ኽምሳ ፣ እስከ ፣ ራት ፣ ያለው ፣ ጊዜም ፣ ሐሳዊ ፣ መሲሕ ፣ እስኪነግሥ ፣ ከምሳው ፣ ግብገር ፣ ለ ቀሩት ፣ ዕረፍትና ፣ ተድላ ፣ ያሳያል ። ከራት ፣ በኹዋላ ፣ ግን ፣ ተኝቶ ፣ ተነሥቶ ፣ በክርስቶስ ፣ ዙፋን ፣ ፊት ፣ መቆም ፣ ነው ፣ (ማቴ፳፭ ፣ ፴፩-፴፫ ። ሮሚ፲፬ ፣ ፲) ። ሺሕ ፣ ዓመትና ፣ መዠመሪያ ፣ ሕይወ ት ፣ (ትንግኤ) የተባለውም ፣ (ራእ፳ ፣ ፩-፯) ፣ በቅዱሳን ፣ አበው ፣ ትርጓሜ ፣ ሺሑ ፣ ዓመት ፣ ዘመ ን ፣ ሥጋዌ ፤ ትንግኤዉም ፣ ትንግኤ ፣ ልቡና ፣ ተብሏል ። ጻድቃን ፣ ምእመናን ፣ በጥምቀት ፣ በቍ ርባን ፣ የክርስቶስ ፣ ሕዋሳት ፣ ስለ ፣ ኾኑ ፣ በትንግኤዉና ፣ በርገቱ ፣ ምስጢረ ፣ መንግሥቱን ፣ ተሳት ፈው ፣ ዛሬዉኑ ፣ ከርሱ ፣ ጋራ ፣ አሉና ፤ ሕያዋን ፣ እንጂ ፣ ሙታን ፣ አይባሉም ፣ (ማቴ፳፪ ፣ ፴፪ ። ኤፈ፪ ፣ ፬-፯) ። ሺሑም ፣ ዓመት ፣ ዘመነ ፣ ሥጋዌ ፣ እንደ ፣ ኾነ ፤ ወሶበ ፣ ጎልቀ ፣ ዐወርቱ ፣ ምእ ት ፣ ዓመት ፣ ይትፈታሕ ፣ ሰይጣን ፣ እምነ ፣ ሞቅሑ ፣ ተብሎ ፣ ከ፮ ፣ እስካ፲ ፣ የተጣፈው ፣ ቃል ፣ ያስ ረዳል ። አይሁድ ፣ ግን ፣ ፊተኛውን ፣ ትንግኤና ፣ ምጽአት ፣ ዘመነ ፣ ሥጋዌን ፣ ስለ ፣ ካዱ ፣ ዘመነ ፣ አ በውን ፣ ሲከፍሉ ፣ ፻፻ዉን ፣ ከፊት ፣ ወደ ፣ ኹዋላ ፣ እንዳዞሩት ፤ ሺሑን ፣ ዓመት ፣ ደግሞ ፣ እንደዚ ኹ ፣ አዙረው ፣ ለትንግኤና ፣ ለሐሳዊ ፣ መሲሕ ፣ ይሰጡታል ። ፯ኛው ፣ ሺ ፣ እንደ ፣ ቅዳሜ ፣ ነው ፤ መሲሓች ን ፣ በመጣ ፣ ጊዜ ፣ ሌላው ፣ ሰው ፣ ኹሉ ፣ ዐልቆ ፣ እስራኤል ፣ ብቻ ፣ ይነሡና ፤ ከርሱ ፣ ጋራ ፣ ንግሠ ው ፣ ሺሕ ፣ ዓመት ፣ ከኖሩ ፣ በኹዋላ ፣ ሌሎቹ ፣ ሙታን ፣ ይነሣሉ ፣ ብለው ፣ ሌላም ፣ ብዙ ፣ ተረት ፣ ጨምረው ፣ ግልብጦ ፣ ወሬ ፣ ያወራሉ ። (ሙሾ ፤ መነኮሲት ፣ አርማዝ ፣ በምጥ ፣ ስለ ፣ ሞተች) ፤ አንች ፣ ሞኝ ፣ አንች ፣ ሞኝ ፣ አንች ፣ ሞኝ ፣ ተላላ ፤ የኹዋላውን ፣ በፊት ፣ የፊቱን ፣ በኹዋላ ።

(፴፮)

ውዳሴ ፣ አምላክ ፣ ወአርጋኖን ፣ ስም ፣ ቡሩክ ፤ አው ፣ መዝሙር ፣ ወ ቅዳሴ ፤ ወአመ ፣ አክ ፣ ድርሳን (ዲስኩር) ፣ በእንተ ፣ ቅድስት ፣ ሥላሴ ፣ እ ምቃለ ፣ ነቢያት ፣ ወሙሴ ። ነቢያትሰ ፣ እሙንቱ ፣ ስኩራን ፣ መንፈስ ፤ ም ሉኣን ፣ ሞገስ ፤ አቅርንተ ፣ ሥሉስ ፣ ቅዱስ ፤ በከመ ፣ ይቤ ፣ ዝፀዕ ፣ አባ ፣ ጊዮርጊስ ። ስብሐት ፣ ለአብ ፣ ሠራዔ ፣ መዋዕል ፣ ወአዝማን ፣ በምዙ ናኑ ፣ ባሕቲቱ ፤ አኰቴት ፣ ለወልድ ፣ የማኑ ፣ ወመዝራዕቱ ፤ ዕበይ ፣ ወክ

ብር ፡ ለመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ሕይወቱ ፤ እስመ ፡ ብሂለ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወ መንፈስ ፡ ሥሉስ ፡ ዕሩይ ፤ ዘከመ ፡ ፀሓይ ፡ ወብርሃን ፡ ወዋዕይ ፤ ኅቡረ ፡ ህላዌ ፡ ወባሕርይ ፤ ዘኢይትከፈል ፡ ወዘኢይትሌለይ ፤ በከመ ፡ ይቤ ፡ ሙ ሴ ፡ ነቢይ ፤ ወባዕዳንሂ ፡ ነቢያት ፡ በቃለ ፡ ግናይ ፤ ስማዕ ፡ እስራኤል ፤ እ ግዚአብሔር ፡ አምላክነ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዋሕድ ፡ (ዘዳ፮ ፡ ፭ ። ማር፲፪ ፡ ፳ ፱ ፡ ፴፪ ። ዮሐ፲፯ ፡ ፫ ። ፩ቆሮ ፡ ፰ ፡ ፬ ፡ ፮) ። ወበዕብራይስጢ ፡ ይሰመይ ፡ ኤሎሂ ም ፡ ወአዶናይ ፤ ይሆዋ ፡ ወሻዳይ (ዳን፡አጥብ) ፤ ኤሎሂምሰ ፡ ወአዶናይ ፡ አም ላክ ፡ ሐዲስ ፡ ወብሉይ ፤ ይተረጐም ፡ በክልኤ ፡ ፍና ፤ በትሥልስት ፡ ወ በዋሕድና ። ቀዳሚ ፤ አምላክ ፡ ወእግዚአ ፡ ዘከመ ፡ ዋሕድና ፡ መለኮቱ ፡ ወሥልጣኑ ፡ ወጠባይዑ ፡ (ዘዕ፩ ፡ ፩ ፡ ፪ ፡ ፩) ። ዝኒ ፡ በተሊወ ፡ አንቀጽ ፡ ባ ሕቲቱ ፡ ወአኮ ፡ በተሊወ ፡ አካል ፡ ሠለስቱ ፤ እስመ ፡ እንዘ ፡ ዋሕድ ፡ ሥ ሉስ ፡ እንበለ ፡ ሕጸጽ ፤ ወእንዘ ፡ ሥሉስ ፡ ዋሕድ ፡ ዘእንበለ ፡ ቢጽ ፤ አን ቀጽኒ ፡ ይተሉ ፡ ህላዌ ፡ ወአኮ ፡ አካለ ፤ ዘውእቱ ፡ ብሂል ፡ መለኮ ፡ ፈጠ ረ ፡ ነበበ ፤ ወዘይመስሎ ፡ ለዝንቱ ። ወካዕበ ፡ ይተረጐም ፡ አማልክተ ፡ ወ አጋዕዝተ ፡ ዘከመ ፡ ትሥልስተ ፡ አካሉ ፡ ወገጹ ፡ ወመልክኡ ፤ ዝኒ ፡ በተ ሊወ ፡ አካል ፡ ወገጽ ፡ ተወከፈ ፡ አንቀጽ ፡ ወአኮ ፡ በተሊወ ፡ ባሕርይ ፡ ወ አንቀጽ ፤ እስመ ፡ ትርጓሜሁ ፡ ለኤሎሂም ፡ በሕገ ፡ ረበናት ፡ ወሰዋስው ፡ አማልክት ፡ ውእቱ ፡ ከመ ፡ ዘብዙኃን ፡ ዕደው ፡ (ዘፀ፳፩ ፡ ፯ ። መዝ፹፪ ፡ ፮ ። ዮ ፩ ፡ ፲) ። ወመብዝኂቱኒ ፡ ይእቲ ፡ ዮድ ፡ ዘሁሎ ፡ ታበዝኅ ፡ ወታፈደፍድ ፤ ወታብህለነ ፡ ለነሂ ፡ መላኪ ፡ መላክያን ፤ ፈጣሪ ፡ ፈጣርያን ፤ ነባቢ ፡ ነባብ ያን ፤ በእንተ ፡ ዘተሰውጠት ፡ ቦቱ ፡ ምስለ ፡ ሚም ፡ (ይም) ። ባሕቱ ፡ ት ትወኅጥ ፡ ወኢትትነከይ ፡ በንባብ ፤ ዘውእቱ ፡ ኤሎሂም ፡ በከመ ፡ ጸሐፍ ነ ፡ ዝየ ፤ ወአከ ፡ ኤሎሂይም ። ወአሐዱሰ ፡ ውእቱ ፡ ኤል ፡ አው ፡ ኤሎሀ ፤ ወናሁ ፡ ሎቱ ፡ ስምዐ ፡ ጽድቅ ፤ ዐማኑኤል ፡ (ዒማኑኤል) ሚካኤል ፡ ወገ ብርኤል ፤ (ኤሊ) ኤሎሄ ። ወፍካሬሁኒ ፡ ለአዶናይ ፡ አጋዕዝትየ ፡ ብሂል ፡ ከመ ፡ ዘሠለስቱ ፡ አካል ፡ (ዘፍ፲፰ ፡ ፪ ፡ ፫ ። ፲፱ ፡ ፪ ። ኢሳ፮ ፡ ፫ ፡ ፰) ፤ ዝኒ ፡ ዘከመ ፡ ንባቡ ፡ ወቃሉ ፡ ገጸ ፡ በገጽ ። ወአሐዱሰ ፡ አዶን ፡ አዶኒ ፤ ወአከ ፡ አዶኒም ፡ ወአዶናይ ፤ እስመ ፡ ብሂለ ፡ አዶን ፡ ወአዶኒም ፡ ከመ ፡ ብሂለ ፡ ኤል ፡ ወኤ ሎሂም ፡ ዘውእቱ ፡ እግዚእ ፡ ወአጋዕዝት ፤ ወአዶኒሰ ፡ ውእቱ ፡ እግዚእየ ፡ ብሂል ። ይሆዋኒ ፡ እግዚእ ፡ ፍጹም ፡ ፍሉጠ ፡ ስም ፤ እግዚአ ፡ ሁሉ ፡ ዓ ለም ፤ ዘውእቱ ፡ ብሂል ፡ እግዚአብሔር ፡ ገባሬ ፡ ሰማያት ፡ ወምድር ። ወ

ሻዳይኒ ፡ አኃዜ ፡ ኩሉ ፡ ወከሃሌ ፡ ኩሉ ፤ ወሥሉጥ ፡ ላዕለ ፡ ኩሉ ። ኤሎ ሂምኬ ፡ በአማን ፡ አምላከ ፡ ፀሓይ ፡ ዘአስተርአዮ ፡ ሥሉሰ ፡ ለአብርሃም ፡ በቀትረ ፡ መዓልት ፤ ወተናገሮ ፡ ዋሕዶ ፡ ለሙሴ ፡ በነደ ፡ እሳት ፡ (ዘፍ፲፰ ፡ ፪ ። ዘፀፎ ፡ ፪-፯) ፡ እስመ ፡ አከ ፡ ክዱን ፡ ወስዉር ፡ ዘኢይትአመር ፡ ሥላሴ ፡ በመ ጽሐፈ ፡ ሙሴ ፤ ዳእሙ ፡ ጥዩቀ ፡ አእመርናሁ ፡ በአሪት ፡ ወበነቢያት ፡ ከ መ ፡ ዝንቱ ፡ ሥላሴ ፡ ውእቱ ፡ ኤሎሂም ፡ አኃዜ ፡ ኩሉ ፡ ዓለም ፤ ዋሕደ ፡ መለኮት ፡ ወኀይል ፡ ወሥሉሰ ፡ አካል ። ኤሎሂምኬ ፡ ውእቱ ፡ ዘበቃሉ ፡ ሰቀሎ ፡ ለሰማይ ፤ ወአጽንዓ ፡ ለምድር ፡ ዲበ ፡ ማይ ፤ ወበመንፈሱ ፡ ከነ ፡ ይጼልል ፡ መልዕልተ ፡ ማይ ፤ ለቀድሶተ ፡ ባሕር ፡ ቀዲሙ ፡ ከመ ፡ ንጠመ ቅ ፡ በስሙ ፤ (ዘፍ፩ ፡ ፩ ፡ ፪ ። ማቴ፳፰ ፡ ፲፱) ። ዘውእቱ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመ ንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አሐዱ ፡ አምላክ ፡ ወአሐቲ ፡ መንግሥት ፡ ወአሐቲ ፡ ሥ ልጣን ፡ ወአሐቲ ፡ ምኵናን ፡ በከመ ፡ ይቤሉ ፡ አበዊነ ፡ (ዘፍ፩ ፡ ፳፮ ። ፳፯ ። ፫ ፡ ፳፪ ። ፲፩ ። ፮ ። ዘጕ፮ ፡ ፳፬-፳፮ ። ኢሳ፮ ፡ ፫ ። ፵፮ ፡ ፲፩ ። ፳፭ ። ፩ ። መዝ፹፪ ፡ ፮ ። ኢ ኮነ ፡ ክልኤተ ፡ ወኢሠለስተ ፡ በመለኮቱ ፡ ወኀይሉ ፤ ወኢይትዌከፍ ፡ ተ ውሳከ ፡ ወኢሕጸተ ፡ ትሥልስተ ፡ አካሉ ፤ አላ ፡ ዘከመ ፡ ፀሓይ ፡ ወእሳት ፡ ወዘከመ ፡ ቀላይ ፡ አምሳሉ ፤ ቅዱስ ፡ ሥሉስ ፡ ይሆዋ ፡ እግዚአ ፡ ኩሉ ፡ ዘ ሀሎ ፡ ወይሄሉ ። ይሆዋኬ ፡ ወሻዳይ ፡ እግዚአብሔር ፡ አዶናይ ፤ ወጣኔ ፡ ኪ ዳን ፡ ብሉይ ፡ ዘኢይበሊ ፡ ወፈጻሜ ፡ ኪዳን ፡ ሐዲስ ፡ ገባሪ ፡ ወከሃሊ ፤ ዘ አክሀለነ ፡ በክሂሎቱ ፡ ወረድኦነ ፡ በረድኤቱ ፡ ጐልቈ ፡ ሥነ ፡ ፊደል ፡ ፍጥ ረቱ ፡ ወጢነ ፡ ወፈጽሞ ፡ በጽሑፍ ፡ ወበተርጕሞ ፤ አሜን ፡ (ዘፀ፲፱ ፡ ፭ ። ፳ ፱ ፡ ፳ ። ኤር፴፭ ፡ ፴፩-፴፪ ። ዘካ፱ ፡ ፲፩ ። ማቴ፳፰ ፡ ፳፲) ። ※ (ማስረጃ) በግእዝም ፡ የአም ላክ ፡ ዘይቤ ፡ እንደ ፡ ኤሎሂም ፡ ነው ፤ ምንም ፡ በልማድ ፡ አፈታት ፡ አንድ ፡ ቢባል ፡ የመለክ ፡ ብዝ ፡ ነውና ፤ በሰዋስው ፡ ሕግ ፡ ብዛትንና ፡ ውስጠ ፡ ብዙንትን ፡ ያሳያል ። ዘሩኑ ፡ አንቀጹ ፡ መ ሊክ ፡ መለክ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ጥሬውን ፡ መልክ ፡ መለክ ፡ ብሎ ፡ «መልክ ፡ ጼዲቅ ፤ መለክ ፡ ስንድ» ብሂውን ፡ አምላክ ፤ አማልክት ፡ (ወይም ፡ መለክን) ያሰኛል ፤ ይኽም ፡ ደብር ፡ ፈለግ ፡ ብሎ ፡ አድ ባር ፡ አድባራት ፤ አፍላግ ፡ አፍላጋት ፤ እንደ ፡ ማለት ፡ ነው ፤ መለክ ፡ አንድ ፤ አምላክ ፡ ብዙ ፤ አ ማልክት ፡ የብዙ ፡ ብዙ ፡ ይባላል ፤ ደብርና ፡ ፈለግም ፡ እንደዚኽ ፡ ነው ። ወረቡ ፡ መለክን ፡ ሲያ በዛ ፡ ሙሉነ ፤ ዕብራይስጡ ፡ ምላኪም ፡ ይላል ። ያንድነትና ፡ የሦስትነት ፡ ምስጢር ፡ ፍሬው ፡ ባሕርይና ፡ አካል ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ ባሕርይና ፡ አካልም ፡ ርስ ፡ በርሱ ፡ እንደ ፡ መሠረት ፡ እንደ ፡ ሕ ንጻ ፤ እንደ ፡ ሥርና ፡ እንዳጽቅ ፡ የተዋሐደ ፡ የተገናዘበ ፡ ኅቡርና ፡ ዕሙር ፡ ስለ ፡ ኾነ ፤ ጀነት ፡ ያ ለሦስትነት ፡ ይኸትም ፡ ያላንድነት ፡ ብቻ ፡ ብቻውን ፡ ሊጣፍ ፡ ሊነገር ፡ አይቻልምና ፤ ከዚኽ ፡ የ ተነሣ ፡ የንቢያት ፡ ቋንቋ ፡ ዕብራይስጥ ፡ የፈጣሪን ፡ ነገር ፡ ሲናገር ፡ የቃሉን ፡ ማሰሪያ ፡ አንቀጹን ፡ ያንድ ፡ ወንድ ፤ ስሚውንና ፡ ባለቤቱን ፡ አንቀጽ ፡ ተቀባዩን ፡ ብዙ ፡ ወንድ ፡ አድርጎ ፤ ባራኤ ፡ ኤ ሎሂም ፡ (ፈጠረ ፡ አምላክ) ። አማር ፡ (ይቤ) አደናይ ፡ እያለ ፡ ባንድና ፡ በብዙ ፡ ይናገራል ። ባራ

እና ፣ አማር ፣ አንድነቱን I ኤሎሂም ፣ አደናይ ፣ ሦስትነቱን ፣ ገልጠው ፣ አጐልተው ፣ ያስረዳሉ ። ፩ነት ፣ የባሕርይ ፣ ምስጢር I ሦስትነት ፣ የአካል ፣ ምስጢር ፣ ይባላል I ይኽም ፣ ዕብራይስጣዊ ፣ ቃል ፣ ሥላሴ ፣ ይሄሉ ፣ ዘልፈ ፣ በሥላሴው ። ንባርኮ ፣ ለአብ ፣ ወወልድ ፣ ወመንፈስ ፣ ክለው ፣ ክሊቃውንት ፣ ቃል ፣ ይስማማል I በብሉያትም ፣ ውስጥ ፣ በብዙ ፣ ቦታ ፣ እንደ ፣ ሊቅና ፣ እንደ ፣ ሐዲስ ፣ አብ ፣ ወልድ ፣ መንፈስ ፣ የሚል ፣ ስም ፣ ይገኛል ። ለስው ፣ ለመላእክት ፣ ሲነገር ፣ ግን ፣ አንቀጹ ፣ ያንድ ፣ የነበረው ፣ ተለውጠ I ኤሎሂም ፣ አቴም ፣ (አማልክት ፣ አንትሙ) ። አደናይ ፣ ሱፍና ፣ (አ ጋፅዝትየ ፣ ገሐሡ) እያለ ፣ የብዙ ፣ ይኽናል I ብዛቱን ፣ ሳይለቅ ፣ በአንቀጽ ፣ ብቻ ፣ መለየቱም ፣ ፭ ገጽ ፣ የሚሉ ፣ አይሁድን ፣ በጣም ፣ ያሳፍራል ። ርሳቸው ፣ ግን ፣ ፭ነትን ፣ ዐቅፈው ፣ ፫ነትን ፣ ነቅፈው ፣ አንዱን ፣ ወገን ፣ ብቻ ፣ ባሕርይና ፣ አንቀጽን ፣ ተከትለው I ኤሎሂም ፣ ማለት ፣ ስላጎቱታ ፣ ስለ ፣ ክበፊታ ፣ ነው ፣ እንጂ ፣ ስለ ፣ ፫ነት ፣ አይደለም ፣ ብለው ፣ ፈራሽ ፣ ሰው ፣ ሠራሽ ፣ ያልተገባ ፣ ምላሽ ፣ ይሰጣሉ I ኤሎሂም ፣ ማለት ፣ ቃለ ፣ አክብሮ ፣ ክኽነ I ፈጠረም ፣ ማለት ፣ አንቱ ፣ ብሎ ፣ አንተ ፣ እንደ ፣ ማለት ፣ ነውና I በግድ ፣ ቃለ ፣ አጎበሮ ፣ ይኽናል ። ወይም ፣ የግእዝ ፣ መዝሙር ፣ ዘእንበለ ፣ ይቁም ፣ አድባር ፣ እንደሚለው ፣ ንባብ ፣ ስሕተትና ፣ ጸያፍ ፣ ይባላል ። ዳግመኛም I ንግበር ፣ ሰብአ ፣ በአርአያን ፣ ወበአምሳሊን ። ናሁ ፣ አዳም ፣ ኮነ ፣ ከመ ፣ አሐዱ ፣ እምኔነ ። ንሁ ፣ ንረድ ፣ ወንክዐው ፣ ያሳቸው ፣ መላእክትን ፣ ነው ፣ ይሰኖ I ወዲያው ፣ ደግሞ ፣ ገድሎ ፣ እንደ ፣ ማዳን ፣ ሰብሮ ፣ እንደ ፣ መጠገን I የአዳም ፣ ተፈጥሮ ፣ በመላእክት ፣ አርአያና ፣ አምሳል ፣ ስለ ፣ ኽነ ፣ ምንም ፣ ራሱን ፣ ክመላእክት ፣ ውስጥ ፣ አግብቶ ፣ ንግበር ፣ ቢል I ክዚያው ፣ አያይዘ ፣ ወገብሮ ፣ ለአዳም ፣ ይላል ፣ እንጂ I ወገብርዎ ፣ አይልምና I መፍጠር ፣ የግዜር ፣ ብቻ ፣ ነው ፣ ብለው ፣ አስታና ፣ ጽድቅ ፣ ያትታሉ I ባ፭ራስ ፣ ፱ምላስ ። ስለ ፣ መሲሕም ፣ መከራ ፣ ስለ ፣ ቤዛነቱ ፣ (ኢሳ፶፫ ፣ ፭-፲፱) ነሥአ ፣ ደዌነ ፣ ወጸረ ፣ ሕማመነ ፣ ወበእንቲአነ ፣ ሐመ I ቀንዒነ ፣ እደውየ ፣ ወ እገርየ ፣ ያለውን I ሌላውንም ፣ ኹሉ ፣ የክርስቶስን ፣ ሥራና ፣ መከራ ፣ ለእስራኤል ፣ ሰጥተው ፣ ይ ፮ታሉ ። ይቤሎ ፣ እግዚእ ፣ ለእግዚእየ ፣ ንበር ፣ በየማንየ I አንተ ፣ ክህኑ ፣ ለዓለም ፣ በክመ ፣ ሚመቱ ፣ ለመልከ ፣ ጼዲቅ ፣ ያለውም I አብርሃምን ፣ ነው ፣ ይላሉ ። ዳንኤልም ፣ ስለ ፣ መሲሕና ፣ ስለ ፣ ሞቱ ፣ ሱባዔውን ፣ ቁጥሮ ፣ ትንቢቱን ፣ ሲናገር I ወእምድኅረ ፣ ስሳ ፣ ወክልኤቱ ፣ ሰንበት ፣ ይትቀተል ፣ መሲሕ I ወአኮ ፣ ለርእሱ ፣ ያለውን I ይጥሉበት ፣ ቢያጡ ፣ ለእግሪጳስ ፣ ሰጥተው ፣ ይፈ ታሉ ። መላእክትን ፣ እንደ ፣ ወልድና ፣ እንደ ፣ መንፈስ ፣ ቅዱስ ፣ የአብ ፣ ተባባሮች ፣ የአዳም ፣ ፈጣሮች ፣ በማድረግ ፣ ላይ ፣ እስራኤልን ፣ አለስሙና ፣ አለመልኩ ፣ የዓለም ፣ ቤዛ ፣ የአሕዛብ ፣ መድኀን I ዕሩቅ ፣ ብእሲ ፣ አብርሃምን ፣ በአብ ፣ ቀኝ ፣ ተቀማጭ ፣ የዘላለም ፣ ክህን I ተቀብያ ፣ የሌለው ፣ አግሪጳስን ፣ ቅቡዕና ፣ መሲሕ ፣ ቅዱስ ፣ ቅዱሳን ፣ ማለት ፣ በውነተኞቹ ፣ ዕብራውያን ፣ በንጻውስዮስ ፣ ዘንድ ፣ ከጥርስ ፣ ዐልፎ ፣ ዐይን ፣ የሚያስቅ ፣ ምፀትና ፣ ሥላቅ ፣ ቢባል ፣ እንጂ ፣ ቁም ፣ ነገርና ፣ ጽድቅ ፣ አይባልም I ምፀትንቱም ፣ ጊዮርጊስ ፣ ሊቀ ፣ መላእክት I ሚካኤል ፣ ሊቀ ፣ ስማዕታት ፣ እንደ ፣ ማለት ፣ ነው ። ከመዝሰ ፣ ግፍዕ ፣ እመ ፣ ተገብረ I አዕይንት ፣ ይስምዑ ፣ ኵሎ ፣ ነገረ I ወአእዛን ፣ ይርአዩ ፣ አድባረ ፣ (ቅኔ) ። ለብሉይና ፣ ለዕብራይስጥ ፣ ምንም ፣ ባላባቶች ፣ ቢኾኑ ፣ ሌላውን ፣ ትርጓሜ ፣ ያስጊጡትና ፣ ያስረግጡት ፣ እንጂ I የሥላሴንና ፣ የሥጋዌን ፣ ምሥጢር ፣ የመሲሕን ፣ ነገር ፣ እንደ ፣ ሐዋርያት ፣ በገባቡና ፣ ባገባቡ ፣ ፊት ፣ ለፊት ፣ አትንተው ፣ መተርጐም ፣ መፍታት ፣ ማየትና ፣ መስማት ፣ ማስተዋል ፣ መመልከት ፣ አልቻሉም I ዐይን ፣ ልባቸውን ፣ ስይጣንና ፣ ርግማን ፣ ስላወረው ፣ ቋንቋቸውና ፣ መጣፋቸው ፣ የቅርብ ፣ ሩቅ ፣ ስዉርና ፣ ድበቅ ፣ ኹኖባቸዋል ። (ምሳሌ) I ቀራንብት ፣ ጎቤሁ ፣ ለዐይን ፣ እንዘ ፣ ቅሩባን I ቀራንብተ ፣ ኢይኔጽር ፣ ዐይን ፣ (ኢሳ፭ ፣ ፱ ፣ ፲) ። የፈጣሪን ፣ ሥራ ፣ ስፍጡራን ፣ ሰጥቶ ፣ መተርጐም I አባቶቻቸው ፣ እንኢዮርብ

ዓም ፣ ሰው ፣ መራሹን ፣ ጣያት I እሱ ፣ እሙንቱ ፣ አማልክቲከ ፣ እስራኤል ፣ ዘአውፅኡከ ፣ እምድረ ፣ ግብጽ ፣ እያሉ ፣ ይስቱበትና ፣ ያስቱበት ፣ እንደ ፣ ነበረው ፣ ቃል ፣ ነው ፣ እንጂ I ክዚያ ፣ ልዩ ፣ አይደለም ። ባህላቸውና ፣ ትርጓሜያቸው ፣ ኹሉ ፣ ብሉይን ፣ ከሐዲስ I ሙሴን ፣ ከክርስቶስ ፣ የሚለይና ፣ የሚያጣላ ፣ የንባብ ፣ የምስጢር ፣ ደዌ ፣ ነው I ከወንጌና ፣ ከዝምታ ፣ በቀር ፣ ማስረኛ ፣ መድኀኒት ፣ የለውም ፣ (ኢሳ፭ ፣ ፭) ። በሐዲስ ፣ ኪዳን ፣ ሥላሴና ፣ አብ ፣ ወልድ ፣ መንፈስ ፣ የ ተባለው I ያው ፣ በብሉይ ፣ ኪዳን ፣ ኤሎሂም ፣ አደናይ ፣ ይሆዋ ፣ ሻዳይ ፣ ይባል ፣ የነበረው ፣ የአብ ርሃምና ፣ የይስሐቅ ፣ የያዕቆብ ፣ አምላክ ፣ ስለ ፣ ኾነ I ብሉይ ፣ ኪዳንና ፣ ሐዲስ ፣ ኪዳን ፣ ክንድ ፣ ጕንደ ፣ ሕይወት ፣ የተገኙ ፣ ጽጌና ፣ ፍሬ ፣ እንደ ፣ መኾናቸው I አምላክ ፣ ወሰብእ ፣ ካህን ፣ ወበግዕ ፣ በተባለው ፣ በመሲሑ ፣ በዐማኑኤል ፣ ደም ፣ ታርቀው ፣ ተስታልቀው I እንደ ፣ ነፍስና ፣ እንደ ፣ ሥጋ ፣ እንደ ፣ ባልና ፣ ሚስት I አንድ ፣ አካል ፣ አንድ ፣ አምሳል ፣ አንድ ፣ ሕግ ፣ ኹነው ፣ ክርሱ ፣ ከባለ ቤቱ ፣ በሐዋርያት ፣ እጅ ፣ ለእስራኤል ፣ ዘነፍስ ፣ (ለቤተ ፣ ክርስቲያን) ተሰጥተዋል ። እስራኤል ፣ ዘ ሥጋ ፣ የተባለች ፣ ቤተ ፣ አይሁድ ፣ ግን ፣ ክጥንትም ፣ ክኹዋላም ፣ ከሙሴና ፣ ከክርስቶስ ፣ ዦምሮ ፣ አሪት ፣ ሲሏት ፣ ጣያት I ወንጌል ፣ ሲሏት ፣ አሪት ፣ እያለች ፣ የአሪት ፣ የወንጌል ፣ ጠበኛ I የሙሴ ፣ የ ክርስቶስ ፣ ጓረኛ I የንቢያት ፣ የሐዋርያት ፣ ደመኛ ፣ ገፋሂት ፣ ሕግ ፣ ስለ ፣ ኾነች I መታረቃቸውን ፣ እንዳታይና ፣ እንዳትሰማ ፣ ዐይኑዋን ፣ ጨፍና ፣ ጕሮዋን ፣ ደፍና ፣ በሕልክ ፣ በንቢታ ፣ በሸፍጥ ፣ ባሉ ታ ፣ ትኖራለች ፣ (ማቴ፳፫ ፣ ፴-፴፮ ። ዮሐ፭ ፣ ፵፭-፵፯ ። ሮሜ፲፩ ፣ ፯-፲ ። ግብ፯ ፣ ፶፩-፶፫ ። ፳፫ ፣ ፳፭-፳፰) ። ክዚኽ ፣ የቀረውን ፣ የብሉይ ፣ ሐተታ ፣ በስማዕ ፣ እስራኤል ፣ ተመልክት I ስማዕ ፣ እስራኤልም ፣ የተባለ ፣ እንግሊዝዊው ፣ ሊቅ ፣ ማርቲን ፣ ፍላድ ፣ በጌዲዎንና ፣ በልጁ ፣ በጕዲት ፣ ስለሚመኩ ፣ ስለ ፣ ስሜንና ፣ ስለ ፣ ጕንደር ፣ ስላገራችን ፣ ፈላሾች ፣ ክኦሪትና ፣ ክንቢያት ፣ እንደ ፣ ንህብ ፣ ቀሥም I እንደ ፣ ወጥ ፣ ቀምሞ I አጣፍጠ ፣ ተርጕሞ I ባማርኛ ፣ ዐትሞ ፣ ያወጣው ፣ ታናሽ ፣ ምእላድ ፣ ነው I ታናሽነቱም ፣ እንደ ፣ ሰናፍጭ ፣ እንደ ፣ ሲርባ ፣ (ሚጥሚጣ) የኾነው ፣ ፍሬ ፣ ነው ። የጌደዎን ና ፣ የጕዲት ፣ ዜና ፣ እንዲት ፣ እንደ ፣ ኾነ ፣ በዋዜማ ፣ ታሪክ ፣ ተመልክት ፣ (ገጽ ፭፭-፴) ።

(ማስታወቂያ) I ጕልቄ ፣ ዘመንና ፣ ውዳሴ ፣ አምላክ ፣ ክነማስረሻቸው ፣ የተጣፉበት ፣ ምክንያት ። ቀድሞ ፣ ባገራችን ፣ ክግእዝ ፣ በቀር ፣ የዕብራይስጥ ፣ ወሬ ፣ አልነበረም I ዛሬ ፣ ግን ፣ በዘመናችን ፣ አይሁድ ፣ ለወገኖቻቸው ፣ ለፈላሾች ፣ መምህራን ፣ (ረበናት) ስደው ፣ የተማሪ ፣ ቤት ፣ ስላቆሙ I በወዲያ ፣ በጕንደር ፣ ፈላሾቹ ፣ ግእዝ ፣ ቋንቋና ፣ የብሉይ ፣ ትርጓሜ ፣ ክክርስቲያኖች ፣ እንዲማሩ I በዚኽም ፣ በሸዋ ፣ ክርስቲያኖቹ ፣ ወደዚያ ፣ እየገቡ ፣ ክፈላሾችና ፣ ክረበናት ፣ ዕብራይስጥ ፣ ቋንቋ ፣ ሲማሩ ፣ አይተን I የተማሩትም ፣ አሪት ፣ አይሁድን ፣ በዘመን ፣ ቀጥር ፣ ሲያጸድቁና ፣ ሲያጐላምሱ ፣ አሪት ፣ ግእዝን ፣ ሲያኰስሱ ፣ ስምተን I ቋንቋቸውን ፣ ከመሳተፋችን ፣ የተ ንግ ፣ እንዚኽን ፣ ክፍሎች ፣ ባጭር ፣ ቃል ፣ ጥር ፣ ላንባቦችና ፣ ለተማሮች ፣ መስጠት I የሚገባን ፣ ኹኖ ፣ አገኘነው ። ኹለቱንም ፣ ነገር ፣ ፊደልና ፣ ቋንቋ ፣ የተማሪ ፣ ቤት ፣ የሚያገናኛቸው ፣ ስለ ፣ ኾነ ፣ ክርስቲያኑ ፣ የዘመን ፣ ቍጥር ፣ የኤሎሂም ፣ ምስጢር ፣ እንደ ፣ አይሁድ ፣ መስሎት ፣ በፈላሻ ፣ ባህል ፣ እንዳይታለል ፣ እንዳይሸነገል I ፈላሻውም ፣ አሪት ፣ ነቢያት ፣ ከወንጌል ፣ የሚጣሱና ፣ ትርጓሜያቸው ፣ እንደ ፣ ርሱ ፣ ዐሳብ ፣ መስሎት ፣ ክክርስቲያን ፣ ትምርት ፣ እንዳይርቅና ፣ እንዳይከለክል I ለኹለቱም ፣ ወገን ፣ እንደ ፣ ዳኛ ፣ የወል ፣ እንደ ፣ ምሰሶ ፣ የመክክል ፣ ኹኖ ፣ የዘመን ፣ ታሪክ ፣ የሃይማኖትን ፣ መልክ ፣ የሚያሳይና ፣ የሚያስረዳ ፣ ጥሩ ፣ መስታዮት ፣ ይኽንላቸው ፣ ዘንድ ፣ ለጊዜው ፣ የሚያሻ ፣ መኾኑን ፣ ዐውቀኁ ፣ ስለ ፣ ፈላሻና ፣ ስለ ፣ ክርስቲያን ፣ ጥቅም ፣ ከፊደል ፣ ጋራ ፣ ጥረንዋል ። (ተረት I ስለ ፣ ተማሪና ፣ ስላንባቢ ፣) I ክዳቦ ፣ የተገኘን ፣ ወጥ I ዐብረኽ ፣ ግመጥ ። በሰጡኽ ፣ አትስነፍ I ክስጡኽ ፣ አትለፍ ። ክበላ ፣ ብላ I ክስው ፣ አትጣላ ።

መ ክ ደ ኛ ፣ ግ ጥ ም ።

የምድረ ፣ ከነዓን ፣ ወተትና ፣ ማር ፣
ብሉይና ፣ ሐዲስ ፣ እግዚአብሔር ፤
ፅቱን ፣ ክፍል ነ ባሕር ፣ ፅቱን ፣ ክፍል ፣ የብስ ፣
ክምረት ፣ ከይብሰት ፣ ሊያድን ፣ ሊፈውስ ፣
የጐርፉ ፣ አወራረድ ፣ ግሥገሣ ፣ ዘመቻ ፣
ከኢየሩሳሌም ፣ እስከ ፣ ምድር ፣ ዳርቻ ።
ምስጢረ ፣ ሥላሴ ፣ የሰማይ ፣ ወተት ፣
መገመሪያ ፣ ትምርት ፣ ምግበ ፣ ሕፃናት ፤
ክርባዕቱ ፣ እንስሳ ፣ ከሱራፌል ፣ ጡት ፣
እንኢሳይያስ ፣ ወልበው ፣ የጠጡት ።
የተረፈውንም ፣ ውሉደ ፣ ጥምቀት ፣
ሐዋርያት ፣ አርድእት ፣ ሠለስቱ ፣ ምእት ፣
በልባቸው ፣ ቁጀ ፣ መልተው ፣ ቢያረጉት ፤
እንደ ፣ ቅቤ ፣ እንዳይብ ፣ እንደ ፣ ወገሜት ፣
የማይለየውን ፣ ለመለያየት ፣
አርዮስ ፣ የናጠው ፣ አይሁድ ፣ የገፉት ።
ምንም ፣ ባንዱ ፣ አካል ፣ ላይ ፣ ቢጨመር ፣ ስብእና ፣
ጣዕሙ ፣ አይለወጥም ፣ እንደ ፣ ማየ ፣ ቃና ፤
በተዋሕዶው ፣ ውስጥ ፣ ባሕርይ ፣ የሚያጸና ፣
ተዐቅቦ ፣ የሚሉት ፣ መድኀኒት ፣ አለና ።
የመድኀኒቱም ፣ ኀይል ፣ የሚፈውሰው ፣
ኢየሱስ ፣ ናዝራዊ ፣ አምላክና ፣ ሰው ፤
አንድ ፣ አካል ፣ አንድ ፣ ልጅ ፣ ምንትዋ ፣ ልደት ፣
የባሕርይ ፣ ተዐቅቦ ፣ የማይፈርስበት ።
ኹሉን ፣ የሚያቈራኝ ፣ ክአብ ፣ ከመንፈስ ፣
አንዱ ፣ አካል ፣ ስንሰለት ፣ የሱስ ፣ ክርስቶስ ፤
በኹለት ፣ ፍንጀቹ ፣ በትእዛዛት ፣
የተሰቀሉበት ፣ ኦሪት ፣ ነቢያት ።

ዐሥር ፣ የሊቃውንት ፣ ዐዋጅ ።

ምስጢረ ፣ ሥላሴን ፣ ምስጢር ፣ ያሰኛት ፣
የባሕርይ ፣ አንድነት ፣ ያክል ፣ ሦስትነት ፤
ምንታዌ ፣ ርባዔ ፣ ስለሌሉበት ።
ምስጢረ ፣ ሥጋዌን ፣ ምስጢር ፣ ያሰኛት ፣
የባሕርይ ፣ ምንታዌ ፣ ያክል ፣ አንድነት ፤
ቱላሔ ፣ ቡኣይ ፣ ስለሌሉበት ።
በሥላሴ ፣ ምስጢር ፣ እንዳንሳሳት ፣
በሥጋዌም ፣ ምስጢር ፣ እንዳንሳሳት ፣
ለይቶ ፣ ጠንቅቆ ፣ ይዝን ፣ ኹለት ፣ ስልት ፣
ማስተዋል ፣ ይገባል ፣ መላልሶ ፣ ማየት ፣
በሐዲስ ፣ ትርጓሜ ፣ በሊቅ ፣ አፈታት ፣
ብሉይ ፣ እንደንጀራ ፣ በሚፈተፍት ።

ምክር ፣ ሠናይት ፣ ለሑሱ ፣ ዘይገብራ ።

የተዋሕደን ፣ ባህል ፣ የኦርቶዶክስን ፣
በሦስቱ ፣ ጉባኤ ፣ የተባለውን ፣
አስተውሎ ፣ ጠንቅቆ ፣ ያልሰማ ፣ ገሮኝ ፣
ከጎረ ፣ ቤት ፣ ጋራ ፣ እንዳያጣላኝ ፤
ምስጢረ ፣ ሥላሴን ፣ ሳታደላድል ፣
ምስጢረ ፣ ሥጋዌን ፣ ዐውቃለኹ ፣ አትበል ።
ዐውቃለኹም ፣ ብለኝ ፣ ብትከራከር ፣
ይፈርሳል ፣ ነገርኝ ፣ ጥቅመ ፣ ሰናያር ፤
ቋንቋኝም ፣ ይለያል ፣ ክቅዱስ ፣ መጽሐፍ ፣
እንዳውጣኪ ፣ አንደበት ፣ እንዳርዮስ ፣ አፍ ።
አፍኝ ፣ እንዳመጣም ፣ ነገር ፣ ብትተች ፣
ውርድ ፣ ይነዙብኻል ፣ የጉባኤ ፣ አፎች ፤
እናባ ፣ አትናቴዎስ ፣ እነቄርሎስ ፣
የማርቆስ ፣ ልጆች ፣ የአባ ፣ አንበስ ፤
ለቤተ ፣ ክርስቲያኑ ፣ እስራኤል ፣ ዘነፍስ ፣
እግዜር ፣ ያበቀለው ፣ በወንጌሉ ፣ ራስ ፣
የድርሳናቸው ፣ ቀንድ ፣ ስማይ ፣ የሚጠቅስ ፣
ሞ ራውም ፣ ትርጓሜ ፣ ምድር ፣ የሚያብስ ።
ክዚኝ ፣ ዐልፎ ፣ ተርፎ ፣ እንዳይገኝፍል ፣
የቀረው ፣ ሐተታ ፣ ተክድኖ ፣ ይብሰል ።



ምስለ ፣ ፍቁር ፣ ወልዳ ።

በኋኗ ፣ ገጽ ፣ ከማስረሻ ፣ በፊት ፣ በኍኗኛ ፣ መሥመር ፣ ከውዳሴ ፣ አምላክ ፣ የቀረ ፣ ቃል ።

ዝኩ ፣ ውእቱ ፣ ዘተነግረ ፣ በመጻሕፍት ፣ አምላካውያት ፤ ወዘተብህለኒ ፣ እምሊቃውንት ፤ ም ኵራብ ፣ እንመት ፣ ዐምረ ፣ ወቤተ ፣ ክርስቲያን ፣ ተዐጽፈቶ ፤ አሕዛብ ፣ አስተጋብኡ ፣ ጽጌ ፣ ረዳ ፤ ወ ሦኩስ ፣ ተርፈ ፣ ጎበ ፣ አይሁድ ። እንክሰ ፣ ብኵርና ፣ ለን ፣ ወአኮ ፣ ለአይሁድ ፤ እስመ ፣ ተስፋሆሙ ፣ ወብኵርናሆሙ ፣ ለሕዝብ ፣ ናሁ ፣ ኮን ፣ ለአሕዛብ ፣ እምእግዚአብሔር ፣ አብ ፤ ከመ ፣ ብኵርና ፣ ዔሳው ፣ ለያዕቆብ ፤ ወቅድምና ፣ ግሩም ፣ ኤልያብ ፣ ለዳዊት ፣ ንጹሐ ፣ ልብ ። ያዕቆብሰ ፣ ወዳዊት ፣ ዐማኑኤል ፣ ሰባኬ ፣ ወንጌል ፤ አምላክ ፣ ሥግው ፣ ፍጹመ ፣ ትስብእት ፣ ወፈጸሜ ፣ ትንቢት ፤ ሰማ ያዊ ፣ ወልደ ፣ አብ ፣ ዋሕድ ፣ ወናዝራዊ ፣ ንጉሠ ፣ አይሁድ ፤ አበ ፣ አበው ፣ ወበኵረ ፣ ብዙኃን ፣ አንው ። መሥላሴንኒ ፣ ቅድስት ፣ ወንጽሕት ፣ እምግብረ ፣ ምንታዌ ፣ ወትርብዕት ፣ ትጹዋዕ ፣ በ ብእሲ ፣ ከመ ፣ አብ ፤ ወከመ ፣ እምኒ ፣ በብእሲት ፤ የማና ፣ ስፋሕ ፣ ለጸግዎ ፣ ጸጋ ፣ ሲሲት ፤ ወፀጋ ማኒ ፣ ድልው ፣ ለሐቂፈ ፣ ውሉድ ፣ ፍጥረት ። ይእቲኬ ፣ ኤሎሂም ፣ አምጻኢተ ፣ ዅሉ ፣ ዓለም ፤ ፈ ጣሪት ፣ በኢጸምዎ ፤ ወጸጋዊት ፣ በኢደንጽዎ ። ለአብናሃ ፣ ስብሐተ ፣ አብ ፤ ወለእምናሃ ፣ ውዳሴ ፣ እም ፤ ከመ ፣ ውዳሴሃ ፣ ለማርያም ፤ ይደልዎ ፣ ይደልዎ ፣ ወይሰናአዎ ፣ በርትዕ ፣ በዅሉ ፣ ጊዜ ፣ ወ በዅሉ ፣ ሳዕ ፤ እምአፈ ፣ ውሉዳ ፣ መላእክት ፣ ወሰብእ ፤ አሜን ።

የስሕተትና ፣ የግድፈት ፣ መግለጫ ።

አንባቢ ፣ ሆይ ፤ ባኋኗው ፣ ገጽ ፣ ከተጣፈው ፣ ዐዋጅ ፣ በፊት ፣ የነአ(ዐ) ፣ የነሀ(ሐ) ፣ ተወራሽነት ፣ እንደሚገባው ፣ አልተጣፈምና ፤ ካዋጅ ፣ በዅዋላ ፣ ወደ ፣ ፊት ፣ ያለውን ፣ ተከተል ። ሥፉ ፣ ዅሉ ፣ ባንድ ፣ ጊዜ ፣ አይከናወንም ።

(ገጽ)	(መሥመር)	(ስሕተት)	(ዕርም)
፱	፳፭	ያምርኛ ፡	ያማርኛ ።
፯	፲፯	ክልፉ ፣	ክአልፉ ፣ ካ ።
፲	፳	ባኋየኛው ፣	ባኋኛው ፣ ክፍል ።
፲፱	፯	ዐዊቂ ፣	ዐዋቂ ።
፲፭	፳	ሯሡዋ ፣	ሻሡዋ ።
፡	፲፯	ባእድ ፣	ባዕድ ።
፴	፴	ውስጡ ፣ ግ	ውስጡም ፣ ግ ።
፴፭	፴፭	ጓድጓድ ፣	ጕድጓድ ።
፴፱	፲፫	፳፱—፯ ፣	፳ ፣ ፱—፯ ።
፶፳	፴፯	አርባእቱ ፣	አርባዕቱ ፣

ስእለት ፡ ወአስተብቊዮት = ልመናና ፡ ምልጃ ።

ይኸን ፡ ጨቅላ ፡ መጽሐፍ ፡ የምታዩ ፡ ኹሉ ፡
ዐደፉ ፡ ስለኔ ፡ ማፊያም ፡ ማፊያም ፡ በሉ ፤
በሆዲ ፡ ያለዉን ፡ የትምርት ፡ ሺል ፡
አለዉ ንቅ ፡ እንድወልድ ፡ እንድገላገል ፤
ከኻያ ፡ ስድስቱ ፡ ወንደች ፡ ፊደላት ፡
አርግፐለኹና ፡ መዝገበ ፡ ቃላት ።

ስንት ፡ እልፍ ፡ አበው ፡ ናቸው ፡ አርግዘው ፡ የሞቱ ፡ ?!
ቀኝ ፡ እኛቸው ፡ ዐጥሮ ፡ ጥፈት ፡ በማጣቱ ፤
እጂ ፡ እንዳባቶቼ ፡ እጅ ፡ ተምሮ ፡ ባይጥፍ ፡
ከሆዲ ፡ ባሎጣም ፡ ይኸ ፡ ጨቅላ ፡ መጽሐፍ ።

ለትምክሕት ፡ አይደለም ፡ ይኸን ፡ መናገሬ ፡
ለማስቀናት ፡ እንጂ ፡ ስንሉን ፡ ገበሬ ፤
ሐዋርያም ፡ ሲጥፍ ፡ ወዳርድእቱ ፡ መንጋ ፡
ቅኑ ፡ አስቀኑ ፡ ይላል ፡ ስምትበልጥ ፡ ጸጋ ።

እስመ ፡ አሪት ፡ በሙሴ ፡ ተውህበት ፤ ጸጋሰ ፡ ወጽድ
ቅ ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ኮነ ፡ (ዮሐ፩ ፡ ፲፯) ።